
**በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት**
**ተከባብሮ ለመኖር**
**መደማመጥ!**
**መቻቻል!**

**ኢትዮጵያዊ**
**የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት**
**በአማርኛ**
**$2.75**

# ላንዳፍታ



"በተመክሮአችን የቀሰምነው ነገር አንዱ ትግል ብዙ ውጣ ውረድ እንዳለው ነው . . ."
አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ
ከኢህአፓ መሥራች አባሎች
ገጽ 22




"በፈጠራ ወሬ እባካችሁ ስሜን አታጥፉ! በአገሬ አንድነት የማምን፤ አገሬን የምወድ ፍጹም ኢትዮጵያዊት ነኝ! ይህንን ስሜቴን ማንም አያደፈርስብኝም! "
አርቲስት አስቴር አወቀ
ገጽ 27

ነሐሴ ፲፱፻፹፱
መስከረም ፲፱፻፺
፮ኛ ዓመት
ቁጥር ፩

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
SEPTEMBER 1997
Vol.6 No.1



# የኢትዮጵያ መንደር







## ETHIO VILLAGE
### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



በቺካጎ ታላቁ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት

ቀይወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ
ሽታው ግቡ ይላል ገና እያሉ ደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገርዎ የገቡ ያስመስላልና።
ዱለት የበግ ወጡ አልጫ ፍትፍቱ፤
ዕሮብና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በአስራሁለት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት
ፍጹም ኢትዮጵያዊ ለሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት፤
አገር ሲናፍቆት።

**አፀደ ይመር**

# ማ ው ጫ CONTENTS


4 ከአዘጋጁ

5 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

6 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

13 ከአንባብያን

15 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

18 የ25ኛው ኢህአፓ ምስረታ በዓል
— አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ ቃለ መጠይቅ
— አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ
— የወጣት ህምራዊት ተስፋዬ ደበሳይ መልዕክት

27 የአርቲስት አስቴር አወቀ ቃለ መጠይቅ

32 ልብ ወለድ – "አትዘንጋ"
(ሰይፉ ብሻው)


41 የግጥም ጉባኤ

42 ስፖርት – የአትላንታ ቡድን ሻምፒዮና ሆነ!!

43 "መንግስት ሲበድልና ፍርድ ሲያጓድል
ቤተክርስቲያን የመገሰፅ ኃላፊነት አለበት!!'
(ቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ)

45 ከአበው (መጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

46 የሰንጠረዥ ጨዋታ

አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ (22)



አርቲስት አስቴር አወቀ (27)




ከንቲባ ቢል ካምብልና
ኢትዮጵያውያኖች (31)

ሽፋን — አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ — የኢህአፓ መሥራች አባል
አርቲስት አስቴር አወቀ


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዎ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

©COPYRIGHT LANDAFTA 1997

ላንዳፍታ
ነሐሴ ፹፱ /መስከረም ፲፱፻፺
፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩
LANDAFTA
AUG/SEPT 1997 Vol. VI - No.1

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*
**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Saefu Bishaw*
*Wuhib Tiruneh*
*Rev. Mekbib Atnaw*
**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant
Express Food Mart
Merkato Market
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Durham, NC
Blue Nile Eth. Cusine
Denver, CO
Emebet Worku
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu
London

# ከአዘጋጁ

**እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ!!**
**እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!**
**መጪው ዓመት የሰላም፤ የደስታ፤ የጤናና**
**የብልፅግና እንዲሁም ለውድ አገራችን የሰላምና**
**የብልፅግና ዓመት እንዲሆን ምኞታችንን እንገልፃለን!!**

እንደምን ከርማችኋል። ይኸው ብቅ ብለናል ደግሞ።

እኛም እንግዲህ ስድስት አመት ሆነን። በዚህ የስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ 29 እትሞች አውጥተናል። የተለያዩ ማህበራዊና አገር ነክ ጉዳዮችን ዳስሰናል፣ አሳውቀናል፣ አወያይተናል፣ አዝናንተናል ብለን እንገምታለን። በዚህ በውጭ አገር ፊደላችን በማተሚያ ቤት በማይታወቅበት አገር በአማርኛ መጽሄት አዘጋጅቶ ለመበተን ትንሽ ማስቸገሩ አይቀርም። ቢሆንም ሁሉንም ተወጥተን መጽሔቱን በወቅቱ ለማድረስ ሙከራ አድርገናል። ስለ ጥራቱ፣ ስለ ምናምኑ ለእናንተው እንተወውና ብቻ ይኸው እስካሁን አለን፣ ብዙ አድገናል ባንልም አለን አለን እንላለን። የማይጠረጠረው ግን ለመጽሔቱ እድገትም ሆነ መኖር የእናንተው የአንባቢዎቻችን ተሳትፎና ጥረት፣ አይዟችሁ ባይነት ወሳኝ መሆኑን አንክድም። አለያማ ምን ተይዞ ጉዞ! ይሆናል።

ይኸው እንግዲህ እንደወትሮአችን በዛሬው እትማችን የአገራችንን ጉዳይ የሚመለከቱ ዜናዎችንና የተለያዩ ዘገባዎችን ይዘን ቀርበናል። የ25ኛውን የኢህአፓ ምስረታ በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባና ከተለያዩ የድርጅቱ ሰዎች ጋር ያደረግነው ቃለ መጠይቅ ይኖረናል። ብዙዎቻችን በር ስማቸው ሲጠራ የሰማናቸው የኢህአፓ መሥራቾች አንዱ የሆኑትን አቶ ኢያሱ ዓለማየሁን ስለ ትግል ታሪካቸው እንዲነግሩን ጋብዘናቸዋል።

ባለፈው እትማችን እንደገለጽነው ከጥቂት ወራት በፊት ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ ወደ አገሯ ሄዳ ትርኢቶች በማሳየቷ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ተቃውሞዎች የደረሰባት መሆኑን በማውሳት ይህንን በተመለከተ በበኩሏ የምትለውን ለመስማት እንድንችል ታዋቂዋን አርቲስት አስቴር አወቀን ይህን ቃለመጠይቅ አቅርበንላታል።

እንግዲህ ዝግጅቱን እነሆ ብለናል አንብቦና አጣጥሞ አስተያየቱን መስጠት ለእናንተው ትነናል። ደህና ሁኑልን።

ስለ መጽሔታችን መስጠት የምትፈልጉት
አስተያየት ወይም በመጽሔቱ እንዲወጣ
የምትፈልጉት ጽሑፍ ካለ በአድራሻችን ይላኩልን።

የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- landafta@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት ከወርቃየሁ

ወንድሜ ገብርዬ፤ ጤንነቱን እንዴት ነህ፤ እኔ እንዳለሁ አለሁ ብልህ ይበቃል። “መኖር ደጉ” አሉ አባቶቻችን፤ እንግዲህ ይኸው “ከድጡ ወደ ማጡ” እያልን ሌላ አዲስ ዓመት ልንቀበል ነው። የበለጠ ችግር፤ የበለጠ ሰቆቃ፤ ደግሞም የበለጠ ዕዳ ይዘን “አበባዬ ሆይ!” ልንል ነው። ትዝ ይልሃል፤ አያ ይግለጡ እንዲህ እንዳሁኑ ሳይከዳኝና ድምጹን ሳያጠፋ እዚቹ ላንዳፍታ ላይ “ተይ አንቺ መስከረም!” ብሎ የገጠመው። አልሰማ አለችን፤ ድሮ ድሮ እንቁጣጣሽ ሲመጣ አዲስ ተስፋ፤ አዲስ ዕቅድ ይዘህ ነበር የምትቀበለው። ታዲያ ይህ ያልታደለው ወገኔ ዛሬ መኖሩን እንጂ ነገ መድረሱን ስለማያውቅ ብዙም ዕቅድ አያወጣ፤ ብዙም አያልም፤ አቅዶ አቅዶ፤ አልም አልሞ አብቅቷል፤ ተስፋ ቆርጦአል ልልህ ግን አልደፍርም። አይምሰልህ! የሚመች ጊዜ የሚጠብቅ የተኛ ነብር ነው የኛ ሰው፤ “ጊዜ እስኪያልፍ . . .” ይልና ያቺ አመቺ ቀን ስትመጣ ታዲያ እኔን አያድርገኝ፤ ለጠላቱ ቆምጣጣ ነው።

አያ ገብርዬ፤ሰሞኑን እንግዶች ነበረባችሁ አሉ፡፡ ኢትዮጵያዊ የእንግዳ መቀበልና መስተንግዶአችሁን ረስታችሁት ነው መሰለኝ ሹማምንቶቻችንን “——— የነካ እንጨት” ያደረጋችሁዋቸው። እናንተ ምናለባችሁ ልጄ? በርቱልን ብቻ፤ የነሱ ግን አይገርምህም! ንቀታቸው ልበል ወይስ ድፍረታቸው! እስቲ ሰው ከመሬት ተነስቶ ነገር ይፈልጋል? ምናለ እዚሁ እኛኑ ቀጥቅጠው ቢገዙ! ነገሩ ምን መሠለህ? እዚህ እንደልባቸው እየፈነጩ ፤ እንደልባቸው እየዋሹ ዝም ተብለው የለ፤ ሁሉ ቦታ እንደዚያ መስሏቸዋል።

ወንድሜ ገብርዬ፤ ኑሮና ብልሃቱ እንዴት ይዞሃል? እናንተማ ምን አለባችሁ፤ በያ ሰሞን የጠቃቀስካቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ብዙ የምለው ይኖረኛል። የዛሬን አያድርገውና ያኔ አያ ይግለጡን ይህን በተመለከተ ብዙ ቁም ነገር አጫውቼው ነበር። እንዲያው አደራ የምትልልኝ ጉዳይ አለኝ፤ እዚያ ለሚኖረው ወገኔ፤ በአገርና በዘመድ ናፍቆት ወደዚህ የመትመጡ ወገኖቼን እንዲህ በልልኝ። የኛን ሁኔታና ያለንበትን ኑሮ እባካችሁ ስትመጡ ከምትሰፍሩበት ሂልተን ሆቴልና ከምትዝናኑባቸው ቦታዎች አንፃር አትገምግሙ በልልኝ፤ ለናንት በአሜሪካን ዶላር ለምትኖሩት ሁሉ ነገር ርካሽ ነው፤ ለኛ በገሸበና ባሽቆለቆለ የኢትዮጵያ ብር ለምንኖረው መዝናኛው ቀርቶ የዕለት ዕለት ኑሮ መደጎሚያው አልሟላ እያለን ወር ተወር ዕዳ በዕዳ እየሆን መሆኑን ተገንዘቡ። ይህን ልል የበቃሁበትን አጋጣሚ ላጫውትህ። አንድ የዘመዴ ልጅ ለአባት ለናቱ የፃፈውን ደብዳቤ ተመልክቼ ቢገርመኝ ነው ይህን ለማለት የበቃሁት። የዚህ የዘመዴ ልጅ ጓደኛ የሆነ አንድ ዘመነኛ በቅርቡ እዚህ መጥቶ ይመለሳል። እኔ እንኳ መምጣቱን ነው እንጂ የሰማሁት አላገኘሁትም፤ የሰፈረው ሂልተን፤ በየት ተደራርሰን። ከዚያም ሲዝናና ከርሞ ይመለስና “አገራችን በቴክኖሎጂና በኢንዱስትሪ ከፍተኛ ደረጃ እደረሰች ነው፤ እኔ ም አገሬ ተመልሼ ንግድ ሥራ ልጀምር ነው፤” ብሎ የነገረውን ተንተርሶ ይኸው የኛ ዘመድ ለአባት ለናቱ የደስታ መግለጫ ደብዳቤ ይልካል። ይህ እንግዲህ በቅርቡ እኔ የማውቀው ነው። በየቦታው ያለውን ደግሞ ቤቱ ይቁጠረው። በዚህ ዓይነት መልክ ከናንተ ወደዚህ እየመጡ ንግድ (በናንተ ቋንቋ ቢዝነስ) የጀመሩትን ኢትዮጵያውያን ስከታተል ያየሁት የንግድ ዓይነት በአብዛኛው የመዝናኛ ያውም ባህል የሚያበላሹ ክለቦች ቡና ቤቶችና የመሳሰሉትን ነው። ኢትዮጵያ የቸገራት የቡና ቤትና የዳንስ ቤት አይደል? አዲስ አበባን በአንድ ምሽት አንድ የአሜሪካን ከተማ ለማስመል የሚሮጡ ይመስላል። እና “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ፤ በነኚህ የመዝናኛ ማዕከላት ለመዝናናት የሚሽቀዳደሙትን ታዳጊ ወጣቶች በተለይ ሴቶች ልጆችን ስታይ መፈጠርህን ነው የሚያስጠላህ። እና የምትልልኝ፤“እባካችሁ!” በቃ! ይኸው የሚበቃ ይመስለኛል፤ መልዕክቴ የሚገባው ይገባዋል። “ብልግና ብልግናውን እዚያው ተውትና የሚበጅ የሚበጀውን አምጡልን ከመጣችሁ። እና ደግሞ ያለንበት ሁኔታ ሰላ ም መሆኑን እኛ እስክንነግራችሁ ጠብቁ እንጂ እናንተ ስለኛ ሆናችሁ ባታወሩ ምን ይቀርባችሁዋል? ስለሌለን ሰላም ስታወሩ ስላለብንና ስላያችሁት ችግር ማውራት ምነው አፋችሁን ያዘው? ስለለማኙ ብዛት! ስለኑሮ ውድነት! — ” ይህን ንገርልኝ። እንደሰማሁትማ ከሆነ ገና ወደዚህ መምጣት ሲያስቡ ነው አሉ ስለዚህ መንግሥት ደግነት ፉ ከካድሬዎቹ ብሰው አነሱ ናቸው የሚለፍ ይባላል፤ እውነት ነወይ? ሆዳም ምንትስ በላቸው!

ወንድሜ ገብርዬ፤ ለመሆኑ እንናፍቃችኋለን ወይ? አሜሪካ እንደሁ ቦልቧሌ አገር ናት አሉ፤ ምንም ትሁን ታዲያ ወንዝንና አገርን የምታስረሳ አትመስለኝም። ልክ ነኝ ወይስ ተሳሳትኩ?

በል እስቲ በአዲሱ ዓመት የሚሆነውን ደግም እንጠብቃለን።

# ሠላምታ ከባህር ማዶ ከገብርዬ – ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ፣ እንደምን ሰንብተሃል?

ጊዜው ኢትዮጵያን ከጉሰኞችና ከዘረኞች ነፃ ለማውጣትና መላውን ህዝብ ለማቀራረብ የተራቀቀ ታክቲክና ስትራቴጂን የሚጠይቅበት ወቅት ነው። በእውነቱ ይህን የተረዱ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ የወያኔን አገሪቷን የመበታተን ፖሊሲ በመቃወም ያደረጉት ተሳትፎ እጅግ የሚያስደስት ነው። ለዚህ የተደራጀ ግብ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በመሰዋት በአንዳንድ ቦታም የእነርሱንና የቤተሰቦቻቸውን ሕይወት አደጋ ላይ በመጣል መጋለጥን ሳይፈሩ ለሰሩ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ምስጋና ይድረሳቸው። በአሁኑ ወቅት እርከን በእርከን እየሸወደ በውጭም ሆነ በሀገር ቤት የድንጋጤ ብርክ ይዞት ሕዝብን በመከፋፈል ላይ የሚገኘው የወያኔ መንግሥትና የስለላ ድርጅቱ ልዩ ልዩ ታክቲኮችን እየተጠቀመ ስለሆነ ትግላችንን ከዚህ አደጋ ለመከላከል በቅተንና ፀንተን መታገል ይገባናል። በደምና በሕብረት አጥንት የተፃፈው ታሪካችን አሁንም ለሰላምና ለአንድነትና ለሀገራዊ ልዑላዊነት የጀግና ዜጐችን ደም ገብሮ ሀገሪቷን እንደገና እንደሚገነባ ጥርጥር የለኝም።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

ዛሬ ግን ከሌላው ጊዜ በተለየ መንገድ ነሸጥ አድርጎኛል። ላንጐራጉር ብልህሳ! በስደት ላይ ያለው ማንኛውም ሀገር አፍቃሪ ዜጋ ከበድንነትና ከግሳንግስ ኑሮ ባሻገር የሀገር ትውስታዊ ናፍቆት (Nostalgia) የማይሰማው እንዳይመስልህ። እንጉርጉሮ አንዳንዴ ለራስ ብቻ የሚሰማ ሳይሆን ከውስጥ ፈንድቶ ጓደኛን በመቀስቀስ ስደተኛው ውስጥ የእሳት ቋያ ይለቃል። ለነሆቺሚን፣ ለነፋኖን፣ ለነአሚልካር ካብራል፣ ለነኬኒያታ፣ ለነባልቻ አባ ነፍሶ፣ ለነገረሱ ዱኪ፣ ... ወዘተ የብሔራዊ መንፈስና መራር ወይም ኮስታራ ሐሞት በመለገስ ያጠናከራቸው የእንጉርጉሮ ትውስታዊ ተምኔት ነው። ስነፅሑፍ፣ እንጉርጉሮና ሽለላ ወኔን በማንደድ የሀገር ፍቅርን ብሔራዊ ደም እንደተንቦልባይ ቤንዚን ያቀጣጥለዋል፤ እሳቱ ብርቱ ሆኖ ጠላትን ሲበላ ወገንን ደግሞ በወላፈኑ ይቆጠቁጠዋል። ወኔን ቀስቃሽ እንጉርጐሮና ዘፈኖች የብሔራዊ ስሜት መግለጫዎች ናቸው። «እኔስ ባገሬ እንኳን ሰው ወፍ አለምዳለሁ፣ አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ፣ እሰይ ስለቴ ሰመረ»፣ ሽለላ፣ በገና፣ የዋሽንትና የመሰንቆ ትዝታዎች ... እና የመሳሰሉት በኢትዮጵያ ከህዝባችን ጥሩና መጥፎ ትካዜ የተለዩበት የታሪክ ወቅት የለም። የእነዚህንም ወኔ ቀስቃሽነት በመረዳት ነው ወያኔ የጀግኖች ዘፈን እንዳይዘፈን «በኋላ ቀር» ባህል ስም ሽለላና ቀረርቶ ላይ እገዳ እንዲደረግ ያደረገው። «እኔስ ባገሬ ወፍ አለምዳለሁ»፣ «አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ»ና እሰይ ስለቴ ሰመረ» የሚሉት የተለምዶ ዘፈኖች ዜማቸውን ሳይለቁ እንደወቅቱ ትርጉማቸውን ከኢትዮጵያ ህዝብ በሶትና ትግል ጋር በማጣመር ህዝብን ቀስቅሰዋል። የአንቂና ቀስቃሽ የኪነት ሰዎቻችንም ይህንን የባህል ቅርስና ሀብት እንደአመቺነቱ ለሕዝብ ማስተማር አለባቸው ብዬ አምናለሁ። ከላይ የተጠቀሱት ዘፈኖች በሰምና በወርቅ አጊጠው የዘማሪውን ወኔ ብቻ ሳይሆን የሰሚውንም ስሜት ይቀሰቅሳሉ። እነዚህ የባህል ቅርስና ሀብት (Cultural Treasures) ዱሩን፣ መንገዱን፣ ወንዙንና ሸንተረሩን በመጥቀስ አድማጭን ይኮረኩራሉ። ሦስቱም ግጥሞች አንዳንዴ በፈረቃና በተከታታይነት ሲዘፈኑ ሰምተናል፤ መልዕክታቸውም ይያያዛል። «እኔስ ባገሬ እንኳን ሰው ወፍ አለምዳለሁ» ከሌሎቹ ጋር ሲዛመድ ትርጉሙ እንደዚህ ነው። ፋኖን መመልመልና ማለማመድ ተግባሬ ነው፤ በለመድኩት ሰርጥና ጫካ እንኳን ለሰውና ለወፎም አፎጮቼ ከእርሷ ጋር እግባባለሁ፤ ታጋዮችንም ወፎን እንዳለማመድኳት ሁሉ ከጠላት ጉያ ሳይቀር ፈልቅቄ ለኅብረትና ለአንድነት አሰልፋቸዋለሁ። እንዳሞራም ስሜቴና ናፍቆቴ በሀገሬ ሰማይ ላይ እየበረሩ ውበትን ይቃኛሉ፤ ለመፍትሄ ፍለጋ ስለቴም ይሳካል ወይም ይሰምራል ማለት ነው።

እንግዲህ ወንድም ወርቃየሁ ከአንባቢያን ጋር እስክስታችንን እያስነካን እናንጐራጉር። እኒህን ግጥሞች ስናነብ ስንኞቹ ራሳቸው ስለሚመሩን ጮክ ብለን እናዚማቸው እኔም አብሬ እየዘመርኩ ነው። እምባችሁ ሊመጣ ስለሚችል እኔን ተጠያቂ እንዳታደርጉኝ፤ ታሪካችሁን ጠይቁ።

እኔስ ባገሬ እንኳን ሰው
ወፍ አለምዳለሁ (አዝማች 2 ጊዜ)
አለምዳለሁ...አሆ
አለምዳለሁ...አሆ
እኔስ ባገሬ እንኳን ሰው
ወፍ አለምዳለሁ
የ ት ግ ሉ ን...አሆ...ጉራማይሌ...አሆ
የሙዳዬን...አሆ...የእውነት ቅሌ...አሆ
የፋኖዬን...አሆ...የመስቀሌ...አሆ
የማህተቤን...አሆ...ያደዋውን...አሆ
ግዳይ ጥዬ...አሆ...መዘመሩን...አሆ
ለፍትህ ሞት...አሆ...መሰዋቱን...አሆ
አዝማች (2 ጊዜ)
የማምዬን...አሆ...የታሪክ ክር...አሆ
ያባቶችን...አሆ...የወል ማኅበር...አሆ
የወገኔን...አሆ...የሁሉም ድር...አሆ
ነፃነቴን...አሆ...ያንድነት ክብር...አሆ
አዝማች (2 ጊዜ)
በሀገሬም... አሆ... እየሞትኩ... አሆ
በስደትም... አሆ... እየሞትኩ... አሆ
በተስቦም... አሆ... እየሳልኩ... አሆ
በመንደሬም... አሆ... እየቆምኩ... አሆ
አቀርቅሬም... አሆ... እየቻልኩ... አሆ
ሲበዛብኝ... አሆ... እያመፅኩ... አሆ
ተሰብሬም... አሆ... እየዳህኩ... አሆ
ጦር ሰብቄ... አሆ... መክቻለሁ... አሆ
ፅዋዬንም... አሆ... ቀምሻለሁ... አሆ
አዝማች (2 ጊዜ)

***

አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ
አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ
ሲያይሽ ዋለ...አሆ...ሲያይሽ ዋለ
የጀግኖቹ አሆ ነሽ እያለ አሆ
በየዱሩ አሆ እየማለ አሆ
የሁሉም ዘር...አሆ...ነሽ እያለ... አሆ...
ሴት ልጅሽ ነኝ...አሆ...ነሽ እያለ...አሆ...
ወንዱ ታጋይ...አሆ...ነሽ እያለ...አሆ...
ኢትዮጵያዊት...አሆ...ነሽ እያለ...አሆ...
የቆራጦች...አሆ...ነሽ እያለ...አሆ...
የአበው ቅርስ...አሆ...ነሽ እያለ...አሆ...

አዝማች (2 ጊዜ)
ጥቁር ዶቅማ...ኦሆ...ነሽ እያለ...ኦሆ...
የጣይቱ...ኦሆ...ነሽ እያለ...ኦሆ...
የብዙነሽ...ኦሆ...ነሽ እያለ...ኦሆ...
አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ
አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ።

***

እሰይ ስለቴ ሰመረ...እሰይ ስለቴ ሰመረ
(አዝማች 2 ጊዜ)
ተራርቆ ጠፍቶ የነበረ...እሰይ ስለቴ ሰመረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ
ታሪኬ ተፍቶ ታውሮ ነበረ...እሰይ ስለቴ ሰመረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ
የጋራ ሠራዊት ተፈጠረ...እሰይ ስለቴ ሰመረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ
ተበታትኖ ወድሞ የነበረ...እሰይ ስለቴ ሰመረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ
በእናት ባባት ታሪክ ተመከረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ...
እሰይ ስለቴ ሰመረ
ሀገር በታኝ ሁሉ ከሰረ..
እሰይ ስለቴ ሰመረ... እሰይ ስለቴ ሰመረ

ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባ፣ ጉሮ ወሸባዬ ወሸባ
እንዲያ እንዲያ ሲል ነው ግዳዬ ... (2 ጊዜ ...ይቀጥላል)
እሽክም ... እሽክም ... እሽክም!

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ወይም ሠራዊት አማካኝነት የብረት ትግል መጀመሩን ያበሰረው ሰላምን ጠልቶ ደም መፋሰስን ወዶ አይደለም፣ ኢሕአዲግ (ወያኔ) የሰላም በሩን በመዝጋቱ ነው። ከትጥቅ ትግሉ ባሻገር አእምሮአቸው በዘር መርዝ የተበከለውን የትግራይ የወያኔ ካድሬዎችንም ማስተማር ይኖርብናል። እስቲ እንደዚህም ብለን እንንገራቸው። «እናንተም የትግራይ ልጆች በሚዘገንን መንገድ ከቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለትውልድ ትውልድ በሚዘገንን መንገድ አትቆራረጡ። ገገር መደብ ለምትሉት በኃይለስላሴም ሆነ በደርግ ዘመን አብራችሁ ስልጣን ተካፍላችኋል። እንኳን እናንተና ኤርትራውያን ቁንጮና ወሳኝ ቦታ ይዘው በስልጣን ተንደላቀዋል። ይህንን ሀቅ እንኳን ወገኖቻችሁ ኢትዮጵያውያን ይቅሩና ዛሬ የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ውን የምታራምዱለት የምዕራቡ ዓለም እንኳ ጠንቅቆ ያውቀዋል። እኛ ትግሬ ቢገዛ ቅንጣት ታህል ምቀኝነትም ሆነ ቁክቻ አይሰማንም። አንድነትን የሚያመጣ፣ የሀገርን ልዑላዊነት የሚያስከብር፣ የጋራ ታሪካችንን የሚያይዝ፣ ህዝብን የሚያቀራርብ፣ ዘረኝነትንና ጉሰኝነትን የሚያጠፋ፣ እንደነማንዴላና ሞሐንደስ ጋንዲ የምዕራብ ገዥዎችን ተንኮል የተረዳ፣ ዘረኝነትንና ጉጠኝነትን የሚፋለም፣ ዴሞክራሲንና ዕድገትን የሚያመጣና ህዝብን ከህዝብ የሚያስታርቅ መሪ ነው የምንፈልገው። ቁስል የሚያክም ወጌሻ ወይም ሐኪም እንጂ ትንሿን ቁረት የበለጠ ስንጥቆ በማመርቀዝ ብሎም በቁስሉ ላይ እንጨት የሚሰድ መሪ አንፈልግም። ደርግ የወደቀው በእናንተ ጥይት ብቻ እንዳይመስላችሁ። ከቀይ ሽብር ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ በርካታ ታጋዮችንና ሊቃውንትን ገብሯል፤ የፖለቲካ ድርጅቶች ህዝቡ ለደርግ እንዳይገዛ ቀስቅሰዋል። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ነው ደርግ የተመነገለው። ሌላው ቢቀር ለደርግ አልዋጋም በማለት ያመፀውን ወታደርና እናንተን መርቶ ለስልጣን ያበቃችሁን የጐንደር፣ የጐጃምና የሸዋ አማራ አርሶ አደር ዛሬ ትምክህተኛ እያላችሁ ስትሰድቡት ታሪክ የማይፋረዳችሁ እንዳይመስላችሁ። ገና ስትገቡ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለእርቅ በሩን ብትከፍቱ ኖሮ ዛሬ አፍጦ የያዛችሁ አይለቄ የአንድነት ደጋፊ ምሁር ሁሉ ከእናንተ ጋር ይሰለፍ ነበር። ብዙዎቻችን ደርግ ሲወድቅ እፎይታ የመጣ መስሎን ልንደግፋችሁ አምርን ነበር። ያ የጠፋ (Misssed opportunity) ዕድል እንደገና የሚመጣ አይደለም። ዕድሉ ተገባዶ የመጨረሻ አፋፍ ላይ ቢደርስም እጅግ በጣም የመነመነ ተስፋ ሊኖር ይችላል። ይህንን ጭለማ ለማስወገድ በጀግንነት መራሩን ኮሶ መዋጥ አለባችሁ። የጐሳና የክልል ፖሊሲ አልሰራም፣ መዘዙም ለትውልድ የሚተላለፍና ጥላቻን የሚፈጥር ነው። ከዚህ የታሪክ አረንቋ በአስቸኳይ መውጣት ይቻላል የሚል ግምት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ለአሁኑ ባይኖረውም ለሰላምና ለአንድነት ብላችሁ ስህተታችሁን እንደመራር ኮሶ በመጠጣትና ማሻሪያ በማምጣት የጐሳንና የከፋፍለህ ግዛውን ፖሊሲ ቀይራችሁ ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ ከሰጣችሁት እናንተም የኢትዮጵያ ዜጋ ስለሆናችሁ ልትመረጡ ትችላላችሁ። የባሰ ከመረራችሁ ህዝብንም ጉድታችሁ እናንተም ትጐዳላችሁ። የሚቃወማችሁ አማራው በአማራነቱ ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሁሉ ተደራጅቷል። የማንኛውም ለውጥ አሳኪ የምሑር ክፍል (Intellegentsia) በአብዛኛው ቁጥሩ ከእናንተ ጋር አይደለም። የማርክስን አወደ ሀሳብ እንተወውና በሦስተኛው ዓለም ለውጥ የሚያመጣው ላባደሩ ወይም አርሶ አደሩ ሳይሆን ይኼ ለጥቀሙ ተገገር የሆነ ንዑስ ከበርቴ ነው። አሁንም ይህ የመጨረሻ በር ዕድሉን እንዳያጣ አሁን የያዛችሁትን መንገድ ቀልብሱ። የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ የኦሮሞውም፣ የትግሬውም፣ የአማራውም፣ የጉራጌውም...ወዘተ ታሪክ ነው። በምዕራቡ ዓለም የምትኖሩ ትግሬዎች የቱን ያህል በቀለምና በጐሳ የሚደረግ ቅስቀሳ ደምን እንደሚያፈላ እንደምትረዱት እንገነዘባለን። ጐሰኝነነት ስሜታዊነትን በማገገስ ትክክለኛ አመለካከትን (objectivity) ያጠፋል። ጥላችን «ትግሬ ለምን ገዛ» የሚል አይደለም። ለምን ህዝብን ለመከፋፈልና ሀገርን ለመበታተን መርዝ ይረጫል ነው። አሁንም ይህንን አስከፊ በሽታ ለመቀልበስ ጊዜ አለ። ጊዜ በመስጠት በማንአህሎኝነትና በውጥረት አናፍርም ካላችሁ የምትጐዱት የኢትዮጵያንና የሌላውን የጥቁር ህዝብ ነው። ሁኔታው መመለስ የማይችልበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት መፍትሔ መፈለግ ይኖርባችኋል።

– ያለው የኢትዮጵያ መንግስት የክልልን ፖሊሲ እንዲቀለብስና ለዚህም የትግራይን ምሁራንና ሕዝብ መጠቀሚያ እንዳያደርግ በተናጠልም ሆነ በጋራ መግለጫ ማውጣት፣

– ለኤርትራ ጥቅም ባለው መንግስት የሚዋቀረውን ፖሊስና መርህ መቃወም፣

– ተቃዋሚው ክፍል እናንተ በተንኮል እንደምትሉት «ትምክህተኛ አማራ» ብቻ እንዳልሆነና አፋጦ የያዛችሁ በሀገርም ውስጥ ሆነ በውጪ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለውና ተደማጭነት ያለው ከሁሉም የተደባለቀ ዜጋ መሆኑን መረዳት፣

– «ኤርትራውያን» እናንተን መጠቀሚያ በማድረግ፣ ካሁኑ የጐሳ መሰሪ መንግስት ጋር በማበርና በነፍሳችሁ በመጫወት የሚያደርጉትን አሻጥር ማጋለጥ፣

– ዘረኝነትን፣ ጐሰኝነትን አለም አቀፍ የከፋፍለህ

ግዛው ዘይቤን መቃወም፣

– ህዝብ እንዲቀራረብ ሌት ተቀን መትጋትና መስራት፣

– የጕሳ እልቂቶችንና የዓለም የዘር ፖሊሲዎችን ውድቀትና አውዳሚነትን መረዳት፣

– የመንግስትን የፕሮፓጋንዳ ባህርይ ማስተዋል፣

– የሁላችንም መኩሪያ የሆነችውን የጥቁሯ ኢትዮጵያን ሐገራዊ ልዑላዊነት መገንባትና ከአንድነት ኃይሎች በዴሞክራሲያዊ መርህ መሰረት መቆም፣

– የበቀልና (Vengeance) ለማይጠቅም ስልጣን ተባባሪ መሆንን በመቃወም አንድነትን የሚያራምድ ፖሊሲ መንደፍ፣

– ዓለም አቀፍ ዘረኝነትንና የጭቁን ህዝቦች ጠላት የሆነውን የምዕራቡ ዓለም የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ማውገዝና መቃወም፣

– ተቃዋሚዎች ሁሉ «የኃይለስላሴና የደርግ ርዝራዦች ናቸው» የሚለውን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሀቁን ፍርጥርጥ አድርጋችሁ ማወቅ፣

– ለግል ጥቅማቸውና ለስልጣናቸው የትግራይን ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚለዩትን የወያኔ መንግስትና አድርባይ ካድሬዎች ማውገዝ፣ መፋለምና ማጋለጥ።

– በሀገርም ሆነ በውጭ የኢትዮጵያውያንን ቁጣና ተቃውሞ ወያኔ እንደሚያቃልለው ሳይሆን መፍትሔ ካልተፈለገለት የበለጠ እልቂትንና መተራረድን ስለሚያስከትል አስቸኳይ የእርቅ የፖሊሲ ቅልበሳ፣ የሰላም፣ የአንድነት፣ የአዲስ መንግስት ምርጫ፣ የጋራ ጥቅምና የፌዴራል መንግስት (አስተዳደር) መድረክ መመስረት ይኖርባችኋል። አለበለዚያ ፈጣሪን፣ ታሪክንና ህዝብን ኮንነን እርስበርሳችን የመጠላላቱ ሁኔታ አድጐ በመተራረድ እንጠፋለን። ይኼ ካልተሰማችሁ ኃላፊነት ያለው ዜጋ አይደላችሁም። ለዚህም የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ቀዌሳን ግጥም በትንሹ የምናስታውሰውን ያህል ብንጠቅስላችሁ ደስ ይለናል፤ ግጥሙን ቃል በቃል ባናስታውሰውም በሕያው አንቂ ብዕሩ የፃፈው ይህንን ይመስላል።

«ይድረስ ወገን ከኛው ለኛ
ፅዋህን ተቀበለኛ
... ከምንጫረስ እንደ እኩይ
የነገው ትውልድ ለፍርድ –
ሳይመድበን ከዘር ድውይ
እባክህን ሳይጨልምብን
የዕውነት ራዕይ አብረን እንይ።»

ለአንዳችን አብርቶ እንኳ ለሌሎች ቢጨልም ይህም ነፃነትና ፍትህ አይደለም። የራሳችንን ጐሳ አቅርበን ሌሎችን ብናርቅና ብናገል ይኼ አንድነት አይደለም። በቂም በቀልና በቁክክር ሌሎችን በማነሳሳት የተወሰነ ብሔርን ማስጠላት፣ ፍቅርን መመስረት አይደለም። ለመንግሥት ስልጣን ተብሎ ሌሎችን በመለየት ወገንን ማስመረጥ ዴሞክራሲ አይደለም። ለስልጣን ተብሎ የህዝብን ስሜተኝነትን በመቀስቀስ ጐሳን ከጐሳ ማባላት፣ ህፃናትን እርስ በእርስ እንዲገዳደሉና እንዲማታ እንደማድረግ ያህል ወንጀል ነው። እዚህ ላይ ህዝብን ህፃናት ማድረጋችን ሳይሆን ያልጠረጠረ ህዝብ ማጫረስን ለማሳየት ነው። ከመካከላችን አንዱ እንኳ ቢያዝን ሁላችንም ማዘን አለብን። ሁላችንም እንድንደሰት ሁላችንም ፍትሕ አብረን መፈለግ ይኖርብናል። ህዝብን የምትቀላቀሉት የወያኔን ፖሊሲና አስተዳደር ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር አብራችሁ ስትታገሉ ነው። አማራው ወጣት ኃይለስላሴንም ሆነ ደርግ አልማረም። ምነው እናንተ ላይ ሲመጣ ታሪክ ቆመ። እናንተስ ኢትዮጵያውያን አይደላችሁም? ይኼ ፕሮፓጋንዳ ከመሰላችሁ ውርድ ከራሳችን ነውና አስቡበት» በማለት ማስተማርና መቀስቀስ ይኖርብናል። ሰሚ ካላገኘን?? «ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው» የሚለውን የአበውን ተረትና ምሳሌ ማስታወስ ይኖርብናል።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

በጊዜው ያሉ አደናቃፊ የወያኔ የመበታተን ታክቲኮች ምን ይመስላሉ።

<u>በእምነት አካባቢ የሚሸረብ አሻጥርና የመበታተን ስልት ውሎ አድሮ መጋለጡ አይቀርም።</u>

ባለፉት የላንዳፍታ እትሞች በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝንና ቀጥተኛ ወረራን በመቋቋም በኢትዮጵያ ታሪክ ይህ ነው የማይባል ሚና ተጫውቷል። የአደዋውና የማይጨው የተዋሕዶ ተቋም ስንክሳር የፍልሚያችን የሰማዕታቱ ገድል ነው። የተዋሕዶ እምነት ለዘመናት ከእስልምና ኃይማኖት ጋር ተቻችሎ በመኖር ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያውያን እስላሞች «እንኳን እኛና ግመሎቻችንም የገዳማትን እጣን ሽታ እየተከተሉ ውኃና ለምለም ስፍራን በተለምዶ ፈልገዋል። የጋራ ችግራችንን በጋራ ተወጥተናል፤ በንግድና በደቦ፣ በሀዘንና በተዝካር፣ በሠርግና በጦርነት አብረን ተሳትፈናል። ወያኔዎች ልዩነታችንን እያጐሉ ለመበታተን ቢሞክሩም አሻጥራቸው ግቡን አልመታም» ይላሉ።

እንደሚታወቀው ተጋዳላይ ጳውሎስ የኢትዮጵያን ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለማዳከም በፖለቲካና በክላሺንኮቭ በመመካት ታሪክ የማይረሳውን የመበታተን ተልዕኮ ፈፅመዋል። በምዕራቡም ዓለም በስደት ላይ የሚገኙ ጳጳሳት፣ ካህናትና ምዕመናን ይህን በመታገል ህዝባችንን በማሰባሰብ የተጫወቱት ሚናና ትግል እንደዚሁም ለኢትዮጵያ አንድነት የዋሉት ውለታ ታሪክ የሚረሳው አይደለም። ዛሬ በእነርሱና በምዕመናኑ ትግል የተነሳ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአንድነትን መፈክርና የትብብርን መርህ በተግባር በመተርጐም የተጠናከረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ናት። ይህም መደራጀት ያስደነገጠው የወያኔ የስለላ ድርጅት በአሜሪካ አንዳንድ ካህናትን በእጅ አዙር በመጠጋት ሕዝብን ለመለያየት የመሞከር ዓላማው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጋለጠ ዛሬ የተዋህዶ ምዕመናን በአሜሪካ፣ በካናዳና በካሬቢያን ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ተጠናክረው እግዚአብሔር ለሚወደው መፈቃቀር፣ አንድነት፣ ታሪክና ባህል በመደራጀት የጠላትን ቅስም ሰብረዋል። ተጋዳላይ ጳውሎስን በመደገፍ ቢነሱ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው ጠንቅቀው የተረዱት አፍራሾች በአንዳንድ ስፍራዎች ህዝብን በጐሳ፣ በከተማና በገጠር፣ በስደተኛና በተማሪ ወዘተ ለመከፋፈል በመሞከር «ብቸኛ» መዋቅር ያለው ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ቢሞክሩም ዛሬ በህዝብ ቁጣ አፍረውና ተነጥለው በበረሃ እንደሚያንፀባርቅ ነጭ ኩይሳ ፈጠው ፀሐይ እየሞቃቸው ነው። ከሰላዮች ጋር በማበር የሚያደርጉት ግፍና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሚቀልዱት ተግባራቸው ማንም አላወቀብንም ቢሉም የአደባባይ ምስጢር በመሆን ገሀድ እየወጣ ነው። በአንድ በኩል አባ ጳውሎስን የተቃወሙ በመምሰል በሌላ በኩል ደግሞ ጐሰኞችንና ዘረኞችን በማደራጀት «የእግዚአብሔር እምነት የቆመው ለሁሉም ነው» የሚለውን እውነተኛ አባባል በተራቀቀ ሰያፍ የፖለቲካ አቋም በመመንዘር ሌት ተቀን የሚሰሩ ከይሲዎች በአንዳንድ ስፍራዎች

ብቅ ብቅ ለማለት ሞክረው ነበር። «ከሁሉም ወገን አይደለንም» በማለት ለታሪክ በሚዘገንን መንገድ በአንዳንድ ስቴቶች ህዝብን በካራ ለማጋደል ሞክረው ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክና ሕዝብ ከዘረኞችና ከከፋፋይ ሰላዮች ጋር በማበር እንጨት ቆስቁሶ ኩፋዳቸውን ሞልቶ፣ ግብር ከፍሎ ያስተማራቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ አሹፈውበታል። እነዚህ ታሪክን አጉዳፊ ግለሰቦች ያልተረዱት ነገር ቢኖር ምንም ቢቀጠፍ የማይታወቅ ነገር አለመኖሩንና የአንድነት ኃይሉም ተንኮላቸውን በውል ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ነው። ለጥቂት ጊዜ ራቅ ያለ ቦታ በስልክ በመገናኘት ለማወናበድ ቢሞክሩም ከእነርሱ ጋር የሚኖረው ህዝብ ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። ሌላው ያልተረዱት ነገር ቢኖር ለእምዬ ኢትዮጵያና የሕዝቦች አንድነት እንኳን ጊዜና ገንዘብን ሕይወታቸውንም እስከሞት ለመሰዋት ዝግጁ የሆኑ ምዕመናንና አኩሪ ዜጐች በስደት ላይ እንዳሉ ነው። ሕይወታቸው የኢትዮጵያ ሕልውናና አንድነት የሆኑ በስደት ላይ የሚገኙ ክቡር የኢትዮጵያ ልጆች እነዚህን ግልገል የጐጠኛ መጠቀሚያዎች ከነታሪካቸው ለመጭው ትውልድ ተፅፎ እንዲቀመጥ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ጥፋተኛ ከጥፋቱ ተምሮ ይቅርታን እስካልጠየቀ ድረስ ያስፈለገውን የመናገር መብት ቢኖረውም እንደሕፃን ሊያሞበረብረን አይገባም። በእርግጥም እነዚህ ከቁጥር የማይገቡ ግለሰቦች ከወያኔ ባላነሰ መንገድ የማይሳካ ተልዕኮአቸውን ለማራመድ ቢፍጨረጨሩም ተቀባይነትና ታዋቂነት የላቸውም። ሁኔታውን ያስፈርኩት ለጠንካራ ጠላት የሚገባውን አስተያየት ለደካማ ጠላት ለመስጠት አይደለም፤ የወያኔን አልሞት ባይ ተጋዳይ ስልትና የተራቀቀ የመበታተን ውዥንብር ለአንባቢያን ለማሳየት እንጂ። የወያኔ የስለላ ድርጅት የሞት ሞቱን (Frantically) የቱን ያህል በምሁራዊ ተቋሞች (Academic Institutions)፣ በኃይማኖት፣ በሙያ ማኅበራት፣ በሲቪክ ማኅበረሰቦችና በፖለቲካ ድርጅቶች የቱን ያህል ሠርጐ ለመግባት ጥረት እንደሚያደርግ ለማሳየት እንጂ።

ሕዝብ እንዲለያይና በኢትዮጵያዊነቱ እንዲጠራጠር እውነት መሰል «የጭቁና ብሔረሰቦች(ጐሳዎች)» ድርሰት ማተምና ማሰራጨት፣ የከፋፋይ ልፋፍና ቅስቀሳ ማስፋፋት፣ ህዝብ በወያኔ የክልል አይዲዎሎጂ እንዲታጠብ እውነቱንም ውሸቱንም በመደባለቅ በኢትዮጵያ መሰሪ ፅሑፍ በምርምር ስም መዝራት፣ በቀልና ቂም እንዲሰፍን ብሎም አለመግባባትና በኢትዮጵያዊነት አለመተማመን እንዲነግስ መፈለግ።

ሙሴ ተገኘ የዛሬውን የአንድነት አቋም ከመያዛቸው በፊት ስቲግማ (STIGMA) ስለሚለው መጽሐፋቸው ወቅታዊነቱንና አንገብጋቢነቱን በመጠየቅ የአንድነት ኃይሎች ተቆጥተንና አዝነንም ነበር። የነባላይ ዘለቀን ፀረ–ነጭና ፀረ–ቅኝ አገዛዝ ኢትዮጵያዊነት በማደብዘዝ ይህ ፅሁፍ በዘመነኝነቱና በጊዜነቱ በወያኔ የክልል ማነቆ ውስጥ እንደሚያስገባ በመገንዘብ ተቆጭተን ነበር። ዛሬ እርሳቸውም ቢሆኑ ወቅታዊነቱን መለስ ብለው በማየት ከወገኖቻቸው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ለመታገል እንደቆረጡ አልጠራጠርም። ሌሎችም ጽሑፎች በወያኔ መሰሪ የስለላ ድርጅት ግፊት (ወይም ግፊት ባይባል የወያኔ መንግስት በፈጠረው ሁኔታ የተነሳ) ተደርሰዋል። ስለሰባት ቤት ጉራጌ፣ ስለወይጦ፣ ስለአገው፣ ስለኢትዮጵያውያን ሶማሌ፣ ስለሻንቅላ፣ ቤንሻንጉል፣ ጉምዝ፣ ሽናሻ... ወዘተ። ይህም ሲሆን ስለኤርትራ ብሔረሰቦች ለምሳሌ ቤኒአሚር፣ ወዘተ የተፃፈ ጽሁፍ እንኳ ቢኖር ሳንሱር ተደርጐበታል። ይህን ግፍ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተረድቶ በየደቂቃውና በየሴኮንዱ መፋለም አለበት። በምሑራዊ ምርምር ስም የተዋቀረውን የምዕራቡና የወያኔ ከፋፍለህ ግዛው የብሔረሰቦች መለያየትን ጠንክረን መዋጋት አለብን። የአሜሪካ ነጩ የገዥው መደብ English first እያለ በሀገሩ እንግሊዝኛ የማይናገሩትን ስደተኞችና ዜጐች በየአዋጁ ለመጉዳት በሚፋለምበት ወቅት ነገር ግን በሀገራችን እንዲራመድ በገንዘቡና በዕርዳታው የሚደግፈውን የብሔረሰቦች የልዩነት ክልተ–ስፍር (Double Standard) አጥብቀን መታገል ይኖርብናል። ጠለምትንና ወልቃይትን በወራሪ ሰፋሪነቱና በባህል የወያኔ ፖሊሲ የተበተበውን የክልል የናዚ የሽቦ ቀጋ (Barbed wire) ሐቁን በማስተማር መቆራረጥ ይኖርብናል። የነገረሱ ዱኪን፣ ደጃች ባልቻን፣ የነአባ ዳጨውንና ሌሎችንም ፀረ–ነጭና ዘረኛ ወራሪ ኃይል የተጋፈጠውን እውነተኛ ታሪክ በዩኒቨርስቲው፣ በየግጥም ጽሑፎቻችን፣ በየታሪክ ዕዛላችን በአደዋ እንደተደረገው ፍልሚያ በብዕራችን ትግል ሐቁንና ዕውነቱን ይዘን ማሸነፍ አለብን።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ባለፉት 30 ዓመታት የውድቀታችን መንስዔዎች ያልረባ ውይይት፣ በወገን መካከል የሚሰለቅ «የመስመር ልዩነት»፣ እንደማስቲካ የሚታኘክ የእኝኝ እገባ ሰጣና የእጅ አልሰጥም እንካሰላንቲያ ነበሩ። ከነገርና ከአተካራ ለቀቅ ያለ ነገር ግን በጋራ ጥቅም ላይ ጠበቅ ያለ ምግባር –መሰል(Business like) ውይይት ማድረግ አለብን። የቁስላችን አመርቃዥና የትግላችን መተተኛ አዚም የማይጨበጥ የውይይት ቲዎሪ ነው። ውይይት ሳይበዛ በመጠኑ ውጤታማና ስኬታማ ሥራ ላይ ካተኮረ መልካም ነው። በላባደርና ወዛደር ቃላት ጥንት እንደተፋለምነው ጉንጫችንን ማልፋት ቶረኝነትና የገደል ጩኸት ነው። ፈረንጅ እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው በውይይት ቢሆንም የእርሱ ውይይት ግን ምግባረ–መሰል ነው። እምዬ ምኒሊክ የአድዋውን ጦርነት ሲያስተባብር በቲዎሪ እንካሰላንቲያ አልነበረም። «አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ» እንዳይሆን የኛ ነገር። አሁንማ ወያኔም «በልቶናል»፣ አውቆናል። ወገንን ለመበታተን ሲፈልግ በደጋፊዎቹ የውይይትና የእንካሰላንቲያ መርዝ ይረጫል። እኛ ስንጣረብ እርሱ ምግባረ–መሰል ታክቲክና ስትራቴጂ ላይ በማተኮር ሀገራችንን ይበታትናል።

«ላባደርም» ሆነ «ወዛደርም» (wage laborer) አንድ እንደሆኑ አልገባንም። ያ ያለፈው የታሪክ ልክፍት ትምህርት እንዲሆነን ይገባል። በቃላት አንሰናጠቅ። የወያኔን ጐሰኝነትና የመበታተን ሸር እደግመዋለሁ የወያኔን ጐሰኝነትና የመበታተን ሸር በመቃወም የሀገር ነፃነትንና ሉዐላዊነትን ለማረጋገጥ የሚፋለመው ሁሉ ሀገር ወዳድ ነው። ግማሽ እርግዝና እንደሌለ ሁሉ ግማሽ ሀገር ወዳድነት የለም።

ሌላው ደግሞ ለነጭ የአፍሪቃ ፖሊሲ ሁሉ እጅ አንስጥ። የነጭ ፖሊሲ የስቃይና የሕማማት መንስዔ ነው። የጋኔል ስቃዥ ውጋት ነው። ወያኔን ብናሸንፍም ወይም ብናቸንፍም ነጮች የዘር መርዝን እንደገና መዝራታቸው አይቀርም። «ጋንዲ» የሚባለውን ባለጥሩ ታሪክ ፊልም ያየ ካለ ስለነጮች ብዙ ትምህርት መቅሰም ይችላል። በጋንዲ ትግል ጥንካሬ የተነሳ እንግሊዞች ለንደን ጋበዙት። አቡጀዲ አጣፍቶ ያ ጠውላጋ የህንድ ህዝቦች ብርሃንና አለኝታ ከእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጋር በአንድ ጠረጴዛ በተቀመጠበት ወቅት የሥነ ምግባሩ ርቀትና ምሳሌያዊነት እንደጦር ወጋቸው። የእንግሊዝም ባለሥልጣናት የዚህን ክቡር ዜጋ ቅስም ለመስበር (In-

timidate ለማድረግ) እንዲህ አለ። «ሕንድ እኮ የአንድ ብሔር ብቻ አይደለችም። የሂንዱ ኢንዲያ አለች፣ የሞስሊም ኢንድያ አለች፣ የሲክ ኢንዲያ አለች ... ወዘተ።» ጋንዲም አለ። «ኢንድያ በተናጠል ሳይሆን የሁሉም ኢንዲያ ናት፣ እነዚህን ሁሉ በርካታ ባህል የያዘች ናት። እንግሊዝም እኮ የአይሪሽ የዌሊሽና የስኮቲሽ ሀገር ናት» ሲል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደነገጡ። ከኮሎኒያሊስት አውሮጳውያን ፍትህን መጠበቅ ማለት የበሬ ቆለጥ ይውድቅልኛል ብላ እንደተንጋለለችው ቀበሮ ዓይነት መሆን ነውና እንጠንቀቅ።

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

ለዛሬው የኢትዮጵያ መከፋፈልና ለሚታየው የአፍሪቃ ኋላቀርነት ትልቁን ሚና የተጫወቱት ነጮች ናቸው። በተለይም እንግሊዞች የጐሳና የዘር አፅም በመቆፈር በሱዳን፣ በኢትዮጵያ፣ በናይጄሪያ፣ በኬንያ ህዝብን ለመግዛት እንዲመቻቸው የወጠኑት የከፋፍለህ ግዛው ታሪክ ነው አፍሪቃን ለድንቁርናና ለድኅነት የዳረጋት። ሌላው ቀርቶ የህዝብ ቁጥር በሦስተኛው ዓለም ሲበዛ እጅግ ይደነግጣሉ። በዚህ መሰረት በ1974 በዴሞክራሲ እገዘታለሁ የሚሉት ሄነሪ ኪሲንጀር እንኳ በታወቀው ቁ. 200 ዶብዳቤያቸው በብሔራዊ ደኅንነት ጥናት የሚያስገርም ነገር ፅፈው ነበር [Henry Kissinger's National Security Study Memorandum 200]። በዚህ ጽሑፋቸው የአንዳንድ ድሃ ሀገሮች ቁጥር መጨመር የተፈጥሮ ሀብትን ስለሚያሟሽሽ ወይም ስለሚጨርስ ለአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት አስጊ ነው ብለው ነበር። ከተጠቀሱት ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ናይጄሪያ ይገኙበታል። በኪሲንጀር አባባል እነዚህ ሀገሮች ጥሬ ሀብታቸውን ለህልቁ መሳፍርት ህዝባቸው ስለሚጠቀሙ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግ ይችላል ባይ ናቸው። የእርሳቸው አስተያየት ይህ ችግር በወቅቱ ባይገለፅም እነዚህ ሀገሮች ካላቸው ያልተበላ የተፈጥሮ ሀብት ጋር ሲመረመሩ ቀውሱ ወደፊት እንደሚመጣ ወይም እንደሚከሰት የሚገልፅ ጭምርም ነው። እነዚህም የተፈጥሮ ሀብቶች ወርቅን፣ ነዳጅንና የመሳሰሉትን ማዕድናት ያጠቃልላሉ። በመቀጠልም ኪሲንጀር የህዝብ ቁጥር እንዳይጨምር መከላከል ወይም ማዘግየት የጊዜው አንገብጋቢ መፍትሔ መሆኑንም ጠቁመዋል። ቁጥር 200 ደብዳቤያቸው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ መንገድ በስራ ላይ ውሏል። ይህም ሥራ ላይ የዋለው መንግስታዊ ያልሆኑ ሰብዓዊ ድርጅቶች (NGOs) እና በዓለም አቀፍ መከሊት ድርጅቶች ነው። በዚህም መሰረት ለአጭር ጊዜ ዕርዳታና ብድር የህዝብ ቅነሳ ሁኔታ (Population control)፣ የምግብ አደላደልና ሌሎችም መዋቅራዊ መስተካከሎች አብረው ተነድፈዋል። እንደ አንዳንድ አፍሪቃዊ ብሔራዊ ፀሐፊዎች አባባል ከሆነ ቁጥር 200 ደብዳቤን ከብሪቲሽ የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ጋር በማጣመርና «የሶቪየትን ኮሚኒዝም ለመምታት» በሚል ስም መሳሪያ በመሸጥና ጦርነት በመቀስቀስ ምዕራባውያን ሕዝባችንን ጐድተዋል። መሪዎችንም በረቀቀ መንገድ ኮትኩተው በማሳደግና በመረዳት በርካታ የአፍሪቃ ሀገሮችን ስልጣን እንዲይዙ አብቅተዋል። ይህንን ለማንሳት ያስገደደኝ የታሪክና የሕሊና ፍርድ አለ። በተለይም እኛ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን፣ በአሜሪካ፣ በካናዳና በሌሎችም የምዕራቡ ዓለም በስደት ላይ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ያለውን ዴሞክራሲና ስልጣኔ በማየት በነጩ አዋቂነት በፈንጢጣችንና በአፋችን እንዳንስቅ ለማስጠንቀቅ ነው። ኢትዮጵያን ከአስካሪ ግልገል ዘረኞችና የጐሳ ናዚዎች ጋር በመመሳጠር ያፈራረሱት ምዕራባዊያን ናቸው። ስለሰው ልጅ መብት መታፈን የአዞ እምባ እያኮለሉ በሰብዓዊ ድርጅቶቻቸውና በሃይማኖት ተቋሞቻቸው በህምሳ ምላስ በመለፍለፍ እምዬ ኢትዮጵያን የፈረካከሱ እነርሱ ናቸው። ሌላው ቀርቶ አንባቢን እንዳይገርም እንጂ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል (Amnesty International) እንኳ የምዕራቡ ዓለም መጠቀሚያ በመሆን በበርካታ የድሀ ሀገሮች ሕልውናንና ሀገራዊ ልዑላዊነትን አስመትቷል። ይኸ በጭራሽ ሊታመን የማይችል ነገር ነው የሚል አይጠፋም። በአንድ በኩል ለሰብዓዊነት መከበር እየታገለ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል በደርግ ዘመን የተገንጣዮች መጠቀሚያ አልነበረምን? ድልድይ አፍራሽንና ህንፃ አፈንጂን በአጠቃላይ የሰሜን ሽብር ፈጣሪዎችን በወቅቱ ደባቸውን በይፋና በእውነተኝነት አጋልጧልን?... ፍርዱን ለታሪክና ለመጭው ትውልድ እንተው።

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

የሀገራችን ያሁኑ የወያኔ ፍልስፍና ፈላስፋው ቪኮ(VICO) ካስቀመጠው የታሪክ ትዝብት ጋር ይገናዘባል። ህዝብን የሚከፋፍሉ፣ ሀገርን የሚለያዩና ጐረቤትን ከጐረቤት የሚያጣሉ አስተሳሰባቸው ሁሉ «በአውሬአዊ ማስላሰል»(Barbarism of reflection) የተበከለ ነው የሚለው የቪኮ አስተያየት ለዘመነኛ የጐሳ ካድሬዎች ባሕርይ ተደግሞ መነገር ያለበት ነው። ይኼ አውሬአዊ ማሰላሰላቸው በተፈጥሮ ከሚታየው የዱር አውሬዎች የኑሮ ትግል (CREATIVE BARBARISM) ሁሉ የከፋ መሆኑንም አንዳንዴ የሰው ልጆች በታሪክ ለጥቅማቸውና ለግለኛ ዓላማቸው እንዴት በእውነት ላይ እንደሚጫወቱ ፈላስፋው በማይፋቀው የሰው ልጆች የታሪክ ብራና ከኃይማኖት ጋር እያገናዘበ ፍርዱን ሰጥቶ አልፏል። ይህንን በመናገሩ ኢጣሊያዊው ጊያማባቲስታ ቪኮ በርግጥም ከጊዜው በፊት በ1668 ዓ.ም. ተወልዶ የሰውን ክፋት በብዕሩና በአዲሱ ሳይንስ መፃፉ ድባቅ የመታ ሊቅ ነው። የተዋበው ጽሑፉ ምዕራፍ ከምዕራፍ እየከወነ ድሮም እንደገደል ማሚቶ ከሲሲሊያ፣ ፓምፔና ሮም ተራሮች እያስተጋባ ፋሽሽቶችንም አሳፍሯል፣ የዛሬ አስካሪዎችም የታሪክን ገጾች ቢያገላብጡ ጩኸቱንና ኃይሉን ሊቋቋሙ እንደማይችሉ ነው የሚታየኝ። እስቲ ይኼም መፋለሰፍ ነው አትበሉኝ እንጂ ከምዕራፎቹ ውስጥ አንዱን አንቀፅ ለመተርጐም ልሞክር። «እነዚህ እንደ ዱር አውሬዎችም ሁሉ ለራስ ሥጋ ብቻ በማሰብ ለከርሳቸውና ለግለኝነታቸው በመቆም በራስ እብሪተኝነትም ስለተለከፉ በረባ ባልረባውም የተናካሽ ቁጡነታቸውን ወይም ሆደ ባሻነታቸውን ያሳያሉ። እንዲሁም በግብራቸውና በድግሳቸው ወቅት አንድ ላይ ይጣበቃሉ፤ እንደ ዱር አውሬዎች በውስጠኝነት ወይም በጠለቀ ሕቡዐዊነት(ሕብዕነት)ና በተፈጥሮ መንፈስ አብረው ያብራሉ። ያም ሆኖ ከመካከላቸው ሁለቱ ቢሆኑም እርስ በእርሳቸው በተንኮላቸው ስለሚተዋወቁ በተቃራኒነት ይጠባበቃሉ፤ ይህም የሚሆነው እያንዳንዳቸው የራሳቸው የደስታ ፈለግና ከርሳዊ መንሰፍሰፋቸው ስለሚለበልባቸው ነው። በዚህም ምክንያት የተፈጥሮ አምላክ ሕጉን በመደንገግ ያስተምረናል። እንዲህም ሲል። አክራሪ ወይም ጠባብ ቡድኖችና የእርስ በእርስ አስከፊ ጦርነቶች ቢቀሰቅሱ እንኳ እነዚሁ የእሳት ጫሪ ተናካሾች ከተሞቻቸውን በዱር፣ ዱሮቻቸውንም በወሽካች ወይም እኩይ ነፍሶች ይተካሉ። በዚህም መንገድ ከረዥም ምዕት ዓመታት አውሬነት በኋላ ዝገት ይህንን በክፋት የተጠነሰሰ

የተፈጥሮ መሰረትነት እንደ እሳት ይበላዋል፤ ይኼ አእምሮን ያጨቀየ የአውሬነት ትግል በልጦና ልቆ ኢ.ሰብአዊነቱን ያስመሰከረው አስተሳሰብ ራሱን ያጠፋል። ሆኖም መታወቅ ያለበት ቁምነገር የአውሬአዊ ማሰላሰል ከአውሬነት ትግል በለዘበ አንደበቱ የቁቃ እሾህ ነው። በሚመስል ቋንቋውና ማዘናጋቱ የወገኑንና የአብሮአደጉን ማጅራት ያርዳል፤ ጊዜ ጠብቆ አደጋ ላይ ይጥላል» [Karl Lawith: Meaning In History, PHOENIX PRESS, 1949, Page 133-34]። በእርግጥም በዚህ ታሪካዊ መጣጥፍ ልቤ ረክቷል። ይህ ጽሁፍ የወያኔ ካድሬዎችን ጠባይ በግልጥ ያሳያል። ሕዝብ እየነቃ ሲሄድ ጐሰኝነትና ዘረኝነትን በመተው የወያኔ አስተሳሰብ በዝገት ይበላል። በዓለም አቀፍ ደረጃ እንኳ ሲታይ በካፒታሊዝም ዕድገት የተነሳ ሀገራዊ ባህልና ንግድ እንኳ ድንበርን በመደርመስ ህዝብን እያቀራረበ ነው። ዛሬ እኛን በእጅ አዙር እያፈራረሱ ያሉት ጀርመኖች፣ እንግልጠሮችና ፈረንሳዮች በአንድ ገንዘብ ለመገልገል የንግድና የባህል መተቃቀፋቸውን እያዳበሩት ነው። ማስተር ቺት የሚባለው አውሮፓን በአንድ የጋራ ብር የሚያሳትፈው የኢኮኖሚ ውል በጥቂት ዓመታት ውስጥ ስራ ላይ ይውላል። እነርሱ እያበሩ እኛን ሲከፋፍሉ እጅግ ይገርማል።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

ስለጐሰኝነት በርካታ ምሑራን ምርምሮችንና ጥናቶችን አድርገዋል። ብዙም ተፅፎበታል። የእኛ መሪዎች ለምን እንደማይገባቸው አይረዳኝም። አንዳንዴ እንደሚረዳኝ ካለው የኢትዮጵያ «የግፉዐን» የውሸት የፍርሃት ስነልቦና (The Psychology of false Ethiophobic victimization) እና የጫካ የተከለለ አመለካከት የተነሳ የወያኔ መሪዎች የሕዝቦችን መቀራረብ አይፈልጉም። አሁንም የሚኖሩት በጫካ የሽፍትነትና የጥላቻ ዓለም ውስጥ ነው። ለዚህም ነው የአፍሪቃ ታጋይ ወንድማችን አህመድ ሴኩ ቱሬ በ1979 ዓ.ም. «ጐሰኝነት (ነገድነት) ከኢምፔሪያሊዝም ሁሉ የከፋ ወንጀለኛ ነው» ያሉት። [Tribalism is more criminal than imperialism] በቅርቡም አቶ ይልማ ቡልቡላ በሶቪየት ሕብረት የደርግ አምባሳደር የነበሩት ስለዘረኝነት የሰጡት አስተያየት መሬት ጠብ አይልም። በእርግጥም የእርሳቸው ከነበረው መንግስት በአመለካከት ብለያይም ንግግራቸው ሐቅን አይሸፍንም። በኦሮሞ ዘር ማንዘራቸው ሐቁን ሳይስቱ እውነቱን ማፍረጣቸው ይበልጡን ሰሚ ጆሮ ይለግሳቸዋል ብዬ አምናለሁ። በሲያትል ከተማ በጁን 5፣ 1997 በአንድ ኮንፈረንስ ላይ ስለኢትዮጵያ ታሪካዊነትና ሕዝቡም በአንድ ብሔራዊ ቋንቋ ልዩነቱን አቻችሎ በመከባበር መኖሩን ገልፀዋል። የጐሰኝነት የአውሬነት ባህርይንም በመግለፅ [The ethnic identity is beastial] ፀረ–ሰብዓዊነቱንና ጠባብነቱን አስረድተዋል፤ እንዲህም ሲሉ «ጐሰኝነት ግለሰብን እንደ ፀረ–ሰብ፣ ጠባብና ከለልተኛ እንስሳ ያየዋል። የጐሳ ሰው እንደማንኛም ዜጋ በሕብረተሰባዊ ምግባሩና እንደሰብዓዊ ዕውቀቱ ከመታየቱና ከመፈተኑ አልፎ እንደቱትሲ፣ እንደ ኪኩዩ፣ እንደ ጉራጌ ...ወዘተ... በጠባብነት ይተመናል። ዘር ማንዘሩ፣ ክልሉ፣ ቋንቋውና ኃይማኖቱ ከሌላው ጋር እንደሚቃረኑ ተደርጐ እንዲያምን ይነገረዋል። ስለሆነም ለጥቂት (ለማይበቃ) የሀገሪቷ ሀብት ጥላቻና ፉክክር ይጀመራል። የዘር(የጐሳ) ባህርይ የግለሰቦችን ታማኝነትና ምርጫ ይወስናል፤ እነዚህም ምርጫዎች በጐሳ ላይ ያተኩራሉ። እስከእለተ ሞቱ ይህን ጥላቻና ዘረኝነት ነው ለቅኝ ገዥዎች የከፋፍለህ ግዛው መርህ የውሸት መነሻ በመስጠት በሕዝቦች ላይ መከፋፈልና መጠራጠር እንዲነግስ ያደረገው።»

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ዲፕሎማሲና የሰላም ድርድር በሩ ከተዘጋ ቆይቷል። ግዙፉ የምዕራቡና የወያኔ ፕሮፓጋንዳ የስደት ፖለቲካ (Exile Politics) እያለ ስላሾፈ የኢትዮጵያ ቆራጥ ልጆች ፍልሚያ አልቆመም። ይህንንም በሚመለከት የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት መመስረት ወያኔን በማስደንገጡ በቅርቡ አንድ ቡድን በኢትዮጵያ ኤምባሲ አስተባባሪነት በአሜሪካ ገለፃ ለማድረግ ሞክሮ በየቦታው በእውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ተቃውሞ ድባቅ ተመትቷል። አትላንታ ባደረገው ስብሰባ የዚህን የላንዳፍታ ጋዜጠኛ ካሜራ የወያኔ ወገኖች በኢትዮጵያ እንደለመዱት ለመንጠቅ ሲሞክሩ የአሜሪካ ፖሊሶች ሳይቀሩ ይኼ አሜሪካ ነው፤ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ ነፃነት አለ» በማለት መብትን እንዳረጋገጡ ታዛቢዎች ዘግበዋል።

አሁን ጊዜው የአመለካከት ጠብ አይደለም። ሁሉም መደጋገፍ አለበት። ብዙ ሊቃውንትንና ወጣቶችን ለእኩልነት የገበረው ኢሕአፓም ተጠናክሮ ደስ የሚያሰኝ ስብሰባ በሎስአንጀለስ አድርጓል። በጓዶቹ መስዋዕትነት ላይ ተክዞ እንደገና አርማውን በማንሳት በሐቀኝነት ኢሕአፓ በመቁረጥ ኢትዮጵያን ከጐሳ ጭለማና ከመበታተን ለማዳን በመሰለፉ የአንድነት ወገን ሁሉ ሲደሰት የበታኝ ኃይሎች ክፉኛ አዝነዋል። እንደ አገር ወዳድና የኢትዮጵያን ነፃነትና ልዐላዊነት አፍቃሪ ግለሰቦች አባባል አዲስ ድርጅትን ከመመስረት የትግል ተመክሮ ያለውን ኢሕአፓን ማጠናከርና ከጐኑም መሰለፍ አስፈላጊ እንደሆነ አምነውበታል። እንደስብሰባው መንፈስ ከሆነ የኢሕአፓ ዓቢይ ትንሣዔና ዕርገት የሚያጠራጥር አይደለም። ወያኔና ኢሕአፓ እሳትና ጭድ እንደሆኑ የተረዳው የመለስ ዜናዊ መንግሥት «የለውጥ ሐዋሪያትን» ወደ አሜሪካ የላከው ትግሉ ስላስደነገጠው ነው። ኢሕአፓን ጠርተን ሌሎችን ባንጠራ ታሪክ ይወቅሰናል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጥቂቶች አደራ በዮዎች በስተቀር ሁሉም ኢትዮጵያዊ እጅ ለእጅ በመያያዝ እየተቀራረበና እየመከረ ነው። በሁሉም አገር ወዳድ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሚዲያ ተከራካሪ አውታሮችና ታጋዮች ብንደሰትም አልፎ አልፎ የሚታዩ እጅግ በጣም ጥቂት ሆዳሞችና የድንጋይ ዳቦ ዘመነኞች አሉ። ባይገርምህ ወያኔ በአትላንታ ስብሰባ ሲያደርግ አብረው በደጋፊነት የተሰበሰቡ ሦስት አማሮች ብቻ ነበሩ። ኦሮሞው እስከነአካቴው አልመጣም። ብዙውን ተሳታፊ በቁጥር ከ30 የማይበልጡትን ያገኙት ከትግሬውና ከኤርትራውያን ነበር።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

እስትራቴጂና ታክቲክ የድሉ ግማሽ መንገድ አድራሾች ናቸው። የቀሩት ፈጠራነት (creativity) በራስ መተማመንና (Self-confidence) ሞራላዊ ጥንካሬነት ናቸው። እነዚህ ከተሟሉ ኢትዮጵያን በነፃነት፣ በእኩልነትና በአንድነት መልሰን እንገነባታለን!

በታሪክ እንደታየው አንድ ቡድን ሥልጣን ላይ በጉልበት ወይም በኃይል ሲወጣ የራሱን ታሪክ በራሱ መልክ ለመፃፍ ይፍጨረጨራል። በናዚ ጀርመኒ የሒትለር «የአራያን ዘር ንፅሕናና እንከነቢስነት፣ ብሎም የአይሁዳውያን የበታችነት» ይህንን የሚያመለክት ነበር። የውሸት ታሪክም እንደሰሯት ትሰራለች። ለጥቂት ዓመታትም ቢሆን ምልዐተ ሕዝቡን ታወናብዳለች። ታሪክ ወደተረትነትና ወደ ቅዠት የጊዜን እውነተኛ ትዕይንት ጥላ ታብዳለች። ወያኔ «የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው» ሲል ይህንኑ ቅጥፈት ወይም ቅዠት ማደለቡ

ነው። እንደዚህ ዓይነቱን የታሪክ ሰለባ በሚመለከት ታሪከኛው ጄ.ራይነር (J. Renier) እንደዚህ ይላሉ። «ታሪኩም የመጨረሻ መልኩን ሲቀይር በድግምት መልክ ራሱን ይገልፃል። ይህም ተረት ተጨምሮበት ወይም ተበርዞበት ከግምት ጋር ይስተናገዳል። በዚህም ሁኔታ ተረት ፀሐፊው ራሱን የሚቃረኑ የታሪክ ማስገንዘቢያዎችን ከፈለገ ለመመርመር ይጋበዛል። የእርሱን ታሪክ ለመፃፍ ያነሳሳውን ነገር ሁሉ ለመዘርዘር ይሞክራል። በየአንቀፆቹ የራሱን በአእምሮው የተቀረፀ አስተሳሰብና አመለካከት፣ ስራው ላይ ያለውን ተሳትፎና በንድፈ ሀሳብ ወይም በቲዎሪ አሳምሮ የሚመክተውን የራሱን የግል አስተሳሰብ እንደ ክቡር አውደ ሀሳብ በማድረግ ያቀነቅናል።» ግን ሌላው ታሪከኛ ሀልፌን (HALPHEN) እንዳሉት «የታሪክ አስቸኳይ ስራ የጥንቱን (የድሮውን) ሐቅ ወይም እውነት ከጥፋት ማዳን ነው።» ["The most immediate purpose of history is to save the facts of the past from oblivion"] ለዚሁም ነው ነጩ መጥፎም ሆነ ጥሩ ታሪኩን በመከወን ለልጆቹ ለማስተላለፍ የሚመክረው። ይህ የጋራ ትውስታ (collective memory) የአንድ ሀገር ህዝብ ትልቅ በረከት ነው። በዓለም ላይ የጋራ ትውስታን የሚያጠፉ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች (ለምሳሌ እሳተጐመራ፣ የውኃ ጐርፍ፣ የኑክሊየር ጦርነቶች፣ የዘር ማፅዳት ዘመቻዎች ወዘተ...) ናቸው። እነዚህም የህዝብ ጠር ናቸው። ለዚህም ነው የወያኔ መንግስት ይህንን የጋራ ትውስታ ታሪክ ለማጥፋት በመታገሉ ነው ብዙዎቻችን ኢትዮጵያዊነቱን የተጠራጠርነው። ሌላው ፀሐፊም ፓል ቫሌሪ በውሸት ታሪክ ላይ በመናደድ ሁሉንም ታሪክ በብሶት ለማውገዝ ይቃጣዋል። ስለተዛባ ታሪክ እንደዚህ ይላል፦ «ታሪኩ በአንጐል ቅመም የጣፈጠ አደገኛ ቁሌት ነው። ጠባዮቹና ባህርያቱ የታወቁ ናቸው። ሕልም ወይም ቅዠትን ይፈጥራል፣ ሀገርን ወይም ህዝብን ያሰክራል፣ በውሸት የጋራ ትውስታ ይጫናቸዋል፣ ስሜታቸውን ያጋንናል፣ አሮጌ ቁስላቸው እንዲያመረቅዝና የበለጠ ቆስሎ እንዲያዥ ያደርጋል፣ ሕዝብ እረፍት ወይም በዓል ላይ ሲሆን ፀጥታ በመንሳት ያሰቃያቸዋል ወይም ያብጣቸዋል፤ እንዲሁም በራስ እብጠት የግብዝነት ልክፍትና (megalomania) በጭቆና ቅዠት ይበክላቸዋል። መራራ፣ ችኮ፣ አስቸጋሪና ዋልጌም ያደርጋቸዋል።» በእኔእምነት ሕዝብ ታሪክን ቢሰራም ጮሌ መንግስትና ቡድን ታሪክ ይቀለብሳል። ግን ይኼ ሁሉ ጊዜያዊ ነው። አይሁዶች ታሪካቸውን እንደገና ፈር ያሳያዙት ከ1500 ዓመት ስደት፣ እሥራትና እልቂት በኋላ ነው። ለታሪክ ትውስታ መጥፋት ትልቁ ምክንያት የትውልድ የእርከን ሰንሰለትና የባህል ድልድይ ሲሰበር ነው[Breakdown of cultural continuity]። ይኼ የሚሆነው ወጣቱ በመጥፎ ትምህርት፣ በመጥፎ ባህል፣ ባባዕድ እምነት ሲላሽቅ ነው። ስለዚህም ነው የጴንጤ ቆስጤ እምነት፣ የምዕራቡ ቅራቅንቦ፣ ፋሽንና ዘይቤ ወጣቱን በመመረዝ የእርከኑን ሰንሰለት ለትውልድ እንዳይተላለፍ የሚበጣጥሱት። ግዴለሽ ዜጋና ወጣት የሀገር ሸክም ብቻ ሳይሆን በሽታም ነው። በታሪክ እንደታየው ወጣቱ አደራ ተቀባይና ታሪኩን አክባሪ ነው። ወጣቱ ህዝባችን ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ጥረት የአባትንና የእናትን አደራ ሳይበላ ለሰላም፣ ለአንድነትና ለሀገራዊ ልዑላዊነት መታገል ይኖርበታል።

እነሆ ለወጣቱ ትንሽ ግጥም፦

## እንዲያ በል ወጣቱ
## (ኧረ ወጣቱ ተቀስቀስ!)

ሊከሰት መተቱ
ዛሬም እንደፊቱ
ማን በነገራቸው –
ቁርጡን ቀን ማየቱ
ለእኩልነት መሞት፣ ለሐቅ መሰዋቱ፣
«አሉ በርከክ በርከክ፣ አውሬ መስያቸው
ከሰው መፈጠሬን፣ ማን በነገራቸው።»
ነኝ አሁንም ወጣቱ፥ ኢትዮጵያ ስትጠፋ ከመሰረቱ
ሰማዕታቱ የሚንገላቱ፥ በከርሰ መቃብር የሚያቃስቱ
ለፍትሕ ለአንድነት የሞቱ።
ኢትዮጵያ ተቆርጣ ሲጠፋ ስምዋ
የጓዶቼ ድምፅ የሚጠራኝ ... የታሪካቸው መረዋ
ቢቀጠቀጥ አጥንቴ ... ሕይወቴ እንኳ ቢሰዋ
አደራ ያልሸሸኝ ... የማልኖር ለዚህ ግሳንግስ ገዋ፣
ለኑሮ ሁሉ ባደማ
የሕዝቤን ጣር ... ሁልጊዜ የምሰማ
የመቃብር ጓዶቼን የማልረሳ ... ለትግሉ የማላቅማማ
ሲሰድቡኝ የማይታክተኝ ... በተርባቸው ሲገፉኝ
ረሻኙ ሌላ ሆኖ ... በጣጣው ሲያሳምሙኝ፣
ለፍትሕ እንዳልታገልኩ ... ቅምቡጥ ሕይወቴን
ሁለንተና ሰውነቴን
ለሐቅ እንዳልሰጠሁኝ
ቢሻው እንኳ ባንቀላፉ፥
አሁንም እኔ ወጣቱ ነኝ
የትውልድ ታዳጊ ተስፋ፥ ያባት አደራን ያልሸጥኩኝ።
የማላፍርበት ታሪክ ያለኝ ... ዕዳዬን የከፈልኩ
ለገባሩ ለድሀው ... ላስተማረኝ ገበሬ የቆምኩ
እየወደቅሁ እየተነሳሁ
የማይታክተኝ አበስ ገበርኩ
ኑሮዬን ሁሉ ሰውቼ ... ላይጥመኝ የተሰደድኩ፣
ደረቅ ችኮ እምነቴ ... ለፍትህ የተሰከልኩ
የምታገል ለህዝቤ ... ለሰሪው ባለታሪኩ
አክራሪዎችን የታገልኩ ... ከፋሽሽቶች የተጋፈጥኩ
የዳልጋ አንበሳ ትውልድ ... ከዘረኞች ያልወገንኩ
የሰማዕታት ዶቃ ... ስንቱን ግፍ የቀመስኩ
አዎ ነኝ ወጣቱ ትውልድ ... እንደየሱስ የተቸነከርኩ።
እንደ ጎለጎታው ሰማዕት ... ተስፋዬ የማይጨልም
ለልጅ ልጅ የማስተምር ... የለኮስኩት የማይከስም
ለትውልድ የሚደውል ... ዘመን ከዘመን የሚተም፤
ወጣቱ ነኝ አሁንም ... ለእናት ኢትዮጵያ የምቆም
ጠላቶቿን የምፋለም
ለኤክስቶርሽንስት የማልሰግድ፥ ለጥላቻ የማልፈርም።
ያማፅያን አጋዥ ነኝ ... ያገራችን የፍትህ ኮምፓስ
እጅ የማልሰጥ ለወያኔ ... ሲያሳንሱኝ የማላንስ
ራሴን የምመረምር ... በሕዝብ እምባ የምርስ።
ካለፈው ሁሉ የምማር ... ለምቾት የማልነግድ
አዎ ነኝኮ ወጣቱ .. በጓዶቼ እሳት የምነድ፣
በፍቅራቸው የምስተናገድ
የእምቢተኛ ትውልድ ሞገድ።

ቸር ይግጠመን!
ገብርዬ ከአትላንታ/ጆርጂያ

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



ላንዳፍታዎች፣

በስደት ያለውን ወገናችንን በአገሩ ቋንቋ ለማስተማርና ለማወያየት የከፈታችሁት መድረክ ቀላል አስተዋጽኦ እንዳልሆነ ስነግራችሁ ደስ ይለኛል። በተለይም በወርቃየሁና በገብርዬ መካከል በሚካሄዱት የደብዳቤ ልውውጦች የሚተላለፉት መልዕክቶችን ስከታተልና ስማርበት እንደነበረ እወቁልኝ። ዛሬ እንድፅፍ ያነሳሳኝ በእነዚህ በሁለቱ ሰዎች፣ አንዴ በአቶ ጌታቸው በጋሻው ከዚያም በኋላ በዶ/ር ጌታቸው መታፈሪያ የቀረቡት የብዙኃን ድርጅቶች አመሰራረት አስፈላጊነትና ተግባራቸውን እንዲሁም ታሪካዊ ሂደታቸውን የሚገልፁ ጽሁፎች ጠለቅ ያለ ቁምነገር ያዘሉና በተለይም አሁን ከገባንበት ማጥ መውጫ መንገድ የሚሰጡን መሆኑን እየታየኝ መጥቷል። በየቦታው ሊቋቋሙ ይገባል የሚባሉት እነዚህ የሲቪክስ ድርጅቶች ህዝቦችን ከፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ባሻገር የዴሞክራሲ ስርዓትን በመከተል ተስማሚ ያልሆኑ የመንግስት ተግባራትን የሚቃወሙበትና የሚገቱበት የነዚህ ዓይነት ማህበራት(ድርጅቶች) መፈጠር በጣም አስፈላጊ መሆኑን አሳምነውኛል። በወያኔ ተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ለሚደረገው የፖለቲካ ስልጣን ሽኩቻ መሣሪያ ከሆኑ ግን «ከድጡ ወደ ማጡ» ይሆናል።

ወደ እነገብርዬ ልመለስና፤ የቴዎድሮሱ ገብርዬ ጠበንጃው የሚተፋው ጥይት መሬት ጠብ አይልም ነበር አሉ። የጠላትን ግንባር በጥርሷል። የላንዳፍታው ገብርዬም ብዕሩ የሚተፋው እሳትም እንዲሁ መሬት ጠብ ሳይል የወዳጅን አንጀት እያራሰ ጠላትን ድብን እርር አድርጓል። ይህን ብዕር፣ ይህን ዕውቀት፣ ይህን ጥልቅ ግንዛቤ አፈር ይበላው ይሆን? ጉሽ ልበልህ ገብርዬ፣ አበጀህ። በርታ። ሌላ የምለው አይኖረኝም።

ገብርዬ፣ ምክርህና የምትሰጠው ትምህርት ቀላል አይደለም። ቀደም ሲል የፃፍካቸው ሸጋ ጽሁፎችህ እንዳሉ ሆነው ባለፈው እትም ላይ ስለካቤላና በዚያም አንፃር አዳዲስ መንግስታት በአፍሪካ ውስጥ በጡንቻ ስልጣን ሲይዙ የአውሮፓና የአሜሪካን «ጌቶቻችን» የሚያደርጉትን ማሽቃበጥ በተመለከተ ያቀረብከው ጽሁፍ ሰሚ ቢያገኝ ትልቅ ትምህርት ሰጪ ነው። በአይኤምኤፍ የብድር ገንዘብ መሬት የጠበባቸው ሞቡቱ ሴሴኮ በኃይል ወርደው ሌላ የተራበ ካቢላን ያዘዘበትን የኮንጎን(ዛየርን) ህዝብ እንግዲህ እግዜር ይርዳው እንበላ፤ ሞቡቱ ተቀናቃኛቸውን ሁሉ አጥፍተው ለረዥም ጊዜ ፈላጭ ቆራጭ መሪ የሆኑት እንዳልከውም የአይኤምኤፍና የአውሮፓ ሃብታሞች ጠፍጥፈው የሰሯቸው በመሆናቸው ነበር። አሁን ግን ሞቡቱ ጊዜ ሲዞርባቸው አሜሪካኖቹ ከአዲሱ ካቤላ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር በመሯሯጥና ጠፍጥፈው የሰሯቸውን ሞቡቱን በመርገም ላይ ናቸው።

(ተካልኝ አለበል–ከዋሽንግተን)

---

ውድ ላንዳፍታዎች፣

እንደምን አላችሁ?

አንድ የሚያሳስበኝ ነገር አለ። በአብዛኛው የአሜሪካ ከተሞች ኢትዮጵያውያን (99.9% ማለት ይቻላል) ምዕመናኑን በማጠናከር፣ ሕዝባችንን በማስተባበር፣ ቤተክርስቲያን በመመስረት አኩሪ ስራን ሰርተዋል። የወያኔው ታጋይ ጳጳስ የሚያደርጉትን ሁሉ ተወጥተው ምዕመናኑ፣ ጳጳሳቱና የኢትዮጵያን ቅርስ ደጋፊ ምሁራን በከፈሉት መስዋዕትነት ዛሬ በምዕራቡ ዓለም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደ እንቁ አብርታለች። ይህ ያስበረገጋቸው ወያኔዎች በተለያዩ ስቴቶች ህዝብን የመከፋፈል ሱስ ያላቸውን ግለሰቦች በመቅረብ ህዝባችንን በጐሳ ለመከፋፈል ያደረጉት ጥረት የሚረሳ አይደለም። ስለዚህ በወገን መካከል ውዥንብር በመርጨት ለመበታተን የሚሞክሩትን ሁሉ ነቅተን መጠበቅ አለብን። ርክበ ካሕናቱና ምሑሮቻችንም በቂ ጥናት በማድረግ አፀፋውን መመለስ መቻል አለባቸው። የመበታተን ፈርጅ በሁሉም በኩል ተንጨፍሮ ስለሚታይ አቋም ለመውሰድ ሁኔታዎችን መመርመር ይኖርብናል ባይ ነኝ። በዚህ አጋጣሚ ላንዳፍታዎች ለምታበረክቱት የሀገር አንድነት ትምህርትና ባህል ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው።

እምነቱ – ከዳላስ

---

ውድ ወገኖቼ፣

ሁኔታውን በትክክል እንደተረዳችሁት አልጠራጠርም። ይህም ዛሬ ሀገራችንን በዘርና በኃይማኖት የሚበጣጥሰው የጐሰኞች በሽታ ወይም መርዝ አገራችንንና ዘመዶቻችንን እያስጨነቀ ነው፤ እዚህም ከዚህ በሽታ አምልጠን በስደት በሁለተኛ ዜግነት በምንኖርበት ቦታ እነዚህ የጐሳ ውሾች በሽታቸውን ለማስተላለፍ እንደተነከሰች ውሻ ሲክለፈለፉ እናያለን። እንደሚታወቀው የውሻ በሽታ ከመልከፉ በፊት መከተብ መፍትሄ ነው፤ አለበለዚያ ያለው አማራጭ ከፅኑ ህመም አልፎ ሞት ነው። ስለሆነም ሁላችንም በመተባበር የተነኩትን ውሾች በማግለል ጤንነታችንን ከጠበቅን ነፃ የምንሆንበት ቀን ቅርብ ስለሚሆን የሁላችንም ክንድ በአንድ ማበር አለበት እንጂ በረባ ባልረባውም መነታረክ የለብንም። እስካላበርን ድረስ ጉርሾውም እንሶስላውም ሊያታልለን ይችላል።

በሌላ በኩልም ወንዱን ብቻ ሳይሆን ሴት ታጋይ እህቶቻችንም ማፍራት አለብን። ሴቶቻችን ወይም እህቶቻችን በታሪካችን ከወንዱ ጐን ተሰልፈው አጋር በመሆን ጦርነትን፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ታግለው ሀገራችንን ወያኔ ስልጣን እስኪያዘበት ድረስ አቆይተውልናል። በብልህነታቸው በ5ቱ ዓመት የአርበኞች ትግል (በጣልያን ጊዜ) በርካታ ጀግኖችን ከሞት አድነዋል። በሀገር ባህል ዘፈንና ጨዋታም በማንተራስ መልዕክትን አስተላልፈዋል፣ ወገኖቻችንን አስጠንቅቀዋል ከጥፋትም አድነዋል። በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ በተለምዶ የተላለፈልንን የእህቶች ምሳሌ እንመልከት።

አንዲት ሴት ነበረች። በዱር በገደል በፋኖነት በጠላት ላይ ያመፀ ወንድሟ ሊጠይቃት ሲመጣ በነጭ ለባሾች ጥቆማ የተነሳ ጠላት የወንድሟን መምጣት ይሰማና ቤቱን ይከባል። ሰው ልካ ለወንድሟ እንዳታስጠነቅቅ እየተጠበቀች ስለሆነ መላክ አትችልም። ወንድሟ እንዴት እንደሚያመልጥ ስታወጣ ስታወርድ ከቆየች በኋላ በዘፈንና ህዝቡ በሚገባው ልሳን ማስጠንቀቅ እንዳለባት

ተረዳችና እንዲህ ብላ ሙክ ብላ ዘፈነች።

«የሳሃሪን ሜዳ፣ ሽንብራ የዘራው
ሽንብራ የዘራው፤»

ወንድምዋም ይህን እንደሰማ

«እጁን ያወጣል የጠረጠረ ሰው» በማለት ፈትለክ ብሎ አመለጠ። ወታደሩም ሊይዘው አልቻለም ይባላል። ይህንን ልውውጥ እዚህ ላይ ለመጥቀስ የፈለግሁት ሴቶቻችን እንደዚሁም በአጠቃላይ ህዝባችን ከባህሉ ጋር ትግሉንና ልፋቱን በማቀናጀት እንዴት በመጥፎም ጊዜ ኑሮውን እንደሚገፋ ለማሳየት ነው። በዘመኑ ቴክኖሎጂ አይግፋ እንጂ ወገኖቻችን ምን ያህል ብልህና አዋቂ እንደሆኑ ዓለም ያውቀዋል። በመጨረሻም በቲፒኤልኤፍ የተዘራብንን ችግር ለመወጣት እጅግ በጣም ጥራት ያለውና የማያሰልስ ትግል ማድረግ ይኖርብናል። ይህም ትግል የህዝባችንን ተመክሮና የአሁኑንም ሁኔታ አብሮ በመመርመር ከጠላት አንድ እርምጃ ወደፊት ርቀን መገኘት አለብን።

በሉ ላንዳፍታዎች ከእንግዲህ አንባቢ ብቻ ከመሆን ያለችኝን ለመወርወር እጥራለሁ። ይህቺ የመጀመሪያቱ ደብዳቤዬ ናት፣ ለወደፊቱ በሰፊው ለመቀጠል እሞክራለሁ።

አይቼው አላልፍም – ከሴንትሉዊስ ሚዙሪ

---

## የእምነት ቃልኪዳን

በሴንትሉዊስ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ቤተክርስትያን ለመመስረት ቃል ገቡ።

እምነታችንና ባህላችን ማሳደግ በሎም ለልጆቻችንና ለመጭው ትውልድ ታሪካችንን ማስተማር የወቅቱ አጣዳፊ ጥያቄ ነው። መሳውን አባላት በማሳተፍ በተደራጀ መልክና በአንድነት ፈጣሪያችንን እንድንለምንና በስደት ህይወታችንም ለመፅናናት ከዚያም አልፎ የጥንቷን ቤተአምልኮት መሰረት ለመጣል ህዝባችን ያለው ፍላጐት እጅግ የሚያኮራና የሚያስደስት ነው።

በምዕራቡ ዓለም ማለትም በአሜሪካ፣ በካናዳና በአውሮጳ የምዕመናኑንና የታጋይ አማኞችን ፈለግ በመከተል እህት ቤተክርስትያን ለመመስረት ከየስቴቱ በማበረታታት ለረዳችሁን ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ምስጋናችን ከፍተኛ ነው። በተለይም ይህንን ዕኑ የሞራል ፍላጐት 'በመገንዘብ የላንዳፍታ መፅሔት ክፍል ከመፅሔት ሽያጭ በመቀነስ ላበረከቱት የገንዘብ ርዳታ ምስጋናችን ከፍተኛ ነው።

በዚሁ በላንዳፍታ መጽሔት ላይ የወጣችዋ የአትላንታው ሳህሊተ ማርያም ቤተክርስቲያን ምዕመናን ቆራጥነት የበለጠ እንድንጠነክርና እንድንሰራ ረድቶናል።

ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋች!!
ሰላም ለሁላችን ይሁን ለማንኛውም ዕርዳታ
ስልክ ቁጥር (314)367–4014
የሴንትሉዊስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መስራችና አስተባባሪ ኮሚቴ

---


Allstate®
You are in good hands.

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978
Fax: (404)299-6266

AUTO
HOME OWNER'S
RENTERS
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO

CALL US FOR
NEW & USED
CARS LOAN



Theodros
Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indeminity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You're in good hands.

# ከዜና ማኅደር

# እንዲህ ሆነ!

## የኢህአዴግ ባለስልጣናት የአሜሪካ ጉብኝት አሳፋሪ ሁኔታ እያስመዘገበ ነው!!

በምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ በአቶ ዳዊት ዮሐንስ የሚመራው የኢህአዴግ/ወያኔ ልዑካን ቡድን ከጁላይ ወር ጀምሮ በሰሜን አሜሪካና በካናዳ ከተሞች በመዘዋወር ኢትዮጵያውያን፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ በዘር በመከፋፈል በተናጠል ለስብሰባ በመጥራት ስለ ኢትዮጵያ «ተጨባጭ» ሁኔታና ስለኢህአዴግ ፖሊሲ ለማስረዳት ያደረጉዋቸው ስብሰባዎች ከፍተኛ ተቃውሞና አድማ የተካሄደባቸው መሆኑን በሚያሳፍር ሁኔታ መክሸፋቸው በዓለም አቀፍ የተግባር ኮሚቴ አማካይነት የደረሰን ዜና ዘግቧል። <u>በአትላንታ</u> 10,000 ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ ከሚገመትበት በዚህ ከተማ ለኢትዮጵያውያን ተብሎ ጁላይ 19 በተጠራው ስብሰባ የተገኙት ሰዎች 30 ብቻ ሲሆኑ እነኚህም የወያኔ ደጋፊ የሆኑ የትግራይ ልጆችና አድርባዮች እንደሆኑ ታውቋል። በዚህ ዕለት ሁኔታውን በቪዲዮ ለማጠናከር የሞከሩ ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን የካሜራ ፊልማቸው ወያኔ በቀጠራቸው የሴኩሪቲ ዘቦች ተነጥቀው ከአዳራሹ ከተባረሩ በኋላ በብዙ ጭቅጭቅ ፊልሙን ሊያስመልሱ ችለዋል። በከተማው የሚገኙ አንዳንድ የወያኔ ደጋፊዎች ያሳዩት የድንፋታና የቁጣ ሁኔታ ማንአለብኝት የሚሰማቸው መሆኑን በቅርቡ ለማየት ተችሏል። በማግስቱም ጁላይ 20 በ2:00PM አማራና ኦሮሞውን ለሁለት በመክፈል በተጠራው ስብሰባ ከአማራው ወገን አንድም ሰው ያልተገኘ ሲሆን ከኦሮሞው ወገን ደግሞ ሁለት ሰዎች ሲገኙ በዚሁ ምክንያት ልዑካኑ እስከ 4:00PM ከጠበቁ በኋላ ተሰብሳቢ ባለማግኘታቸው በሚያሳፍር ሁኔታ ወደመጡበት መመለሳቸው ታውቋል።

<u>በሚኒያፖሊስ፤ በሲያትል፤ በኦሃዮና በኦቶዋ ካናዳ</u> ልዑካኖቹ ሊያደርጉ ያቀዱዋቸው ስብሰባዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍተኛ ተቃውሞ የደረሰባቸው መሆኑን ከየቦታው የተገኙት ዜናዎች ያበስራሉ።

ኦገስት 2 ቀን <u>በዋሽንግተን ዲ ሲ</u> በኤምባሲው አማካይነት በተደረገ ጥሪ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ኢትጵያውያኖች መካከል ጥያቄ ለማንሳት በፈለጉ ኢትዮጵያውያን ላይ በአምባሳደሩ ትዕዛዝ የዱላ ውርጅብኝ የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ለህክምና ወደ ሆስፒታል መላካቸው ታውቋል። ኦገስት 9 በሳምንቱ ተስስይ ስብሰባ ተጠርቶ በዚሁ ስብሰባ ላይ ወደ 300 የሚጠጉ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን ተሰብሳቢዎቹ 1ኛ. በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙት አቶ ዳዊት ዮሐንስ ኢትዮጵያ የምትባል አገር በታሪክ የለችም ያሉ ስለሆነ ስለ ኢትዮጵያ ሊናገሩ አይችሉምና አዳራሹን ለቀው ይውጡ፤ 2. አምባሳደሩ ባለፈው ሳምንት በአደረጉት የሰው ማስደብደብ ወንጀል ይፋ ይቅርታ ይጠይቁ፤ 3. አንደኛው ተናጋሪ ኤርትራዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደሉምና ድርሽን ለቀው ይውጡ የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው መልስ ባለማግኘታቸው በአዳራሹ የተሰበሰበው ሕዝብ "አትነሳም ወይ! አትነሣም ወይ! የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ! " በማለት መዝሙር አሰማ። አምባሳደሩ የፖሊስ ሃይል እንዲመጣ ቢያዙም ተቃዋሚዎቹ ከተሰብሳቢዎቹ 95% በመሆናቸው ፖሊሶቹ በሆቴሉ ጥያቄ ስብሰባው እንዲበተን በማድረጋቸው ተበትኗል።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስራ አስኪያጅ ከነካቢኔያቸው ተባረሩ ከተወገዱት አንዱ ከሀገር እንዳይወጡ ታገዳ

ዝነኛውን የኢትዮጵያን አየር መንገድ ለውድቀትና ለኪሳራ በመዳረጉ የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ዶ/ር አህመድ ቀሎ ከነካቤኒያቸው ከስልጣን መባረራቸው ሲታወቅ የስራ አመራር ቦርዱ በስራ ዘመኑ በችሎታ ማነስና የአመራር ድክመት ድርጅቱን ኪሳራ ላይ ከመጣሉም በላይ ከፍተኛ ምዝበራና ብክነት ማድረሱን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ። በዚሁ ካቢኔ ይመራ ከነበረው የሥራ አመራር ቡድን አባል የነበሩት ኤርትራዊው አቶ ገብረህይወት ገ/እግዚአብሔር ከሀገር ሊወጡ ሲሉ ከአውሮፕላን እንዲወርዱ መደረጋቸውም ታውቋል።

አቶ ገብረሕይወት መቀሌ ተወልደው ያደጉ ኤርትራዊ ሲሆኑ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ በኮንትሮሰርነት፣ በማርኬቲንግ ማኔጀርነት ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን አሁን በፈረሰው የአየር መንገዱ የአመራር ቡድን ውስጥ ቁልፍ ስፍራ ይዘው በርካታ ገንዘብ ሲያንቀሳቅሱ የቆዩ ናቸው። ኤርትራዊ ባለቤታቸውም በአየር መንገዱ ውስጥ ሲኒየር ሆስተስ በመሆን እየሰሩም ናቸው። አቶ ገብረሕይወት በስልጣን ዘመናቸው ወቅት ከአንድ የአሜሪካን የኮምፒየተር ሲስተም አቅራቢ ኩባንያ ጋር ባካሄዱት ግዢ በተገኘ ጥቅም አሜሪካና ካናዳ ውስጥ ቤት እንዳላቸው በሰፊው ይወራል።

በሌላ በኩል አቶ ሰዬ አብርሃ አሁንም በቦርድ ሊቀመንበርነት አየር መንገዱን የሚመሩ ሲሆን በስራ አስኪያጅነቱ ቦታ በአየር መንገዱ ውስጥ ለ24 ዓመት በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ይሰሩ የነበሩት አቶ ብሥራት ንጋቱ የተባሉ ሲተኩ፤ የአየር መንገዱ የሽያጭ መምሪያ፣ የፋይናንስ መምሪያ፣ የቴክኒክና የበረራ ኦፕሬሽን፣ የህግ፣ የአስተዳደርና የኮርፖሬት ፕላኒንግ መምሪያዎች በአዲስ ሹማምንት ተክተዋል። እኒህ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ከውድቀት ለማዳን ከመንግስትም ሆነ ከሠራተኛው ኃላፊነት የተጣለባቸው አዲሱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ብሥራት በዶ/ር አህመድ ቀሎ ወቅት በጡረታና በካሳ የተገለሉትን እውቅ የአየር መንገዱን ባለሙያዎች ሰብስበው በማነጋገር ወደ ስራቸው እንዲመለሱ፤ እንዲሁም የወደቀውን አየር መንገዳችንን አመቺ አመራር በማስፈን ከውድቀት ለማንሳት ከኢህአዲግ አመራር ማንዴት እንደተሰጣቸው ለማሳመን ቢሞክሩም ተጠያቂዎቹ ወደ ስራ ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

## ኢትዮጵያና ኬንያ ወንጀለኞችን መለዋወጥ የሚያስችል ስምምነት አደረጉ

31ኛው የኢትዮጵያና የኬንያ የጋራ ኮሚሽን ሰሞኑን አዲስ አበባ ውስጥ ባካሄደው ስብሰባ ሁለቱ ሀገሮች ወንጀለኞችን ለመለዋወጥ የሚያስችል ስምምነት ላይ በቅርቡ እንደሚደርሱ ፍንጭ ሰጠ። ከዚህም በተጨማሪ የጋራ ኮሚሽኑ ስደተኞችን ለመመለስም የሚያስችል ስምምነት ከመድረሳቸውም በላይ በጋራ ድንበሮቻቸው ላይ ሊፈጸሙ የሚችሉ ህገወጥ የጦር መሣሪያዎች፣ የአደገኛ ዕፅ ዝውውሮችና ንግዶችን ለመቆጣጠር፣ የጋራ

ሰላምና ደህንነትን ለማስከበር ጥረት ለማድረግም መወሰናቸው ታውቋል። እንዲሁም በድንበሮች አካባቢ በሚኖሩ ጐሳዎች ለሚነሱ ግጭቶችም በተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች እንዲዳኙ በኬንያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስቴፋን ኮሎንቦ መሰያካና በኢትዮጵያው አቻቸው በአቶ ስዩም መስፍን የተመራው የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ሌላው ትኩረት የሰጠበት ጉዳይ ነበር። ይሁን እንጂ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሁለቱ ሀገሮች ድንበር ላይ በተቀሰቀሰው የዘላን ጐሳዎች ውጊያ ከኢትዮጵያ የተሻገረው የተደራጀ ኃይል በርካታ ኬንያውያንን ገድሎ የከብቶች ዝርፊያ በመፈፀም ላደረሰው ጥፋት ኬንያ ላቀረበችው የካሣ ጥያቄ የጋራ ኮሚሽኑ እንደተወያየበት ቢታወቅም ምን እልባት እንደሰጠው ግን የታየ ፍንጭ የለም።

በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው የአዲስ አበባው የሁለቱ አገሮች ሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ እየተካሄደ የተለያዩ የዓለም የዜና አውታሮች በኢትዮጵያ ጠረፍ ላይ የሚኖሩ ጐሳዎችና በኬንያ ቱርክና ጐሳዎች መካከል ግጭት መደረጋቸውንና የኢትዮጵያ ዘላኖች ከ24 የማያንሱ የኬንያ ቱርካናዎችን በመግደል ከብቶቻቸውን መዝረፋቸውን የገለፁ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዴይሊ ኔሽ የተባለው የኬንያ ጋዜጣ የኬንያ ቱርካናዎች በኢትዮጵያ የሜሪሊ ጐሳዎችን በድንገት ወርረው ከብቶቻቸውን ዘርፈው፣ ቤቶቻቸውን አቃጥለው ህፃናትን እንደገደሉ አስታውቋል። ኢትዮጵያ ከጅቡቲና ከኤርትራ ጋር ተጠርጣሪ ወንጀለኛ የምትላቸውን ስደተኞች ለመመለስ ያስቻላትን ስምምነት ቀደም ሲል ያደረገች ሲሆን ሰሞኑን ከኬንያ ጋር ያደረገችው ውል የሰብአዊ መብትን የሚጥስ መሆኑን የፖለቲካ ተንታኞች ይተቻሉ። በኬንያ የኢህአዴግ የጐሳ አመራርን በመቃወም የተሰደዱና በተቃዋሚነት የሚንቀሳቀሱ በርካታ ወገኖች መኖራቸው የሚታወቅ ነው።

## የኢትዮጵያ ብር በኤርትራ ህጋዊ አይሆንም

በኤርትራ ሐምሌ 8 ቀን ናቅፋ የተሰኘውን አዲሱን የኤርትራ ገንዘብ ለማረጋገጥ የወጣው አዋጅ የኢትዮጵያ ብር በኤርትራ ሕጋዊነት እንደማይኖረው ደንግጓል። አዋጁ አዲሱ የኤርትራ ገንዘብ «ናቅፋ» ታሪካዊና ፖለቲካዊ ትርጉም እንዳለው ገልጾአል። የናቅፋ መለያ አርማ ግመል ሲሆን የ1፣ 5፣ 10፣ 50ና 100 ብር ኖቶች ይኖሩታል። «ናቅፋ» ስራ ላይ መዋል በሚጀምርበት ጊዜ አሁን ያለውን ብር ለመሰብሰብ ብቻ የምንዛሪ ተመኑ ከኢትዮጵያ ብር ጋር አንድ ለአንድ ማለትም እኩል በእኩል የሚለወጥ ሲሆን እየቆየ ሲሄድ ግን ብርና ናቅፋ በገበያ ዋጋቸውን ለመፈለግ ይገደዳሉ።

ሐምሌ 8 ቀን «ናቅፋ»ን በገንዘብነት የደነገገው አዋጅ ከ5 ሺህ ብር በላይ በእጁ ያለ ኤርትራዊ በአስቸኳይ ወደ ባንክ ገቢ እንዲያደርግ ያዛል። በዚህ የተደናገጡ ሀብታም ኤርትራውያን ያላቸውን የገንዘብ ብዛት ለሻዕቢያ ላለማሳወቅ ገንዘባቸውን ወደ ኢትዮጵያ ከተሞች በማሸሽ በኢትዮጵያ ባንክ እያኖሩ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ በኢትዮጵያ አሁን የሚሰራባቸው የብር ኖቶች ላይ የደርግን ዘመን የሚያስታውሱ አርማዎች መኖራቸውን የኢህአዴግ አመራር ባለመውደዱ የብር ኖቶቹ እንደሚለወጡ ይሰማል። ይህ በኢትዮጵያ ሊደረግ ይችላል ተብሎ የተገመተው የብር ኖቶች ለውጥ የኤርትራው «ናቅፋ» ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ የሚችለውንም የተደበቀ ብር ለመግታት እንደሆነም ይታሰባል።

## ነጋዴዎቹ ሱቆቻቸውንና ንብረታቸውን ተቀምተው ሊባረሩ ነው

የአዲስ አበባ አስተዳደር በስራ ላይ ያዋለው ከፍተኛ የኪራይ ተመን ነግደን ለመኖር አላስቻለንም በማለት ባለፈው ግንቦት 11 ቀን 1989 ዓ.ም. ሱቆቻቸውን ዘግተው ተቃውሞ ያሰሙትን ነጋዴዎች ለአድማው አነሳስታችኋል፣ የታሸጉ ሱቆችን ሰብራችኋል ተብለው የተወነጀሉት ንብረታቸውን የሚረከብ ኮሚቴ መዋቀሩን በኪራይ ቤቶች አስተዳደር የመኖሪያ ቤቶች ክፍል ኃላፊ የሆኑት ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ በኢህአዴግ/ህወሀት ከሚታተሙ ጋዜጦች አንዱ በሆነው እፎይታ ለተባለው ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ ነው።

የኪራይ ቤቶችም ሆኑ በአዲስ አበባ የሚገኙ ቀበሌዎች የንግድ ሱቆቹን ለመረከብ አስፈላጊውን ዝግጅት ያጠናቀቁ ሲሆን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ በፈቃዳቸው ንብረታቸውን ያላወጡት የሱቅ ባለንብረቶች ከፖሊስ፣ ከቀበሌና ከሌላም አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ እንደሚረከብ ወ/ሮ አወጣሽ ተናግረዋል። የአዲስ አበባ አስተዳደር የንግድ ፈቃድን የመሰረዙና የመዝጋቱ እርምጃ በተለይ ትኩረት ያደረገው የኢህአዴግን የፖለቲካ አቋም በመቃወም በሚጠረጥራቸው ነጋዴዎች ላይ ሲሆን የእነዚህን ተጠርጣሪ ግለሰቦች ሱቆች ግንቦት 11 ቀን በተካሄደው ሱቆችን የመዝጋት አድማ ተካፋይ ባይሆኑም ከሳምንት በኋላ ተካፋይ ነበራችሁ በማለት ሱቆቻቸው የተዘጋባቸው እንዳሉ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ነጋዴዎችን ለአድማ አስተባብራችኋል በሚል የታሰሩት ነጋዴዎች አሁንም እንደታሰሩ ነው።

## ሻዕቢያ በባህር ውንብድና ተወነጀለ

የሻዕቢያ አመራር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀይ ባህርን እያቋረጡ ወደ ተለያዩ የዐረብ ሀገሮች በሚሄዱ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን ላይ በፈጣን የጦር ጀልባዎች የባህር ላይ ጥቃት እንደሚፈፀም ተወነጀለ። የመን ውስጥ የሚንቀሳቀስ አንድ ፀረ–ሻዕቢያ ቡድን በዐረብ ሀገሮችና በሱዳን ለሚኖሩ ስደተኞች በበተነው ጽሁፍ በጀልባዎች ወደ የመንና ሳዑዲ ዐረቢያ የሚሄዱ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ኤትራውያን በተቃዋሚ ኃይሎች እንቅስቃሴ ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ ብሎ ስለሚሰጋ ሻዕቢያ ጀልባዎችን በመገልበጥ አደጋ እንደሚያደርስ ገልጾአል። የሻዕቢያ መንግስት በፈጣን የጦር ጀልባዎች የስደተኞቹን ጀልባ አሳዶ ከመታ በኋላ ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንደሚባለው አደጋ የደረሰው ጀልባዎቹ ትርፍ ሰዎችን በመጫናቸው ነው በማለት በሬዲዮ እንደሚለፍፍ በበተነው ወረቀት አትቷል።

አንድ ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ከኤርትራ ጠረፍ ተነስተው ወደ የመን ከተጓዙ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን መካከል 156 ሰዎች በባህር ላይ በሰመጡ የጀልባዎች አደጋ መሞታቸው ይታወቃል።

## ኢህአዴግ(ህወሀትና) ሻዕቢያ ድንበር እየተካለሉ ናቸው

ኢትዮጵያና ኤርትራን ገነጣጥለው የሚገዙት

ኢህአዴግ(ህወሀት)ና ሻዕቢያ የህዝቡን ፍላጐትና ጥቅም እንዲሁም ታሪክን ሳያገናዝቡ ድንበር መካለል መጀመራቸውን የሚደርሱን የዜና ምንጮች ያስረዳሉ። እነዚህ አስገንጣይ ቡድኖች ገና በረሃ እያሉ የድንበር መካለል ውል አጠናቀው ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የነደፉትን የራሳቸው የሆነ የተለየ አጀንዳ አሁን ቀስ በቀስ ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸውን የፖለቲካ ታዛቢዎች ይጠቁማሉ።

በዚህ የአዲሱ የድንበር ክለላ ትግራይ ውስጥ ያሉት ዛላአንበሳ፣ ዓዲ አውዓላ፣ ዓዲ ሀገራይ፣ ባድመና ሽራሮ እንዲሁም የአከራን አካባቢ ለኤርትራ የሚሰጡ ሲሆን ከኤርትራ ደግሞ የኲናማና የባሬንቱ አካባቢዎች ወደ ትግራይ ይከለላሉ። የኲናማና የባሬንቱ ህዝብ ወደ ትግራይ መካለሉን ባይቃወምም የኤርትራ ህዝብ ግን በለምነቱ የታወቀው አካባቢ ወደ ትግራይ መሄዱን አጥብቆ የሚቃወም ቢሆንም ሻዕቢያ ለዚህ ውሳኔ የደረሰበት ዋናው ምክንያት በትጥቅ ትግሉ ዘመን የባሬንቱና የኲናማ ህዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት በመቆም እጅግ ጠንካራ ውጊያ በማካሄዱና አሁንም በኢትዮጵያዊነቱ ሰለሚፀና በህወሀት ኃይል እንዲጠበቅ የታቀደ ስልት ሲሆን፣ ወደ ኤርትራ የተከለለው የዛላአንበሳ ከተማ ህዝብም ወያኔና ሻዕቢያን አናስጠጋም በማለት ለኢትዮጵያ አንድነት ከመፋለሙም በላይ አሁንም በድንበሩ ያለአግባብ ወደ ኤርትራ የሚተላለፈውን ሸቀጥ በመቆጣጠር ከፍተኛ የሀገርና የህዝብ ሀብት ማዳኑ ሲታወቅ ወያኔ ለሻዕቢያ አሳልፎ በመስጠት በኤርትራ ሰራዊት ተጽእኖ ስር እንዲወድቅ በመታቀዱ መሆኑ ታውቋል።

## መንግስት ቤቶችን በማፍረሱ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች ያለመጠለያ ቀሩ።

የአዲስ አበባ ክልላዊ መንግስት ከሰኔ 28 እስከ ሐምሌ 5 ቀን 1989 በዘመቻ መልክ ከ1200 በላይ ቤቶችን ለማፍረስ በወሰደው እርምጃ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጐችን ያለመጠለያ አስቀርቷቸዋል። የክልሉ አስተዳደር በህገወጥ መንገድ የሚሰሩ የቤት ግንባታዎችን በአደራጀው አፍራሽ ግብረኃይል ወደፊትም በተከታታይ የማፍረስ እርምጃ እንደሚወስድ ያስታወቀ ሲሆን እስካሁን በአዲስ አበባ ዙሪያ በቦሌ ቡልቡላ፣ በአየር ጤና፣ በካራ እንዲሁም በአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ ቤቶችን በቡልዶዘር እያፈራረሰ የግንባታ ቁሳቁሶችን ወስዷል።

የአዲስ አበባ አስተዳደርም ሆነ የፌዴራሉ መንግስት የዜጐችን ችግር ሳያገናዝቡና ሌላ አማራጭ ሳይፈጥሩ አፍራሽ ጦር አሰልፈው በዚህ በክረምት ወቅት ህፃናት፣ አረጋውያን አባቶችንና እናቶችን ሜዳ ላይ መጣሉና ለችግርና ስቃይ መዳረጉ ኃላፊነትና ሰብአዊነት የጐደለው እርምጃ ነው ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

## ኢህአዴግ(ህወሀት) 4 ሺህ ሴት ታጋዮችን ከሰራዊቱ ሊያባርር ነው

የወያኔ ቡድን በረሃ በነበረበት ጊዜ በተዋጊነት ተሰልፈው የነበሩ 4 ሺህ ሴት ተጋዳላዮችን ከሰራዊቱ ለማባረር እየተዘጋጀ መሆኑንና ይህንንም እቅድ ተፈፃሚ ለማድረግ በታጠቅ 4 ጦላይ ጦር ማሰልጠኛ ውስጥ ትምህርት ቤት በመክፈት ለ4 ዓመት አስተምሮ ለብሔራዊ ፈተና እንዲቀመጡ እያዘጋጃቸው መሆኑ ታውቋል።

ማንኛውም ሰው ለ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለመብቃት የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተናዎችን ማለፍ ያለበት ቢሆንም ኢህአዴግ የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓት ደንብ በመጣስ እንዲፈተኑ ወስኖአል። እነዚህ ሴት ታጋዮች የፌዴራሉ መንግስት መከላከያ ሠራዊት ባወጣው ፕሮግራም መሰረት በየወሩ 225 ብር እየተከፈላቸው የሚማሩ ሲሆን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ሁመራ ውስጥ «ዳንሽ» በተባለው አካባቢ በ40ሺህ ሄክታር መሬት ላይ በሚገነባው መንደር እንዲሰፍሩ ይደረጋል።

## የእንግሊዝና የኢህአዴግ መንግስት ግኑኝነት እየሻከረ ነው

አዲሱ የእንግሊዝ የሌበር ፓርቲ መንግስት ለኢህአዴግ አገዛዝ የሚሰጠው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድጋፍ የወያኔን አምባገነንነት የሚያጠናክር መስሎ ስለታየው ፊቱን በማዞሩ በእንግሊዝ መንግስትና በኢህአዴግ አመራር መካከል የነበረው የጋራ ግኑኝነት እየሻከረ መሄድ ጀምሯል።

የኢህአዴግን ፖሊሶች በዘመናዊ የኮሚኒኬሽን መሳሪያ አጠቃቀምና የወንጀል ክትትል ኦፕሬሽንና በስለላ ሙያ በማሰልጠን ከፍተኛ አገልግሎት ሲያበረክቱ የቆዩት ከእንግሊዝ «ቀርት ያርድ ፖሊስ» የመጡት አሰልጣኞችን የኢህአዴግ መንግስት ከኢትዮጵያ ለቀው እንዲወጡ ካደረገ ወዲህና የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በነበሩት የአቶ አሰፋ ማሩ ግድያን ጉዳይ ከአዲስ አበባ ሰፊ ዘገባ በማጠናቀር ለመላው ዓለም የነዛቸውን የእንግሊዝ ጋዜጠኛ ከሀገር በማባረሩ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ አዲስ የተሾሙትን የእንግሊዝ አምባሳደር የሹመት ደብዳቤያቸውን ለሁለት ወራት ያህል ሳይቀበል በመቅረቱ የሁለቱ አገሮች ግኑኝነት ይበልጥ እየሻከረና የቅራኔ ገጽታ እየተንፀባረቀበት መሄዱ ታውቋል።

አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ደግሞ የእንግሊዝ መንግስት በቅርቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጳጳስ ዶ/ር አባ ጳውሎስ ወደ እንግሊዝ እንዳይገቡ ቪዛ የከለከለ ሲሆን የሰጠው ምክንያትም ጳጳሱ እንግሊዝ ሀገር በሚገቡበት ወቅት ኢትዮጵያውያን በሚያሰሙት ተቋውሞ የተነሳ ለፀጥታ አጠባበቅ ችግር በማጋጠሙ ነው የሚል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የኢትዮጵያ ባለስልጣናትና የኢትዮጵያ ፓስፖርት የሚይዙ የኤርትራ ሹማምንት በዲፕሎማቲክ መብት ሽፋን በመጠቀም አደገኛ እጾችን ወደ እንግሊዝ አገር ሲያስገቡ በመገኘታቸው የእንግሊዝ መንግስት በኢትዮጵያ ሹማምንት ላይ ጥብቅ ፍተሻ ለማካሄድ እንደተገደደ እነዚሁ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ሲጠቁሙ፣ በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ቢሮ የወጣው «ማንኛውም የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት የያዘ የመንግስት ባለስልጣን አስገዳጅ ካልሆነ በቀር ወደ እንግሊዝ አገር እንዳይሄድ» የሚል እገዳ ማተላለፉ ለጉዳዩ እውነተኛነት ዓይነተኛው ፍንጭ እንደሆነ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

## የትግራይ ክልላዊ አስተዳደር ለኤርትራውያን መታወቂያ መስጠት ከለከለ

የትግራይ ክልላዊ መንግስት እስከዛሬ ለኤርትራ ተወላጆች ይሰጥ የነበረው መታወቂያ ወረቀት

እንዲታገድ በክልሉ ለተዋቀሩ የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ትዕዛዝ አስተላለፈ።

ከዚህ ትዕዛዝ በስተጀርባ የኤርትራ መንግስት እጅ እንዳለበት የተገኙ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን ትዕዛዙ ትግራይ ውስጥ የሚገኘው የኤርትራ ቆንስላ ጽ/ቤት በኤርትራውያን ላይ ቁጥጥር ለማድረግ አመቺ ይሆንለታል። ኤርትራውያን የአስመራው የሻዕቢያ አገዛዝ ከሚያደርስባቸው ረገጣ ለመሸሽ የኤርትራን ዜግነት በመተው በኢትዮጵያዊነት ስም እንደልብ መንቀሳቀሱ ተስማሚ ሆኖ አግኝተውታል።

## አምነስቲ ኢንተርናሽናል ስለኢትዮጵያዊቷ ጆርጂያዊት መግለጫ ሰጠ

በትውልድ ጆርጂያዊት በዜግነት ኢትዮጵያዊት የሆኑት ወ/ሮ ስቬትላና ማሚዶቫ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከ2 ዓመት በላይ ከታሰሩ በኋላ ለ5ኛ ጊዜ ሰኔ 6 ቀን እንግሊዝ ሀገር ተወስደው መጣላቸውን በመቃወም አምነስቲ ኢንተርናሽናል መግለጫ አወጣ።

እኒህ ሴት ለትምህርት ወደ ሶቪየት ከሄደ ኢትዮጵያዊ ጋር ተጋብተው ወደ ኢትዮጵያ ከዛሬ 20 ዓመት በፊት መጥተው የኢትዮጵያን ዜግነት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ይኖሩ እንደነበር ሲታወቅ ባልታወቀ ምክንያት በህዳር ወር 1984 በኢህአዴግ የጥበቃ ልዩ መምሪያ በተባለው የፖሊስ ተቋም ከታሰሩ በኋላ መጀመሪያ የዜግነት መብታቸው ተገፈው በሱዳን፣ በሞስኮ፣ በቱርክ እንደገናም በሱዳን ከተሞች እየተወሰዱ እየተጣሉ የዜግነት መብታቸውን ለማስከበር እየተመለሱ እየመጡ በኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶች 2 ዓመት ከቤተሰባቸውና ከወለዱት አንድ ወንድ ልጃቸው በመለየት አሰቃቂ ችግር ደርሶባቸዋል።

አምነስቲ ስቬትላና ማሚዶቫ በኢትዮጵያ እስር ቤት በቆዩበት ዘመን ህክምና መከልከላቸውን በሰንሰለት መታሰራቸውንና መደብደባቸውን በቅርቡ ባወጣው ልዩ መግለጫ ጠቅሶ በተለይ አንድም ጊዜ ፍርድ ቤት ያለመቅረባቸው በጣም እንዳሳዘነው አስታውቋል።

ኢትዮጵያዊቷ ጆርጂያዊት ማሚዶቫ በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ አገዛዝ ያለ ፓስፖርት ለ5ኛ ጊዜ ከሀገር አስወጥቶ ከጣለበት ሎንደን ውስጥ በስደተኝነት ይኖራሉ።

## ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት ከተመሰረቱባቸው ክሶች ውስጥ ሁለቱ ውድቅ ሆኑ። የትምህርት ዓለም አቀፍ ልዑካን ቡድንን በወህኒ ቤት አነጋገሩ።

ኢህአዴግ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርን ለማዳከም ሲል በፈጠረው የእስር ሰበብ በመንግስት ግልበጣና በሽብር ፈጣሪነት ወንጀሎ በእስር የሚያሰቃያቸው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት ዶ/ር ታዬ ከተመሰረተባቸው ክስ ሁለቱ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጋቸው ታውቋል። ዶ/ር ታዬ በአሜሪካ እርዳታ ድርጅት ጽ/ቤት ቦምብ ያመጣል፣ በኢጣሊያው የስራ ተቋራጭ ሲኤምሲ ሰራተኞች ላይ የአፈና ተግባር መፈጸም ጋር በተያያዘ የተመሰረተባቸውን ክስ ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገላቸው ሲሆን መንግስት ለመገልበጥ አሲረዋል የተባሉበትን ክስ ብቻ እንዲከላከሉ መደረጋቸውን ከጠበቃቸው በተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከግንቦት 12–17 በኢትዮጵያ ቆይታ አድርጐና ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያትን በወህኒ ቤት ቀርቦ ያነጋገረው የትምህርት ዓለም አቀፍ የተባለው የልዑካን ቡድን ያቀረበውን ዘገባ የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ ተመልክተው በማኅበራት ነፃነትና በነፃ የመደራጀት መብት ላይ የቀረቡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ሊሆኑ በሚገባቸው ነጥቦች ላይ ኢመማንና መንግስትን አቀራርቦ ለማነጋገር መወሰናቸውን ገልፀዋል። በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ይኸው የልዑካን ቡድን አቶ መለስን ለማነጋገር ቢፈልግም አቶ መለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የልዑካኑ ቡድን አባል የሆኑትን የአሜሪካ መምህራን ማህበር ተወካይ ሚስተር ሚኪ ኢባራን ብቻ በአሜሪካዊነታቸው ተቀብለው ማነጋገራቸው ታውቋል።

በዚህ ወቅት ለሚስተር ሚኪ አቶ መለስ ከኢመማ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆናቸውን ፍንጭ የሰጡ ቢሆንም ከኢመማ ለመደራደር ግን ኢመማ ሽብርተኝነትን እንዲያወግዝ፣ ከሽብርተኞች ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲያቋርጥና የኢትዮጵያን ህገመንግስት እንዲቀበል ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ማስቀመጣቸው ታውቋል።

## ከወልቂጤ ወህኒ ቤት እስረኞች አመለጡ

በጉራጌ ዞን ከወልቂጤ ወህኒ ቤት 22 እስረኞች ግንቦት 23 ቀን ግንብ ደርምሰው ጠባቂ ፖሊሶችን አዘናግተው ማምለጣቸውን ከአካባቢው የተገኘ መረጃ ጠቁሞአል።

እስር ቤቱን ደርምሰው ያመለጡት እስረኞች እስካሁን ያልተያዙና አድራሻቸውን የሰወሩ ሲሆን ለማምለጥ ውሳኔ ያደረጉት ለበርካታ ወራት ክስ ሳይመሰረትባቸው ንፅህና በጐደለውና የምግብ አቅርቦቱ ባልተስተካከለ ሁኔታ በእስር በከፍተኛ ስቃይና እንግልት ስለደረሰባቸው ህይወታቸውን ለማትረፍ የወሰዱት ቆራጥ እርምጃ መሆኑን የደረሰን መረጃ አክሎ ገልጿል። በወልቂጤው እስር ቤት አሁንም ቁጥራቸው ወደ 300 የሚጠጉ እስረኞች በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን የደረሰን መረጃ ጠቅሶ በወህኒ ቤቱ የጤና አጠባበቅ ሁኔታ መጓደልና በረሃብ የተነሳ በቅርብ ጊዜ ውስጥ 3 ሰዎች መሞታቸው ታውቋል።

## እንግሊዞች ለአቡነ ጳውሎስ የመግቢያ ቪዛ ከለከሉ የሚባል ወሬ ይነፍሳል

አቡነ ጳውሎስ በቅርቡ ወደ ዋሽንግተን ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት እግረ መንገዳቸውን እንግሊዝ ለመሄድ በማሰብ እንግሊዝ መግቢያ ቪዛ ቢጠይቁ የተከለከሉ መሆኑን አንዳንድ በውል ገና እርግጠኛ ያልሆኑ ምንጮች ገልጸዋል። ለዚህም ምክንያት ሆኖ የቀረበው እንግሊዝ አገር ያሉ ተቃዋሚዎቻቸው ቀደም ሲል በ1993 ያደረሱባቸው ዓይነት አደጋ እንዳይደርስና እንዲያውም ባስገደሉት ባህታዊ ሳቢያ ከፍተኛ ጥላቻ ስላላለባቸው እንግሊዝ ስለደህንነታቸው የፈራች ሳትሆን አትቀርም የሚል ግምት አለ።

## መርካቶ ገበያ
## አትላንታ
## Merkato Gebeya
## Atlanta

- ♠ ቅመማ ቅመም — Eth. Food & Spices
- ♠ እንጀራ — Injera
- ♠ ጤፍ — Gift Items
- ♠ ቪዲዮ ቴፕ — Video tapes
- ♠ መጽሔቶች — Cultural Items
- ♠ የባህል ዕቃዎች — Magazine
- Teff

በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ምግብ
ይዞ ለመሄድ

CARRY-OUT
FOOD

3300 Buford Hwy
Atlanta GA 30329
Phone: (404)320-9777
Fax: (404)320-6863



## የእትመትና
## የትርጉም ሥራ

በኮምፒውተር የአማርኛና
የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

ከለር ማስታወቂያዎች፣
መጽሐፍት፤ መጽሔቶችና
የተለያዩ የአማርኛና
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን በጥሩ ዋጋ
በፍጥነትና ጥራት ባለው ሁኔታ
ለማሰራት ከፈለጉ ደውለው
ገንትን ያነጋግሩ።
በተጨማሪ የትርጉም ሥራዎችን እንሠራለን

ስልክ — (404)508–4657
ፋክስ — (404)508–2447



$115

ዋሸራ 2.0
*for Windows 3.1x Windows 95*

## *EthiO Systems*
PO Box 36921
Houston, TX 77236
(713)995-4360
ethiosys@neosoft.com
http://www.neosoft.com/~ethiosys/ethiosys.html

**Supported Software**

**Word Processing:** MS Word, WordPerfect, WordPro, AmiPro,...

**Spreadsheets:** Lotus 1-2-3, MS Excel, Quattro Pro,...

**Database:** MS Access, Lotus Approach,...

**Publishing:** PageMaker, QuarkXPress, Corel Ventura,...

**Illustration:** CorelDRAW, Adobe Photoshop, Photoworks, ...

**Internet:** Eudora, Internet Explorer, Netscape Navigator, Exchange,...
**Windows 3.1x and Windows 95** resident programs

**በኢትዮጵያ ቋንቋና ፊደል**

መዕሄት፣ መዕሀፍና ልዩ ልዩ ሰነዶችን፤
ስፕረድሽቶች፤
ዴታቤዝ፤
ንግግር ማቅረቢያ ዝግጅት፤
ኤሌክትሮኒክ መልክት፤
ዌብ ገፅ፤
ልዩ ልዩ ስዕላዊ ፊደላትና የመሳሰሉትን
ከታወቁ ሶፍትዌሮች ጋር ለማዘጋጀት
የሚያስችል ሲስተም።

ዋሸራ 2.0
በነዚህ መደብሮች ይገኛል

**Maru Grocery**
**Houston, TX (713)665-6608**
**Dallas, TX (214)373-6278**

**Ethio Sound**
**Washington, DC (202)232-0076**

**Addisu Gebeya**
**Washington, DC (202)986-6013**

**Queen of Sheeba**
**Fallls Church, VA (703)998-0180**

# ኢህአፓ ባለፉት 25 ዓመታት

## ከላንዳፍታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል

ስለኢህአፓ የማያውቅ የለም። አህአፓ ከተመሠረተ ይኸው 25 ዓመታት አለፉ። ዘንድሮ የምሥረታው 25ኛው ዓመት በደመቀ ሁኔታ ሉስ አንጀለስና በተለያዩ ቦታዎች ተከብሯል። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ምን ተከናወነ? ምን ችግር ገጠመ? በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ በቃለ መጠይቅ መልክ ያቀናበርነውን ዝግጅት ይዘን ቀርበናል። በመጀመሪያ አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ የ25ኛው በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ አባልን ሰለ በዓሉና ሰለ ኢህአፓ በአጠቃላይ ከጠየቅን በኋላ ከድርጅቱ መሥራች አባላት አሁንም በአመራር ላይ ያሉትን የአቶ ኢያሱ ዓለማየሁን ቃለመጠይቅ እናቀርባለን። በመጨረሻም የታዋቂው የኢህአፓ መሥራች የዶክተር ተስፋየ ደበሳይ ልጅ ወጣት ሀምራዊት ተስፋየ በጉባኤው መክፈቻ ላይ ያቀረበችውን ታሪካዊ ንግግር እናቀርባለን።

### ከአቶ ሰለሞን ገ/ስላሴ የ25ኛው የኢህአፓ በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ አባል ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ላንዳፍታ፣
ኢህአፓ ባለፉት 25 ዓመታት ያደረገውን ትግል አጠር ባለ ሁኔታ ቢገልጹልን።

አቶ ሰለሞን፣
የኢህአፓን የ25 ዓመት ግምገማ በአምስት በአምስት አመት ከፍሎ ማየቱ ለግንዛቤ ያመች ይሆናል። ይህንንም በይፋ ከታወጀበት ከ1975 መጀመር ይቻላል።

1975–1980

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዲሞክራሲ፣ ለመሬትና ለእኩልነት ባደረገው ተጋድሎ በግምባር ቀደምትነት እየታገለና ህዝቡን እያታገለ (በተለይም በልሣኑ በ«ዲሞክራሲያ» ወቅታዊ ሁኔታውን እየተነተነና መረዳት እየሰጠ) ታግሏል። በዚህ ወቅት በአንድ በኩል ከደርግ አስከፊ ጥቃት ሲደርስበት በሰሜናዊ የአገሪቷ የገጠር ክፍል ደግሞ ከወያኔና ሻዕቢያ ጣምራ ጥቃት ደርሶበት ከፉኛ ተጐዳ።

1980–1984

የሰፊው ህዝብ እንቅስቃሴ በወታደራዊው ቡድንና በሶቭየት ደጋፊዎቹ ተነጥቆ የሰፊው ህዝብ ወገኖች ቁስላቸውን የሚያጠጉበት ጊዜ ነበር። በደረሰው ጣምራ ጥቃት ምክንያት በኢህአፓ ውስጥም ክፍፍል የተፈጠረበትና ድርጅቱ የተዳከመበት ወቅት ነበር።

1984–1990

ድርጅቱ እያገገመ ሰሜናዊ እንቅስቃሴዎችን ማለትም በኤርትራ፣ በትግራይና በወሎ ያሉትን ትቶ ደቡብ ጐንደርና ጐጃም ወሎ ውስጥ የተንቀሳቀሰበትና በኢትዮጵያ በመላ የሚተላለፍ የሬዲዮ ፕሮግራም ‹ፍኖተ ዲሞክራሲ› የጀመረበት ጊዜ ነበር። በዚህ ወቅት በ1984 በቋራ የፓርቲውን 2ኛ ኮንግረስ አድርጐ የጐደሉ አመራሮችን ያሟላበት ከደርግ፣ ከወያኔና ሻዕቢያ ና ሱዳን ጋርም ይታገል የነበረበት ወቅት ነው።

1990–1995

«ኢህአፓ እስካለ ድረስ ወያኔና ሻዕቢያ ላገሪቷ ያቀዱላት ተንኮል እንደማይሳካ ስለተገነዘቡ የሱዳንን ህብረት በማግኘት በዚህ ወቅት መጀመሪያ ፓርቲውና ሠራዊቱ ላይ ሰፊ ጥቃት በድጋሚ አድርሰዋል። በዓለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍ ደረጃም ደርግና ሶቭየት ህብረት ሲወድቁ አሜሪካ ወያኔና ሻዕቢያን በመያዝ (አነግን ደግሞ ሽፋን ሰጪ) በማድረግ አገሪቱን የከፋፈለና የጐሣ ፓለቲካን እውን ያደረገ የመንግስት ለውጥ አድርገዋል። ኢህአፓ በትጥቅም ሆነ በራዕይ (ሕብረ–ብሔራዊነት) አንድ ታላቅ የፖለቲካ ኃይል ቢሆንም እሱን በማግለል ማለትም የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጐት ወደ ጐን በመተው አለም–አቀፋዊ ደባው ተሳክቷል።

1995–1997

ኢህአፓ ምንጊዜም ያላቋረጠውን የተበጠሱና የተጨፈለቁ ፓርቲ መዋቅሮችን በአገሪቱ በሞላ የሚያስተካክልበትና እንደገና ጉባኤ አድርጐ አመራር ያሟላበትና አሁን ደግሞ በ1997 ከዚያ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ 25ኛ አመቱን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር የቻለበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ላንዳፍታ፣
የኢህአፓ ዋና ዋና የተግባር መርሆዎችን በአጭሩ ቢገልጹልን። በአሁኑስ ጊዜ በምን በምን ተግባር ላይ እየተሳተፈ ነው? ባደረጋቸውስ ተግባራት ምን ውጤት አግኝቷል?

አቶ ሰለሞን፣
የኢህአፓ መመሪያዎችን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ አንፃር ማየት ይቀላል።

1. በፖለቲካ

ሰፊው ህዝብ ያለ ምንም ተፅዕኖና ያለ ምንም ችሮታ ራሱ የመረጣቸውን እንዲሾምና ሲያስፕው ደግሞ ሊሽራቸው ለሚችልበት መብት ያለማቋረጥ ኢህአፓ ታግሏል። ከ1985 እ.ኤ.አ. ወዲህ ደግሞ ይኸ መብት የሚረጋገጥበትን ሥርዓት «መድብለ ፓርቲ» ብሎ ሰይሞ ብዙሃኑ ፓርቲዎች በሰላማዊ መንገድ ለሚወዳደሩበትና አብረው ለሚሰሩበት ሥርአት እየታገለ ነው። ከሞላ ጐደል ከወያኔ በስተቀር አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች እዚህ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ትልቅ እርምጃ ነው እንላለን።

2. በኢኮኖሚ

የሰፊውን ህዝብ ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ ያካተተ በግል፣ በመንግሥትና በህብረት ሥራና መዋዕለ–ንዋይ ተሳታፊነት የተገነባ ኢኮኖሚ ለመመስረት መመሪያ አለው። ዛሬ በአገራችን የድሃው ብዛት ከመቼውም በበለጠ መንሰራፋቱ ህሊና ያለውን እንደሚቆጠቁጥ አንጠራጠርም።

3. በማህበራዊ

በጤና፣ በትምህርት፣ በስፓርት፣ ወዘተ አብዛኛው ህዝባችን ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስርዓት ለመመስረት ዕቅድ አለ። ዛሬ የወያኔና የIMF አገዛዝ እነዚህ የዜጋ መብቶች ከተራ ዜጐች አቅም በላይ እየሆኑ ለጥቂቶች ብቻ የተሰጡ መብቶች መሆናቸውን የማንቀበለውና እንዲለወጥ የምንፈልገው ጉዳይ ነው።

ላንዳፍታ፣
የኢህአፓ ጠንካራና ደካማ ጐኑ ምንድነው ይላሉ?

አቶ ሰለሞን፣
ከኢህአፓ ደካማ ጐኖች ውስጥ የተፈጠረበትና

የአደገበት አሁንም ያለበት በህጋዊነት ለመስራት ካለመቻሉ የተነሳ በምስጢራዊነት የሚሰራ ፓርቲ መሆኑ ነው። ሚስጢራዊነት ችግር አለበት፣ በወጣትነቱ ተመክሮ በማጣት ችግር ነበረበት፣ የኃይል ሚዛንን ሳያጤኑ በከተማ የመከላከል ትግሉን መግፋት፣ በኢህአፓና በዙሪያው ካሉም ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ውጪ ሌሎችን በስፋት ለማቀፍ አለመቻል፣ ምንም እንኳ እየተሻሻለ ቢሆንም በወቅቱ ጥያቄዎች ላይ አንድ እርምጃ ቀድሞ ያልተቋረጠ መሪነት በመስጠት ላይ ያሉ ችግሮች አሉ ነበሩ። ጥንካሬው ወዳጅና ጠላት የማይክድለት በፅናት መቆምን፣ የህዝብ ባለአደራነትን፣ ከሙስና መራቅን፣ መስዋዕትነት መድፈርን የመሳሰሉ ፀጋዎችን ተላብሷል።

ላንዳፍታ፣

በሌሎች ወያኔን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና በኢህአፓ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

አቶ ሰሎሞን፣

ኢህአፓን ከሌሎች ፀረ ወያኔ ኃይሎች ከሚለዩት ጉዳዮች መካከል፦

1) ሙሉ ጊዜያቸውን ለትግሉ ያዋሉ የአመራር አባሎችና ሌሎችም ታጋዮችን ያቀፈ ድርጅት በመሆኑ፣

2) በታሪኩ «ሂዱና ተዋጉ» የሚል አመራር የሌለው ድርጅት መሆኑና የአመራር አባላትም አብረው እንደሚዋጉና እንደሚሰዉ ይታወቃል። ለምሳሌም ያህል፣ (ተስፋዬ ደበሳይ፣ ክፍሌ ተፈራ፣ ፍቅሬ ዘርጋው፣ ፀሎተ ህዝቅያስ፣ ገ/ወ/ሚ (ጋይም)፣ እንዳለ ??ተፈራ፣ ወዘተ)ና በወያኔ እጅ ገብተው መድረሻቸው ያልታወቀ፣

3) በፖለቲካ ጥያቄ ኢህአፓ የሚያነሳው የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ጥያቄ የሰፊውን ህዝብ መሠረታዊ መብቶች ማለትም በልቶ የማደር፣ መጠለያ የማግኘት፣ ሠርቶ የመኖር፣ ወጥቶ በሠላም መግባትን የማዕዘን ደንጊያው ያደረገ መሆኑ፣

4) «ኢትዮጵያዊ አይደለንም እንደራደርበታለን» ከሚሉት ወገኖች አንፃር በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ፣ ህብረ–ብሔርነቱ ጥንካሬን ያላበሰው ድርጅት መሆኑ ነው።

5) በብሔር ጥያቄ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መሠረታዊ የሆኑትን የሰው ልጆች መብቶች ከተጠበቁላቸው በታሪክ በጋራ በክፉም በደጉም የኖሩትንና የተጋሩትን ኢትዮጵያዊነት እንደማይሸሩ በማመን ለእነዚህ መብቶቻቸውና ባህሎቻቸው መከበር ይታገላል፣

6) ኢትዮጵያን የማንም መንግሥት አሽከር በማድረግ ኢህአፓ አያምንም። ይኸ የሚመነጨው ህዝቡን ካለማመንና በሌላ ኃይል ጉያ ውስጥ በመግባት (ደርግ–ሶቭየት፣ ወያኔ–አሜሪካ) የግዛት ቀንን ለማራዘም ከመፈለግ ነው። በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚተማመን ኃይል በገለልተኝነት ላይ የተመሰረተ ከሁሉም ጋር ያለ አድልዎ በወዳጅነት የውጭ ግኑኝነትን ያካሂዳል።

ላንዳፍታ፣

የዘንድሮው የኢህአፓ 25ኛ ዓመት መታሰቢያ ስብሰባ ምን ያህል ውጤት አምጥቷል?

አቶ ሰለሞን፣

25ኛው በዓላችን በኢህአፓና በኢትዮጵያውያን ምሁራን፣ በኢህአፓና በወዳጅ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በኢህአፓና የህብረት ግንባርን ለማምጣት በሚጥሩ ክፍሎች መካከል የትግል አጋርነትንና ትስስርን አሳይቷል። ጉባኤው የምንፈልገውን ብቻ የምንሰማበት ብቻ ሳይሆን ተቃውሞና ትችቶችን (መሰረተ ቢስ የሆኑትን ጭምር) ለማንሸራሸር እንደምንችል አሳይቷል። በአጭሩ ኢህአፓ ለነፃይቱ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መፈጠር ታላቅ ሚና ከሚጫወቱ አንደኛው እንደሚሆን የታየበት ነበር።

ላንዳፍታ፣

የቀድሞውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል በማንኳሰስና ያንን ትውልድ አሁን ለተፈጠረው ችግር በደፈናው ምክንያት በማድረግ፤ ከዚያም በተጨማሪ የኢህአፓን ትግል የአባላቱን መስዋዕትነት በተመለከተ «አላስፈላጊ መስዋዕትነት» የሚሉና ለብዙ ችግሮች ኢህአፓን ተጠያቂ ማድረግ የሚፈልጉ ብዙም ባይሆኑ የተወሰኑ ኃይሎች እንዳሉ ይታወቃል፤ በዚህ በኩል ለሚቀርበው ስሞታና ክስ የሚያቀርቡት መልስ አለ ወይ?

አቶ ሰሎሞን፣

ጥያቄው ሚዛናዊ ፍርድን ለመስጠት የሚችል ጭንቅላቶች ጉዳይ ነው። የዘውዱ አገዛዝ ፍትህን ለጥቂቶች ብቻ ሰጥቶ፣ የመሬትና ባህላዊ ጭቆናን አንሰራፍቶ አገሪቷን ለወሎ ረሃብ አይነቱ አጋልጦ የነበረ ስርዓት ላይ ማመፅ ተገቢ አይደለም የሚሉ የህሊና ዓይናቸው የታወረና ከታሪክ ጋር የተጣሉ ናቸው። የተማሪው እንቅስቃሴ የራሱን ግላዊ ጥቅሞች ወደ ጐን አድርጐ ለህዝቡ የኑሮ ዕድገት መሻሻልና ለአገሪቱ ታላቅነት ያደረገው ትግል አርአያዊ ነው ። የዛሬውስ ተማሪ ያለፈውን እንቅስቃሴ እንዲደግም እንፈልግ የለም ወይ? ከዚያም ኢህአፓ ከደርግ ጋር ያደረገው ተጋድሎ ለፍትህና ለፖለቲካ ሕዝባዊ ሥልጣን ጥያቄ ነበር። በእርግጥ የወጣትነት ትኩስነት ስለነበረ አላስፈላጊ መስዋዕትነቶችና ችግሮች ታይተዋል። ይኸኛው ስህተት ነበር ብሎ በሙሉ ልብነት መናገር ይቻላል። ለዚህ ነው ሚዛናዊ ፍርድ ያስፈልጋል ያልኩት።

ላንዳፍታ፣

ኢህአፓ በደርግም፣ በሻቢያም በወያኔም በጠቅላላ በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ በጉልበት በተንሰራፉ ኃይሎች በየጊዜው እንደተቀጠቀጠ ነው። ከተቋቋመም 25 ዓመታት ሆኖታል። ረዥም ጊዜ ነው። ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ ማሸነፍ አልቻለም፤ ... ተሸንፏል ማለት ግን አለመሆኑ ያው በእንቅስቃሴው እንዳለ ይታወቃል፣ ታዲያ ችግሩ ምንድነው?

አቶ ሰለሞን፣

ኢህአፓ 25 አመት ታግሎ እንዴት «ሊያሸንፍ» አልቻለም? ሁለት ነገሮች አሉ እዚህ ላይ መስተዋል ያለባቸው።

1) ኢህአፓ ስሙ እንደሚያመለክተው ህዝባዊ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ነው። ራሱን ሥልጣን ላይ ማውጣት ቢፈልግ ብዙ አቋራጭ መንገዶች ነበሩለት። ዓላማው ግን ይኸ አይደለም። የሚታገለው ሙሉ በሙሉ ህዝባዊና ኢትዮጵያዊ ሥልጣን በመሆኑ የሚያሸንፈው የኢትዮጵያ ህዝብ በሞላ ሲያሸንፍና የመብቱ ባለቤት ሲሆን ነው።

2) እንደዚህ ዓይነት ህዝባዊ ስልጣን ለማግኘት ደግሞ በርካታ አመታት፣ መስዋዕትነትና እልህ አስጨራሽ ትግል ይካሄዳል። የክፍለ ዓለማችንን የደቡብ አፍሪካን ትግል ብናይ መሪ ድርጅቱ የተመሰረተው (ANC) በ1912 እ.ኤ.አ. ነው። ኢህአፓ ከ60 ዓመት በኋላ በ1972 ነው የተመሰረተው። ANC ሥልጣን የያዘው በ1994 ማለትም ከ82 ዓመት በኋላ ነው። የእኛ የትግል ውጤት ያን ያህል እንዲቆይ ፍላጐት የለንም፤ ወያኔን ለማቸነፍና ህዝባዊ ስልጣንንና መብትን ለኢትዮጵያውያን በአጭር

ጊዜ ለማጉናፀፍ ሰፊ መሠረት ያለው የህብረት ግንባርና ሁለገብ ያልተቋረጠ ትግል የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው።


**ላንዳፍታ፣**
በአሜሪካ አገር ባሉ ከተሞች የሚደረጉ የኢህአፓ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ስለኢህአፓ የሚወሩ፣ እናንተም መልስ ልትሰጡበት ይገባል የምንለው አንድ ጥያቄ አለን። ኢህአፓ ታዋቂ ትልቅ ድርጅት ሆኖ ሳለ በሰሜን አሜሪካ አንዳንድ ከተሞች የሚገኙ አንዳንድ የኢህአፓ አባላት ግለሰቦች በሚሰሩት ስራ ፤ የሚያደርጉት ተግባራት፤ በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ ሌሎች የኢትዮጵያውያን ተግባራት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፣ የሚያሳዩት የጠባብ ድርጅት ስሜት ...ወዘተ ለድርጅቱ ስም መጥፋት ምክንያት ሆኗል የሚሉ አሉ። ጥሩ ስም እንደሌላቸውና ከህብረተሰቡ ጋር በደንብ እንዳልተዋሃዱ ይሰማል? ለኢህአፓ በቅን የሚያስቡ ሰዎች ይህ ሁኔታ እንደሚያሳስባቸው ይናገራሉ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ? ይህ ነገር ፓርቲውንስ አይጎዳውም ወይ?

**አቶ ሰለሞን፣**
በየትም ከተማ የሚገኙ የኢህአፓ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ከዕለት ዕለት የዚህ አገር ኑሮ ባሻገር የሀገርን ጉዳይ እንደኃላፊነት መውሰዳቸው በጣም የሚያስመሰግን ዕርምጃ ነው። አያይዞም በፓርቲያቸው የተለያዩ ስራዎች ላይ መሰማራታቸው ያላቸውን ሀገራዊና የወገን ፍቅር ያሳያል። በተረፈ ግን የኢህአፓ የስነ–ምግባር መመሪያው በውስጠ ደንቡ በግልፅ የሰፈረ ጉዳይ ነው። ዓባላቱና አመራሩ በየትም ቦታና በማናቸውም ጊዜ ህዝብን አክባሪ፣ ኅብረተሰቡ ጉጂ ከሚላቸው ተግባሮች የራቁ፣ በኅብረተሰቡ የተለያዩ ድርጅቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ማንም ሊገምተው እንደሚችለው አልፎ አልፎ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ችግሮቹ እንዳይቀጥሉና እርምት እንዲደረግባቸው ከአካባቢ የፓርቲ አካላት ጋር ቀጥተኛና ገንቢ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ኢህአፓም በዚህ በኩል አጠቃላይ የሆነ ስነምግባርን፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ስለሚኖር ተሳትፎ በተለያዩ ቦታዎች የዓባላት ውይይትና ሰሚናር የማዘጋጀት ዕቅድ አለ። ከብዙ አካባቢዎች በአመዛኙ የምንሰማው አባሎችና ደጋፊዎች ከፓርቲ ስራ በተጨማሪ የህብረተሰቡን ስራዎች በቤተክርስቲያን፣ በኮሚዩኒቲ፣ በህብረት ግንባር ወዘተ እየተሳተፉ እንዳሉ ነው።

**ላንዳፍታ፣**
ቀደም ሲል አባል የነበሩ፣ ለድርጅቱ ትልቅ መስዋዕትነት የከፈሉና በአሁኑ ወቅት ከድርጅቱ ተገልለው ያሉትን መልሶ ለማቀፍ የተደረገ ሙከራ አለ ወይ? እነሱንስ ለመሳብ የገጠመው ችግር ምንድነው? እነሱስ ለመግባት አንፈልግም ብለው የሚያቀርቧቸውና እናንተ የተረዳችሁትን ምክንያቶች ብትገልፁልን።

**አቶ ሰለሞን፣**
ኢህአፓ አብረውት የነበሩት ወደ ድርጅቱ እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ጥረት አድርጓል። ከፍተኛ የአመራር አባላት ባለፉት 10 ዓመታት በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ በግልና በስብሰባ መግለጫ ሰጥተዋል፣ የቀድሞ አባሎች ወደ ድርጅቱ እንዲመለሱ ወትውተዋል። የቀድሞና ቀጣይ አባላት አብረው በተሰበሰቡባቸው መድረኮችም ላይ (ለምሳሌ ሳንዲያጐ 1995) ይኸው ጥሪ ተስተጋብቷል። ጥሪውን በመቀበል ወደ ፓርቲው የተመለሱ አሉ። ኢህአፓ ይኸን ጥረት ያለ ማቋረጥ ይቀጥላል። ሆኖም የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የሥራ ድርርብና በሌሎችም ምክንያቶች ያሰብነውን ያህል የጥሪ ምላሽ አላገኘንም።

ከዚህ በተጨማሪ በድርጅቱ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ላይ ጥያቄ ያላቸው ካሉ ቀረብ ብለው ቢያዩን ከግምታቸውና ከሚሰሙት ውጭ ሁነን ሊያገኙን እንደሚችሉ አልጠራጠርም። እንዲሻሻሉ የሚፈልጓቸውንም ድርጅቱ ውስጥ ሆነው ሊገፉ የሚችሉበት መብት እንዳለ ሁሉም የሚያውቀው ይመስለናል። መቀራረባችን ግን ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ ስለሄደ በፓርቲው፣ በቅንጅቱ፣ በግንባሩ ዙሪያ ዞረን ዞረን ለዚያ ቃል ለገባንለት ህዝብ የድርሻችንን እንደምናበረክት ግን አንጠራጠርም።



የ25ኛው ኢህአፓ ጉባኤ ተሳታፊዎች በከፊል

# ስለኢህአፓ 25ኛ ዓመት ክብረ በዓል ከፓርቲው የወጣ መግለጫ

የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢህአፓ) የ25ኛ አመት በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ከሰኔ 22–24 1989 ዓ.ም. በሎስ አንጀለስ ከተማ አክብሮአል። በዚህ በአይነቱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ የመጀመሪያ በሆነው ጉባኤ ከተሳታፊዎችና ከተጋባዡ ህዝብ የፓርቲውን ታሪክ በተመለከተ ገንቢ ትችቶችና ወቀሳዎች ተስተናግደዋል። የፓርቲው አባላት፣ አመራሩና ደጋፊዎች በሰከነ መንገድ የፓርቲውን ታሪክና የአሁኑን የትግል ሂደት ለተሳታፊው በሰፋት አስረድተዋል።

በጉባኤው የመጀመሪያ ቀን ከፓርቲው የሰሜን አሜሪካ ወኪል ከአቶ ፋሲካ በለጠ ንግግር ቀርቧል። በዚሁ የመክፈቻ መልዕክት ባለፉት 25 ዓመታት ፓርቲው ያሳለፋቸውን ተመክሮዎች ዳስሱዋል። ኢህአፓ የተመሰረተው በወቅቱ የነበሩትን የተለያዩ የህዝብ ጥያቄዎች – የመሬት፣ የብሄር፣ የፖለቲካ ስልጣን በህዝብ ቁጥጥር ስር የመሆን ጥያቄን መልስ ለማግኘት የነበረውን አገዛዝ በትግል ለማስወገድ መሆኑ ተገልፁዋል። ኢህአፓ በሂደት ለህዝባዊ ትግሉ በርካታ አስተዋጽኦ ያደረገ ትግሉንም በግምባር ቀደምትነት በመምራት ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለ መሆኑ ተብራርቷል። በትግሉ ሂደት ውስጥ ስህተቶች መፈፀማቸው ግልፅ ቢሆንም እነዚህ ስህተቶች የተፈፀሙት ለሀገርና ለህዝብ ከሚደረግ ትግል እንጅ ከሌላ አለመሆኑን እንዲሁም ስህተቶች ተገምግመው ለህዝብ ግልፅ የተደረጉና እርምጃ የተወሰደባቸው መሆኑ ተብራርቷል። በኢህአፓ ላይ አለአግባብ የሚሰነዘሩ ክሶች ግን መሰረተ–ቢስ መሆናቸው ተጠቁሟል። የወያኔ መንግስት ዘረኛ፣ አምባገነናዊና ጉሰኛ በመሆኑ ኢህአፓ 17 ዓመት የደርግን አምባገነን አገዛዝ እንደታገለው ሁሉ ይህንንም አገዛዝ በመታገል ላይ መሆኑንና ትግሉ በሁለገብ የትግል ስልት በህብረት መካሄድ ያለበት መሆኑ ተገልፆአል። ኢህአፓ አባል የሆነባቸው የህብረት አካሎች ኢ.ድ.ሀ.ቅና ኢ.አ.ግ. ሁለገብ ትግል እያካሄዱ መሆናቸው ተገልፆ የወያኔን አገዛዝ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ መስዋዕትነት ለመገርሰስ ሰፋ ያለ ህብረት ለመመስረት ሁሉም ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ ተላልፎአል።

ከዚህ በሁዋላ የተማሪውን እንቅስቃሴና የኢህአፓ/ሰን ትግል የሚያሳዩና እንዲሁም የአቶ መርሻ ዮሴፍ የእንኳን ደስ አለን ንግግር በቪዲዮ ቀርቧል። በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ ከአቶ ገብሩ ገብረወልድ፣ ከዶ/ር ንጉሴ አየለ፣ ከዶ/ር ፀሀይ ብርሃነስላሴ፣ አቶ ክፍሉ ታደሰ፣ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ፣ አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ፣ ዶ/ር ጳውሎስ ሚልክያስ፣ ዶ/ር ሙሉጌታ ስዩም፣ ዶ/ር ሹመት ሲሻኝ፣ ፕሮፌሰር ቴዎዶር ቬስታል፣ ዶ/ር ሰለሞን ጋሻውና ዶ/ር ዓለም አንተ ገብረስላሴ የጥናትና የምርምር ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጉባቸዋል። ምሁራኑ ያነሱዋቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ።

– ትግሉን የጀመረው ትውልድ ለትግል ያነሳሱትን ነባራዊ ሁኔታዎች የሚጠቁሙ

– የህብረት ትግል ጥያቄ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ጥያቄ ስለመሆኑ

– የፓርቲው በጎ ተግባሮችና የሰራቸው ስህተቶች

– ሴቶች በትግሉ ያላቸው ቦታና በርካታ የኢትዮጵያ ሴቶች ዛሬም ከዳር የቆሙ ስለመሆናቸው

– ኢህአፓ ትግል ስለጀመረበት ታሪካዊ ሁኔታ

– ወያኔ በዘር አድሎአዊነት የአንድን ጉሳ ተጠቃሚነት ስለማስፋፋቱ

– የስደተኛ ወጣቶችና የፖለቲካ ጥገኞች የሚያነሱዋቸው በደሎች ተመሳሳይነት ናቸው።

ተሸንፈናል ወይ? ለሚለው ጥያቄ አልተሸነፍንም በሚለው ቀጥተኛና የማያወላውል መልስ በመስጠት ገለፃቸውን የጀመሩት የፓርቲው መስራችና የአመራር አባል አቶ ኢያሱ አለማየሁ የኢህአፓን አቋምና እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ብዙ ህዝብ በትግሉ ህይወቱን በማጣቱና ኢህአፓ ስልጣን አለመያዙን እንደ ምክንያት በመቁጠር ኢህአፓ በትግሉ እንደተሸነፈ አድርገው የሚያቀርቡ አሉ ይህ ግን ትክክል አይደለም ሲሉ አስረድተዋል። ቀጥለውም ኢህአፓ አልተሸነፈም፣ አሁንም እየታገለ ነው። ሽንፈት የሚመጣው ለወያኔ አጉንብሰን እጃችንን ስንሰጥ ነው ብለዋል። ኢህአፓ ስህተት የፈፀመው ኢትዮጵያን ከመታደግ አንፃር እንጂ የግል ጥቅምን ከማራመድ አንፃር እንዳልሆነ ግልፅ አድርገዋል።

ኢህአፓ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያበረከተውን አስተዋፅኦ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

1. የፖለቲካ ተቋሞች መፍጠር፣ በፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀትና የመታገልን ዘዴ ኢህአፓ አስተምሯል።

2. ጭቁን የህብረተሰብ አባላትን፣ ሰራተኞችን፣ አርሶአደሮችን፣ ሴቶችን ወዘተ ወደ ፖለቲካ እንዲመጡና ለመሰረታዊ የፖለቲካ ለውጥ እንዲታገሉ አድርጓል።

3. ኢህአፓ ኢትዮጵያዊነትን ጠብቋል። ለኢትዮጵያዊነትም ታግሏል። እንደ ወያኔ የሻዕቢያን ቅኝ ግዛት ጥያቄ ቢቀበል ወይም የሱማሌን የግዛት ጥያቄ ቢቀበልና ለባዕድ ኃይሎች ታዛዥ ቢሆን ምናልባትም ስልጣን ይይዝ ነበር። ይህን ባለማድረግ ኢትዮጵያዊነትን ጠብቁዋል። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቃት ሰንዝረውበት ብዙ ጉዳት ደርሶበታል። የኢህአፓ ህብረብሄራዊነት የኢትዮጵያዊነት ምልክት ነው።


አቶ ኢያሱ ወያኔ ጠላት በመሆኑ ልንታገለው ይገባል፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የሙብቱ ባለቤት እስኪሆን ድረስም ኢህአፓ ትግሉን ይቀጥላል ብለዋል። በመጨረሻም ትግሉ በህብረት መካሄድ አለበት፣ ኢህአፓ ለህብረት ትግል ጥረት ያደረገው ገና ሲመሰረት ነው። በተለያየ ወቅትም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ህብረትም ተመክሮ ገብይቶአል ብለው ንግግራቸውን ጨርሰዋል።

እንዲሁም የታወቁ የሀገር ሽማግሌዎች ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌና ዶ/ር ሃብተጊዮርጊስ ቸርነት ፓርቲው ለ25ኛ ዓመት መድረሱን አድንቀው ትግሉ ግቡን እንዲመታ የህብረት ትግልን ሚና አስምረውበታል። ግልፅ መድረክ በተባለው የጥያቄ መልስና አስተያየት ጊዜ ሁለት ሰዓት ቢመደብም የተሳታፊው ብዛት ከቁጥር በመብለጡ ሁሉንም ለማስተናገድ ባይቻልም በርካታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል። በመጨረሻም አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ባደረጉት የመዝጊያ ንግግር ተዛብቶ የቀረበውን የፓርቲ ታሪክ በማስተካከልና ኢ.አ.ግ. እያደረገ ያለውን ትግል ኢትዮጵያውያን እንዲረዱ አበክረው አስገንዝበዋል።

ከተጋበዙ እንግዶችና ድርጅቶች ውስጥ ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ፣ አቶ ዘርኡ ክሽን፣ ህብረ ህዝብ፣ መኢሶንና ታንድ አበረታቺ የድጋፍ መልዕክት አቅርበዋል/ልከዋል።

ከፓርቲው ጋር በምንም ሰንሰለት ያልተያያዙ በርካታ ዜጎች ጉባኤውን በከፍተኛ ስሜት በማድነቃቸው የመሳካቱ ዓይነተኛ ምስክር ነው እንላለን። ኢህአፓ ይህን በዓል ያዘጋጁ የተለያዩ ቅርንጫፎች አባሎችንና ደጋፊዎችን፣ በእንግድነትና በሽማግሌነት የተሳተፉትን፣ ሌሎችንም የረዱንን ሁሉ ከልብ ያመሰግናል። ፓርቲው ከዚህ ጉባኤ የተማረው ታላቅ ትምህርት ለህብረት ግንባር መፈጠርና መጉልበት የሚደረገው ጥረት ይበልጥ መጠናከርና ትግሉም መፋፋም እንዳለበት ነው።

# ከአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ



አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ

*ከ25 ዓመታት በላይ በትግል ላይ ተሳትፈዋል። ኢሀአፓን ከመሠረቱት ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው። ዛሬም በትግል ላይ ናቸው። ስማቸውን ብቻ በሩቅ እንሰማ የነበሩትን አቶ ኢያሱ ዓለማየሁን ስለእሳቸውና ስለኢሀአፓ እንዲነግሩን ቃለ መጠይቅ አቅርበንላቸዋል።*

<u>ላንዳፍታ፣</u>

ስለ ትውልድዎ፤ አስተዳደግዎና ትምህርትዎ እንዲሁም? በኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ውስጥ እንዴትና መቼ ተሳትፎ እንደጀመሩ፤ ስለ ቤተሰብዎና አሁን በምን ስራ ላይ እንዳሉ በመግቢያ መልክ ቢገልጹልን፤

<u>አቶ ኢያሱ፣</u>

በአዲስ አበባ ከተማ ግንቦት 19, 1941 ዓ.ም. ተወለድኩ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በአርበኞች ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በተፈሪ መኮንን ት/ቤት የተማርኩ ሲሆን በአ/አበባ ዩኒቨርስቲ በ1965–1966 በፈረንጆች አቆጣጠር ነበርኩኝ። በተማሪው እንቅስቃሴ ከ1965–1966 ጀምሮ ተሳትፎ አደረግሁ፤ በ1969 (በፈረንጆች) በአይሮፕላን ጠለፋ ወደ ሱዳን ሄድኩ። ጠለፋው የተማሪውን ትግል ለማስተጋባትና ከዚያም ከሀገር ወጥቶ ተደራጅቶ ለትጥቅ ትግሉ ተባብሮ ለመመለስ ነበር።

ባለትዳርና የአንዲት ሴት ልጅ (ፀደይ) አባት ነኝ። አባቴ በልጅነቴ የሞተ ሲሆን ያሳደገችኝ እናቴ ለህዝብ እንዳስብ እንድታገል በቅድሚያ ካስተማሩኝና ከገፋፉኝ አንዷ ናት።

ሥራዬ ከድሮ ጀምሮ የኢሕአፓ ሥራ ነው። መታገል። በትርፍ ጊዜዬ ማለትም ጊዜ ባገኘሁ ጊዜ መጽሐፍት እጽፋለሁ።

<u>ላንዳፍታ፣</u>

ለኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህና ነፃነት ትግል በኢትዮጵያ ተማሪዎች (የቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ) የትግል ታሪክ ተሳትፎዎ ጀምሮ ኢሀአፓ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ የነበሩበትን ሁኔታ ቢገልጹልን።

<u>አቶ ኢያሱ፣</u>

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በመሰረቱ የሕዝብን ብሶትና ጥቅም በማስተጋባት የታገለ ነው። አንዳንዶች ዛሬ ሀቅን ክደው ሊሉ እንደሚሞክሩት በባዕዳን ወይም በገንጣይ ኃይሎች የተፈጠረና የተሾፈረ እንቅስቃሴ አልነበረም። መሬት ለአራሹ፣ ደሀው ይማር፣ የኢምፔሪያሊስታዊ ተፅዕኖ ይወገድ፣ ባህላችን ይከበር፣ የሕዝቦች እኩልነት ይረጋገጥ ወዘተ ሲል የታገለው ወጣት ሀገሩን ከልቡ የወደደና ለሀገሩ ዕድገት ብልጽግናና ደጉን የተመኘ ነበር። የብሔረሰቦችን እኩልነትም ጥያቄ ያነሳው ብዙሀኑን አስተባብሮ ለአንድ ዓላማ ለአንድ ሀገር ለማሰለፍ፣ ለማታገል መመኘቱ ነበር። የተማሪ ትግልና እንቅስቃሴ ሚና ከፓርቲና ከሕዝባዊ የተደራጀ ሁለገብ ትግል ሚና ጋር በሁሉ መልኩ አንድ አለመሆኑ ግልጽ በሆነልን ጊዜ በድርጅት ተደራጅቶ ከተማሪና ምሁር ባሻገር፣ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ አሰባስቦ ማታገል፣ መታገል ያሻል ብለን ባመንበት ወቅት ለዚሁ ተልዕኮ ተግባራዊነት ተሰማራን። በ1961 ዓ.ም. አይሮፕላን ጠልፈን ለመውጣት ስንወስን የተማሪውን ትግል በይፋ አሳውቀን መንግሥትን አጋልጠን ከዚያም በውጭ ሀገር ካሉት ጋራ በማበር ተደራጅተን ወደ ሀገር በአጭር ጊዜ በመመለስ ትጥቅ ትግሉን ለመጀመር ነበር።

አይሮፕላኑን ጠልፈን ከባህር ዳር ሱዳን ገባን። በነሐሴ 1961 በሱዳን ካርቱም ከተማ ለእስር ተዳረግን። የኃ/ስላሴ መንግሥት ሊያስመልሰንና በእጁ ሊያስገባን ብዙ ጣረ። የሱዳን መንግሥትም በራሱ ተነጋግሮ ወደ አልጀሪያ ላከን። አልጀሪያ ደርሰን ሁናቴያችንን ለመረዳት እንደተቻለን በአውሮጳና በአሜሪካ ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ለመገናኘት ጣርን። በሀገር ቤት ከእነዋለልኝ፣ ፀሎተ ሕዝቅያስ፣ ፀጋዬ ገ/መድህን ወዘተ ግኑኝነት ነበረን። ለመደራጀት፣ ፓርቲ ለመመስረት፣ በፓርቲው የሚመራ ትጥቅ ትግል ለመጀመር።

ግን እንዳሰብነው ነገሩ ቀላል አልነበረም። በኃይለሥላሴ መንግሥት ግፊት ከሱዳን ወደ አልጀሪያ ተባረርን። በዚህ ዘረኛ የሰሜን አፍሪካ ሀገርም የመንጓጓዣ፣ የወረቀትና መንቀሳቀሻ ገንዘብ ማግኘት ቀላል አልነበረም። ይባስ ብሎ ደግሞ ለትጥቅ ትግሉ ዝግጁ ይሆናሉ ብለን በገመትናቸው በአሜሪካና በአውሮጳ የነበሩ የተማሪ ማህበራት መሪዎችና ተራማጅ ምሁራን በጠበቅናቸው አልተገኙም። ስለዚህ በራሳችን ጥረት ድርጅት መስርተን ትግሉን ማካሄድ አማራጭ የሌለው ተግባር ሆነ።

<u>ላንዳፍታ፣</u>

የኢሀአፓ መመስረት አስፈላጊነት እንዴት ሊወሰን እንደበቃ ወይም እንደቻለ፣ መስራቾቹ እነማን እንደሆኑ አሁን ከመስራቾቹ ማን በህይወት እንዳለና

እንደሌለ፣ አሁን ማን ተሳትፎ በማድረግ ላይ እንዳለ ቢገልጹልን። እንዲሁም የኢሕአፓ አወቃቀር ፊት የነበረውን አሁን ካለው ጋር በማስተያየት ቢነግሩን። እርስዎ ከመጀመሪያው እስካሁን ድረስ በኢሕአፓ ትግል ውስጥ የነበረዎትን የተሳትፎ ደረጃ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ቢገልጹልን።

አቶ ኢያሱ፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በተደራጀ መልክ መካሄድ መጀመር አለበት ብለን ከወሰንን ጀምሮ ይህንኑ ድርጅት ለመፍጠር ተንቀሳቀስን። ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ ተቋቋመ። በዚህ ጥረት እነ መስፍን ሐብቱ፣ ሱዳን የነበሩ ጓዶች፣ እነ ፀጋዬ ገ/መድህን ነበሩበት። በአልጀሪያ የነበርነው እንደ ማዕከል ሆነን ለድርጅታዊው ጥረት አስተዋጽኦ አድርገናል። ብንያም አዳነን ወደ ሩሲያ ልከን እዚያ የነበሩትን፣ እህቱን ንግስት አዳነን ጭምር አግኝቶና አሳምኖ በሂደቱ እንዲሳተፉ እንዲያደርግ ሞክረን ተሳካ። ገዛኸኝ እንዳለ ለተመሳሳይ ሥራ ወደ ሆላንድ ሄደ። ከዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ በሶማሊያ ከነበረው ከመርሻ ዮሴፍ ጋርም ግንኙነት ተደረገ፣ መልክ ያዘ።

በየቦታው የጥናት ክበቦች ተቋቁመው በመሠረታዊ የፖለቲካና የድርጅት ጥያቄዎች ላይ ያልተቋረጠ ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ ተካሄደ። ከዚህ በኋላ ነው በሚያዝያ 1964 ዓ.ም. የፓርቲ ምስረታው ጉባዔ የተጠናቀቀው። በዚህ መስራች ጉባዔ ላይ ተሳትፈው የነበሩት እነ ብርሃን መስቀል ረዳ፣ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ በሕይወት የሉም። በምሥረታው ጉባዔ ላይ ተገኝተው እስካሁን ኢሕአፓ ሆነው ከቆዩት ውስጥ የቀረሁት እኔ ነኝ። ከምሥረታው እስካሁን በፓርቲ አባልነት የቆዩ ካልን ግን እነ ጓድ መርሻም አሉ።

በኃላፊነት ደረጃ በፓርቲው ፖሊት ቢሮና ማዕከላዊ ኮሚቴ በልዩ ልዩ ዘርፎች ታግያለሁ። በ1976 ሁለተኛ ጉባዔ ላይ ደግሞ በፈቃዴ ከኃላፊነት ቦታ ለቅቄ በአባልነት ደረጃ ፓርቲው በመደበኝ ስሰራ ቆይቼ በቅርቡ ደግሞ እንደገና ወደ አመራር ኃላፊነት ተመርጬ በመታገል ላይ ነኝ። የኢሕአፓ አወቃቀር ሲጀመርና አሁን ተመሳሳይነትና ልዩነትም አለው። በመሰረቱ የሥራ ቅልጥፍናን፣ ስፋትና ጥንካሬን ከምሥጢራዊ አደረጃጀት ጋር ለማቀናጀት፣ ትግሉ የሚጠይቀውን ጥብቅነት ከዲሞክራሲያዊ አሰራር ጋር ለማዛመድ የሚጥር መዋቅር ነው። ከድሮው የሚለየው ሌላ ነገር በተለይ በውጭ ሀገር ያለው መዋቅሩ ከሞላ ጐደል መሆኑና የአመራር አባላቱም ሆነ አባላቱ መታወቃቸው ነው።

ላንዳፍታ፣

በደርግ የመጀመሪያ ዓመታት ኢሕአፓ የደርግን መንግሥት ያንቀጠቀጠ ትልቅ ሕዝባዊ መሠረትና በብዙ አባላት የታቀፈ ድርጅት እንደነበረና ኋላም በቀይ ሽብርና በውስጡም በተፈጠሩ ችግሮች መዳከሙ፣ በኋላ ደግሞ እየጐለበተ መምጣቱ ይነገራል። እስቲ ይህን የታሪክ ሂደት ከእርስዎ አስተያየትና ግምት ጋር አጠር አድርገው አያይዘው ቢያስረዱን።

አቶ ኢያሱ፣

ትግል ውጣ ውረድ አለው። በተመክሮአችን የቀሰምነው ትምህርት ይህ ነው። በመጀመሪያ ዘመናችን አደግን፣ ሰፋን። በኢሕአፓ ስር ተሰልፎ ለዲሞክራሲ የታገለው ሕዝብ በጣም ብዙ ነበር። ወቅቱም የትግል መንፈስ ተጠናክሮ የተነሳሳበት የነፈሰበት ነበር። ደርግ ባወጀብን ሽብር በውስጣችን በተነሱ አንጃዎችና ራሳችንም በፈጸምናቸው ስህተቶች የተነሳ ብዙ ጉዳት ደርሶብን ተዳከምን።

ብንዳከምም ግን ትግሉን አላቋረጥንም። ተሸንፍን በቃ ብለን እጅ አልሰጠንም። በገጠር ትጥቅ ትግሉን ቀጠልን። በዚህም ደግሞ ወያኔና ሻዕቢያ ተባብረው ወጉን፣ ተረባረቡብን። ከትግራይ ለቀን በበጌምድር ተጠቃለልን። ትግሉን አሁንም ቀጠልን እንጂ አልቆምንም። ከዚያም በልዩ ልዩ ምክንያት የመበተን አደጋ ተከስቶ ብዙ የሠራዊታችን አባላትና ካድሬዎች ጥለውን ሄዱ። ወደ ደርግ፣ ወደ ሱዳን፣ ወይ እንደ ታምራት ላይኔ ወደ ወያኔ፤ የቀረነው ደግሞ ተሰባስበን ሁናቴያችንን በረዥም ውይይት ገምግመን ዛሬም አልተሸነፍን ብለን ትጥቅ ትግሉን እንደገና ቀጠልን። ብዙ መከራ አይተን እንደገና ልንጠናከር ልንሰፋ ቻልን። በቋራ መሬት ነፃ ባወጣነው ግዛት ሁለተኛውን የድርጅታችንን ጉባዔ በ1976 ዓ.ም. ለማካሄድ ቻልን። ድርጅታችን እንደገና እየጠነከረ መምጣት ሲጀምርም ወያኔ ሻቢያና የባዕድ ሀገርም ተባብረው እንደገና ወጉን። እንደገና ጉዳት ደረሰብን። አባላትና የአመራር ኮሚቴ ጓዶችም ተሰዉብን ወይም በጠላት እጅ ወድቀው የደረሱበት ጠፋ። መርዘኛ ጠላታችን ሁኖ የቆየው የወያኔ ና የሻዕቢያ ጣምራ ቡድንም በጉልበት ሥልጣን ጨበጠ።

በዚህም ተስፋ ሳንቆርጥ አስፈላጊውን መስዋዕትነት እየከፈልን ትግሉን ለመቀጠል ስንዋደቅ ቆይተን እነሆ ዛሬ በኢትዮጵያ አንድነት ግንባር አማካኝነት ወያኔን በሜዳ በመፋለም ላይ አለን። ካለፈው ተመክሮ ሁሉ በመማርና ቃልኪዳናችንን በማደስ በትግሉ እየገፋን ነው። የሕዝቡ የትግል ዓላማ በርካታ ድሎችን ያስመዘገበ ቢሆንም ገና ከመጨረሻ ግቡ ስላልደረሰ የጀመርነው ትግል ገና አላለቀም።

ላንዳፍታ፣

በትግል ተሳትፎዎ ወቅት ከገጠመዎ ነገሮች ውስጥ አንድ የሚያስገርም፣ አንድ የሚያሳዝን፣ አንድ ደግሞ የሚያስደስት ነገር ቢነግሩን?

አቶ ኢያሱ፣

ከገጠሙኝ ብዙ ነገሮች ሁሉ የመምረጡ ጉዳይ ቀላል አይደለም። ከሚያስገርሙ ነገሮች አንዱ፣ አንድ የቆሰለ ጓድ አንጀቱ ወጥቶ ተዘርግፎ የሕክምና ጓዶች በጥሞና አንጀቱን በኮዳ ውኃ አጥበው ወደ ሆዱ መልሰው ሰፍተውት ጓዱ ጤና ሆኖ ትግል መቀጠሉን ሳስታውስ ነው። በጣም ካሳዘኑኝና ከነኩኝ አንዱ የእነ ፀጋዬ ገ/መድህን በወያኔ እጅ መውደቅና የእነገለብና ኃይሌ መስዋዕትነትና የእነ ቆንጂትና ከሊፋ መሞት ነው። ትግል መከራ ስቃይ ብቻ ሳይሆን ደስታም ነው። ሳቅ፣ ሕይወት፣ ፍቅር። ስለዚህም ብዙ አስደሳች ጊዜዎችን አሳልፌያለሁ። በጣም ካስደሰቱኝ ነገሮች አንዱ ግን ከመካከለኛው ምሥራቅ በተለይም ከቤይሩት (ጦርነት) መሣሪያና ጥይት ሰብስበን ይህንኑ ከብዙ ችግር በኋላ አሲምባ በማድረስ የኃይላችንን ትጥቅ ለማደራጀት በቻልንበት ወቅት ነው። ከብተና በሁዋላም ለሁለተኛ ጉባዔ መብቃታችን የከፍተኛ ደስታ ወቅት ነበር።

ላንዳፍታ፣

ኢሕአፓ ለምሁሩ ክፍል ምን መልዕክት አለው?

ኦቶ ኢያሱ፣

ምሁሩ በሕዝባችን ትግል ሂደት ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ነበረው። በእርግጥ ያኔም ሆነ ዛሬ ሕዝብን ከድተው ለጨቋኝ መንግሥት የሚያድሩና ያደሩ አሉ። ግን ብዙሃኑ ምሁር ሀገር ወዳድ ነው። ስለዚህም በተጨባጭ ሕብረቱን አጠናክሮ የህዝቡን ትግል እንዲደግፍ ማሳሰብ እፈልጋለሁ። በየዘርፉ እያካሄደ ያለውን ጥረት በማስተባበር በተደራጀ መልክ እንዲታገል። ኢሕአፓ በበኩሉ ለምሁሮች የሚስብ የሚመች እንጂ የሚጐረብጥ አልነበረም፣ አይደለምም። እቀፉኝ ደግፉኝ ተባብረን እንታል እንደራጅ እንታገል ይላቸዋል።

ላንዳፍታ፣

በአጠቃላይ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ሊሰጡት የሚፈልጉት ምክር ካለ።

አቶ ኢያሱ፣

ለወጣቱ ትውልድ ያለኝ መልዕክት የተለየ አይደለም። ለወጣቱ ትውልድ የሀገር ፍቅርንና የትግልን ቆራጥነት ስሜት ማስተላለፉ የእኛ ግዴታ ነው። ወጣቱ ደግሞ እያንዳንዱ ትውልድ የራሱ ተልዕኮና ግዳጅ እንዳለው በመረዳትና በመቀበል ሀገራችንን ከጥፋትና ከወያኔ ግንጠላ ለማዳን ተባብሮ መታገል ይጠበቅበታል። ኢሕአፓ የወጣቱ የትግል ድርጅት ነበረ። ዛሬም ነው። የትግል ጥሪም ሲደረግ ይህንኑ እንደገና በማረጋገጥና አብረን ታሪክ እንስራ እያለ ወጣቱን በመጋበዝ ነው።

# የዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ ልጅ ወጣት ሐምራዊት በ25ኛው የኢህአፓ ምስረታ በዓል ላይ ያቀረበችው ጽሁፍ ሙሉ ቃል



በቅድሚያ አክብራችሁ በዚህ ታሪካዊ ዝግጅት ላይ እንድቀርብ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ። ለማህበራዊ ፍትህ ሲታገሉ የተሰዉትን የኢትዮጵያ ወጣቶችን ለማክበርና ለማስታወስ በሚል የተሰየመውን ጉባኤ በማዘጋጀታችሁና ለዛሬ ወጣቶች ተሳትፎ ያላችሁን ምኞት በማሳየት የእኛውንም ተስፋ በማሳደሳችሁ በእኔና በወጣቶች ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ውድ የዚህ ታላቅ ጉባኤ ተሳታፊዎች፣ አገራችን በአሁኑ ጊዜ ችግር ላይ ነች። ችግር ስንል ደግሞ ቀላልና ኃላፊ ችግር ማለት አይደለም። በዘር በጐሳ የመጣ ችግር ተዛማች፣ ከትውልድ ትውልድ ቆይ፣ አገር አጥፊ አንደኛው ጠላት መሆኑ ድብቅ አይደለም። የጠላቶቻችን ምኞት ተሳክቶ አንዴ ህዝቡ መሃል የጐሰኝነት፣ ግለኝነት እስተሳሰብ ከገባ የማያልቅ፣ አገርን የሚያጠፋ፣ የእርስ በእርስ ጥላቻ የሚያሰፍን ትልቅ አደጋ ያዘለ የፖለቲካ ክስተት መፈጠሩ አይቀርም። ይህንን ችግር ለማጥፋት አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ወላሞ፣ ወጣት ሽማግሌ፣ ሴት ወንድ ሳይባል ሁሉም ተባብሮ መስራት አለበት። ይሄ ችግር ወደ ዋናው ነጥቤ ያመጣኛል። የኢትዮጵያን የወደፊት እጣዋን ለማወቅ ስትፈልጉ አይናችሁን ወደኛው ወደ ልጆቻችሁ ብታዞሩ መልሱን ታገኛላችሁ።

አባቶቼ እናቶቼ እስቲ ራሳችሁን ጠይቁ። በአሁኑ ጊዜ ያለነው ወጣቶች የወደፊቷን ኢትዮጵያ ለመረከብ ዝግጁ ነን ወይ? እናንተ በእኛ እድሜ እያላችሁ ከነበራችሁ ሁኔታ በምን እንለያለን? ይህ ጥያቄ በሁላችሁም አይምሮ ውስጥ ሊጉላላ ይገባል። ይህን ጥያቄ ራሳችሁን ስትጠይቁ የምታገኙት መልስ ልባችሁን በደስታ ባያሞቀው ተስፋ አትቁረጡ። የፈለጋችሁትን መልስ ባታገኙ ልባችሁ አይሰበር፣ እንደፈለጋችሁት ልንሆን ባንችል አንገታችሁ አይቀርቀር። አይዟችሁ መንገድ የሳትን መስሏችሁ አትዘኑ።

“ድሀ እድለቢሶች ብንባል ሳናፍር ሌላው ቢቀር የጀግኖች፣ የእውነተኞች ልጆች ነን እንድንል ሁኑልን–የአባቶቻችሁ የተሰዉትና እየተሰዉ ያሉት ጓደኞቻችሁ አደራ አለባችሁና። ከሁሉ በላይ ደግሞ ከየት ናችሁ ስንባል ሳናፍር በኩራት ፊታችንን ፈገግ አንገታችንን ቀና አድርገን ከኢትዮጵያ እንድንል እርዱን! . . .”

ወጣት ሃምራዊት ተስፋዬ ደበሳይ

ከእናንተው አብራክ የወጣን ልጆቻችሁ ነን። የእናንተው ደም ደማችን ውስጥ ያለ፣ ብዙዎቻችን አገራችንን ከልባችን እንወዳለን። ፍቅራችንን እንዴት አድርገን እንደምንገልፅ ጨንቆን እንጂ! አገራችንን እንዴት እንደምናድን መላው ጠፍቶን እንጂ!

እንደምታውቁት ከሆነ በተለይ በደርግ ጊዜ ያደግነው ወጣቶች ብዙ ያጣነው ነገር አለ። መሪዎቻችን ሊሆኑ የሚገባቸው ሰዎች አይናቸውን አፍጥጠው ሙልጭ ያሉ ውሸት ሲዋሹን፣ በቴሌቭዥንና በሬዲዮ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆችን እንድንጠላ ሲሰብኩን፣ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ሲሉ የተዋደቁትን እናትና አባቶቻችንን እንድንፈራና እንድንጠላ ሲያስገድዱን፣ እኛ እንድንኖር

ብለው እነሱ የሞቱልንን እንድንጠላና እንድናይ ሲነግሩን አድገናል። ለህዝቤ ብሎ የሚዋደቀው፣ ለአገሩ የሚዋጋው፣ ለእውነት የቆመው ሁላ መጨረሻው ሳያምር ቤተሰቡ ተበታትኖ እስር ቤት ሲወረወር እያየን አድገናል። የእናንተን ትግል እንድምትፈልጉት ባናደንቅ አትፍረዱብን—የብዙ ደግ አሳቢዎች ታጋዮች መጨረሻ ሳያምር አይተናልና። የምትሉትን ለማመን ቢያቅተን ወይ ጊዜ ቢፈጅብን አትጥሉን—ያመንነው ሲከዳን አይተናልና። የአገራችን የወደፊት እጣዋ ጨለማ ቢሆንም አይግረማችሁ። ተስፋ የቆረጥን ብንመስል አትናቁን—በተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ተከበን ኖረናል። እውነትን እንድንሸሽ፣ አገርን እንድንጠላ፣ ለባለጊዜው እንድናጉበድድ፣ ጉሰኞች እንድንሆን ብዙ ተሞክሯል።

ሆኖም ሆኖም እኛ የእናንተ ልጆች አሻፈረኝ እምቢየው ብለን እዚህ ደርሰናል። የተሰቃየባትን፣ እየተጨቆነ ያደገባትን አገር እያስታወሰ ሰላማዊ ሰልፍ አለ በተባለ ቁጥር ከፊት ተሰልፎ ኢትዮጵያዬ እያለ የሚያለቅሰው ወጣት አገሩን ቢጠላ ነውን? ተንቆ የተባረረባትን፣ እንደ እንጀራ እናቱ እንዲያያት ተገዶ ያደገባትን አገር መኪናው ላይ ለጥፎ «I Love Ethiopia» እያለ የሚዞረው ወጣት ያችን አገሩን ቢረሳ ነውን? ሁለት ሶስት ስራ ደም ተፉቶ እየሰራ በማንም እየተናቀ ያገኘውን ገንዘቡን ኢትዮጵያን ለሚደግፍ ለመሰሉት ድርጅቶች የሚያዋጣው ወጣት ገንዘብ በዝቶበት ነውን? አገርህ ድሀ ነች አገረ ቢስ ነህ ሲባል ስሜቱ አንተክትኮት ካልተደባደብኩ የሚለው ወጣትስ መደባደብ አምሮት ነውን? አገርህ ልትከፋፈል ነው ሲሉት ሆድ ብሶት ያቺን የቀረችኝን ኩራቴን ላጣ ነው ብሎ አንድ ኢትዮጵያ የሚል ካናቴራ ላገር እያስጉበኘ የሚዞረው ወጣትስ የደርግ ቃል አቀባይ ሆኖ ነውን? አይምሰላችሁ እናቶቼ አባቶቼ ወጣቱስ አገሩን ይወዳል። የአገር ማዳኛ ዘዴው መላው ጠፍቶት እንጂ። ማንን አምኖ ማንን እንደሚጠረጥር ማወቅ ተስኖት እንጂ። ወደላይ አይቶ ከእርሱ ከፍ አርጎ የሚያያቸው በእድሜና በልምድ ከሱ የሚልቁት ሊከተላቸው የሚገባቸው እርስ በእርሳቸው ሲከፋፈሉ ሲወነጃጀሉ ሲያይ እሱም መጨመር ፈርቶ እንጂ። ወጣቱስ አገሩን ይወዳል። አሰባሳቢ፣ መሪ፣ አይዞህ ባይ፣ አበራታች ሳያገኝ ቀርቶ እንጂ። አገር እያቋረጠ እግር ኳስ ለማየት የሚመጣው ወጣት ትንሽ ገንዘብ ከፍሎ የፈለገውን አይነት ስፖርት በያለበት ማየት ይችል ነበር። የአገር የወገኑ ፍቅር ቢኖርበት ነው አገር አቋርጦ የመጣው።

እናቶቼ አባቶቼ ወጣቱ ለምን እኛ በእርሱ እድሜ እያለን እንደነበርነው አልሆነም በማለት ፉንታ እንዴት አድርገን ነው ይህንን ተስፋ የሚያሳየውን የወጣቱን የአገር የወገን ፍቅር ከፍ ልናደርግለት የምንችለው ብትሉ ትልቅ ውጤት ታገኛላችሁ። ወጣቱን ከራሳችሁ ጋር አታስተያዩት። ለምን እንደኛ አልሆንክም አትበሉት። ራሱ ያደገበትና ያለፈበት ሁኔታ ከእናንተው በጣም ይለያያልና። ማለት የሚገባችሁ «እንደዛ በተኮላሸ ስርዓት አድጐ አሁንም ህዝቡን ይወዳል፣ እንደዛ ተሰቃይቶ አሁንም አገሩን ይወዳል። እኛ ስለሀገራችን የተማርነውን ቢማርማ፣ እኛ ያገኘነውን እድል ቢያገኝማ እንዴት ሊሆን ነው?» ብላችሁ ራሳችሁን መጠየቅ አለባችሁ። ነገር ግን «ሂዱ ወደዚያ የታባታችሁ» ብትሉን ያው ደርግ ሲነግረን የነበረው እውነት መሆኑን አምነን ወደ ፈረንጆች ባህል መግባታችን ነው።

ውሀ ውስጥ ገብተን የሚፍጨረጨረው እጃችንን ያዙት፣ ራሳችን ከመጥለቃችን በፊት አድኑን፣ ኢትዮጵያዊ መሆናችንን ማስታወቂያው መልካችን ብቻ ከመሆኑ በፊት ድረሱልን።

እናቶቼ አባቶቼ በቃኝ ደከመኝ፣ የምችለውን ሞክርኩ ብላችሁ ተስፋ አትቁረጡ። የሚረከበኝ የለም ብላችሁ አታውሩ። ከማንኛውም ጊዜ በላይ አገራችሁን ልትጠቅሙ የምትችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ደርግ ላያችን ላይ የተበተበውን ገመድ እንድትበጥሱልን ከማንኛውም ጊዜ በላይ ኢትዮጵያ ትፈልጋችኋለች። እኛ ልጆቻችሁ እየጠበቅን ነው እስክትጠሩን ድረስ—ሀሳባችንን ሳትንቅፉ በጉሳችን ሳትከፋፍሉን፣ ውሸት ሳትዋሹን፣ እስክትቀበሉን ድረስ። እስኪ አስተምሩን—ድሮ ያላወቅነውን፣ መልሱልን—ድሮ የተወሰደብንን ተስፋችንን። ለእውነት ስለ እውነት የቆማችሁ ኢትዮጵያውያኖች እንዳላችሁ እንድናምን እርዱን። ስልጣኔ ማለት አገርን መጥላት የሌላውን መመኘት ማለት አለመሆኑን አስረዱን። ኢትዮጵያዊ ማለት እድለ ቢስ ማለት እንዳልሆነ አስተምሩን። እናትና አባቶቻችን በአፋቸው የተናገሩትን በተግባር ያደርጋሉ ብለን የእናንተን ምሳሌ ለመከተል እንድንችል ሁኑልን። የጀግኖችን እግር ለመከተል የተዘጋጁ ግን አቅጣጫ የጠፋቸው ብዙ እግሮች አሉ—ምሯቸው ያ ስናድግ ስለእናንተ የሰማነው ሁሉ ውሸት መሆኑን አሳምኑን። ደርግ እንደነገረን ሳይሆን ትልቅ ደረጃ የመድረስ እድል እንዳለን አሳዩን። በተለይ ከአዲስ አበባ በቀጥታ ትላልቅ ከተማ ለመጣነው ወጣቶች የአሜሪካ አገር እጣ ሁለት ሶስት ስራ እየሰሩ ኑሮ ጠብ ሳይል መኖር ብቻ እንዳልሆነ ንገሩን። የትምህርት እድል እንዳለን ንገሩን። በተለይ ለትምህርት ቤት አመቺ በሆኑ ስቴቶች ውስጥ የምትኖሩ እናትና አባቶቻችን ለአንድ ለሁለት ሶስት ቀን መተን እንድናያችሁ ጋብዛችሁ ትምህርት ቤት የት እንዳለ አሳይታችሁ፣ ጥሩ ቤት እንዴት ልናገኝ እንደምንችል፣ ፋይናንሽያል ኤድ እንዴት እንደምናገኝ፣ አንዳንድ ችግር በትምህርታችን ቢደርስብን ልትረዱን ልታስረዱን ፈቃደኛ መሆናችሁን አሳዩን። አንዴ እኛ ትምህርት ቤት መጥተን ከጀመርን ጓደኞቻችን ደግሞ የእኛን አርአያ ተከትለው ይከተሉናል። ብዙ አንፈልግም የትምህርት ገንዘቡን መንግስት ይከፍላል። የቤት ኪራዩን ራሳችን እንከፍላለን—አይዟችሁ አለን ባይነታችሁን አባታዊና እናታዊ ምክራችሁንና ተምሳሌነታችሁን እንጂ።

እናቶቼ አባቶቼ፣ ከእናንተ በኋላ ያለው ትውልድ ለአደጋ የተጋለጠው የመጀመሪያው ትውልድ ነው—በተለይ በውጭ አገር ያለው። እናንተ ስትመጡ ብዙዎቻችሁ ከፊታችሁ ብሩህ ተስፋ አይታችሁ ነው። አገራችሁ የመመለሱን ምኞት በልባችሁ አሳድራችሁ፣ ሌላው ቢቀር ስለማንነታችሁ፣ ስለታሪካችሁ፣ ባህላችሁ ጉዳይ ጥያቄ ሳይኖራችሁ ነው። በሌላው መልኩ ከእናንተ መሃል የመጣው ትውልድ አብዛኛው ተስፋ ቆርጦ የመጣ ነው። ከአገሩ የወጣው ተምሮ ነው። ምርጫ አጥቶ ነው። እናንተ የነበራችሁ አቅጣጫ እኛ የለንም። ይሄን ትውልድ ለማዳን ዛሬ ነገ መባል የለበትም። ያ ትናንትና ስብሰባ ላይ ያሳፈራችሁን ሰውዬ እናንተም በተራችሁ ለማሳፈር ወይም ስለዛ ሰውዬ የአነጋገር ስልት ለመተቸት ጊዜ አላችሁ። እኛን ልጆቻችሁን የማዳኛው ጊዜ ግን እያለፈ ነው።

ከጠላታችሁ ጋር ያላችሁን ጦርነት ብታሸንፉ የወጣቱን ልብ ካላሸነፋችሁ አሸነፍን ልትሉ ነውን? ያሸነፋችሁትን ድል ከማን ጋር ልትካፈሉ ነው? ለማን ልታስረክቡ ነው? መቼም ዓላማችሁን፣ ባህላችሁን፣ ጀግንነታችሁን፣ አገር ወዳድነታችሁን አብራችሁ ይዛችሁ አትቀበሩ! እናቶቼ አባቶቼ የዛሬውን አትዩ። ለዚች ዛሬ ለምትሯሯጡላት አገራችሁ ነገ ኃይሉ አይኖራችሁም። እኛ እስክናልፍ ድረስ ለፍተንላት ካለፍን በኋላ ኢትዮጵያ ብቻዋን ትቅር እንደማትሉ እተማመናለሁ። ወጣቱ ምን ያህል አገሩን ቢወድ፣ ባህሉን ቢያከብር፣ ትምህርቱን ካልተማረ እንዴት አድርጐ ነው ለአገሩ ገንዘብ የሚያዋጣ? እንዴት አድርጐ ነው የአገሩን ስም የሚያስነሳ? እንዴት አድርጐ ነው የ«C.I.A.»ን ተንኮል የሚደርስበት? በሌላው በኩል ደግሞ ወጣቱ ምንስ ቢማርና ገንዘብ ቢኖረው ወጣቱ ባህሉን ካልተማረ፣ አገሩን ካላወቀ፣ እንዴት አድርጐ ነው ላገሩ አንድ ሳንቲም እንኳ የማውጣት ፍላጐት የሚያድርበት። እናቶቼ አባቶቼ ስለዚህ ወጣቱ ትምህርቱን እንዲማርና ባህሉን እንዲያውቅ መታገል አለባችሁ። አንዴ ወጣቱን ማዳኛ ጊዜ ካለፈና ወጣቱ ተስፋ አጥቶ የሌላውን መሆን ከመረጠ ወዲያ እዩዩ ቢባል ለእምዩ የሚደርስላት አይኖርም።

ውሀ ውስጥ ገብተን የሚፍጨረጨረውን እጃችንን ያዙት። ካለ አባት እናት አሜሪካ በልጅነታችን መተን በአሜሪካው አሳሳች ባህልና በእኛው በምርጡ ባህል መሀል መወሰን አቅቶን የደርግ አንሶን ፈረንጅ የመጨረሻ ድሀ ናችሁ፣ ራሳችሁን ጥሉ እያለን የምንታገል ብዙ ወጣቶች አለን–አስተምሩን– ድሀ ብንሆን የታሪክ ሀብታም እንደሆንን–ድርቅ ቢያጠቃን በባህላችን አለምን እንደምናስንቅ አስረዱን። ዶክተሮች ሳይንቲስቶች ብዙ ባይኖሩን የኮሩ ምርጥ ጀግና የጀግና ልጆች እንዳሉን ንገሩን። የውጭ አገሮቹ ጉራ ሲነዙብን እኛም በተራችን የምንለውን አስተምሩን። ምን አባታችሁ ሂዱ ወዲያ ብትሉን እጁን ዘርግቶ ወደሚጠብቀን ወደ አሰቃቂው ባህል ነው የምትገፉን። ውዱን እውቀታችሁን አገራችሁ ሄዳችሁ ከአገራችሁ ህዝብ ጋር መካፈል ባትችሉ ከአገራችሁ አብራክ ከወጣነው ከእኛው ከልጆቻችሁ ጋር ተካፈሉት–ወደፊት እኛም አገራችን ተመልሰን እውቀታችሁን እንድናንፀባርቅ ይሆናልና። ወጣቱ አምኗችሁ፣ አክብሯችሁ፣ እናንተ የደረሳችሁበትና ከዛም በላይ ለመድረስ እንዲጥር አድርጉ።

ያኔ ነው እናቶቼ አባቶቼ፣ ያኔ ነው ጦርነቱን የምታሸንፉ፣ ድል የምታደርጉ፣ ልባችሁ በተስፋ ሞቆ አይናችሁ በኩራት በርቶ እልል የምትሉ። ያኔ ነው አይናችሁን ሀፍረት ሳይሰብረው ቀና ብላችሁ «አይዞሽ ኢትዮጵያዩ እኔ ባልፍ ቅር አይበልሽ–ልክ እንደእኔ ሆኖ የሚያስብልሽ ልጅ ተካሁልሽ የምትሉ»–ያኔ ነው የጐነበሰውን አንገታችሁን አንቅታችሁ ለጠላት «ምን አባክ የኢትዮጵያ ልጆች ብናጐነብስ አልወደቅንም። እኔ ብሄድ ልክ እንደእኔ ሆኖ ያሰብኩትን አሳክቶ፣ የሚያኮራኝ፣ የአገሬን ህዝብና አገሬን የሚጠብቅልኝ ልጅ አገኘሁና ደስ አይበልህ የምትሉ።» ብቻዬን መስዬህ ስትስቅ ደሜን የሚተኩ ልጆች እንዳሉኝ በል ተዋወቅ ብላችሁ ለጠላት የምትናገሩ። ያኔ ነው ታሪካችሁ በእኛ የሚወራ፣ ያነባችሁት እንባ የሚደርቅ፣ ድሉ የናንተ የሚሆነው ያኔ ነው። እኛ ልጆቻችሁ የአገራችንን ምንነት ስናውቅ፣ ዶክተር ሆነን ኢትዮጵያን ስንጠግን፣ ጠበቃ ሆነን ለኢትዮጵያ ህዝብ ስንከራከር፣ ታሪክ አጥንተን የአገራችንን ስም አጉዳፊውን አፍ ስናስይዝ–ያኔ ነው ቀኑ የድላችሁ እልል የማያችሁ።

ስራው ቀላል አይደለም። ህይወቱን በሙሉ በደርግ ውሸት ሲደበደብ የኖረው ወጣት ትዕግስት ይፈልጋል። ግን ደግሞ ተስፋ ሊሰጣችሁ የሚገባው ነገር አለ። እንደዛ በውሸት ተቀጥቅጦ፣ በአታላይነት ተገዝቶ፣ ተስፋ አጥቶ ያደገው ወጣት ሰው አገር መጥቶ ማንም ሳይረዳው ብቻውን ወንጀል ውስጥ ሳይገባ አገሩን አስከብሮ ሁለት ሶስት ስራ እየሰራ በሠላም ለመኖር እንደሚጥር ድብቅ አይደለም። ይህ ትውልድ በራሱ ተፈራግጦ፣ በድካሙ፣ በትዕግስት፣ ኑሮን ለማሸነፍ የሚጥር ትውልድ ነው። ይሄ ወጣቱ ላይ የሚታየው ትዕግስተኛነትና መጣጣር ተስፋ ሊሰጣችሁ ይገባል። አብዛኛው ጐበዝ ነው። ተጣጣሪ፣ ታማኝ፣ ለነገው አሳቢ፣ አገሩን ወዳድ፣ ብልጥ ነው። የእናንተ ተግባር ሊሆን የሚገባው ለዚህ ወጣት የወደፊት ህይወት ብሩህ ተስፋ መስጠት ነው። አይዟችሁ፣ ተማሩ ባይ፣ የትምህርትን ጥቅም አስታዋሽ፣ እንፈልጋለን። ከእናንተ በኩል ብዙ ጥረትና ትዕግስትን እንጠይቅ ይሆናል።

ግን፣ ግን እንኳን ይቺን ቀርቶ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ሌላስ ሰርተን የለ? እኛ የነአሉላ አባ ነጋ፣ ባልቻ አባ ነፍሶ፣ ቴዎድሮስ፣ ምኒሊክ ልጆች፣ በትዕግስታችን፣ አርቆ አሳቢነታችን ጀግንነታችን አለምን አስገርመን የለ? እንኳን ይችንና ሌላም አርገናል።

የአርበኞች ልጆች ሆይ አሁንም ያንን ወኔ ያችሁን ይዛችሁ እኛን ልጆቻችሁን ከአደጋ አውጡን።

የራሳችንን አክብረን፣ የሌላውን ንቀን፣ ከጥፋታችሁ ተምረን፣ በጥሩ ስራችሁ ኮርተን፣ አገራችንን እንድናለማ እርዱን። በልባችን ውስጥ የሚንተከተከውን የአገር ፍቅር ስሜት ለማንፀባረቅ እንድንችል አግዙን። አይዟችሁ፣ አለን፣ የእኛው ናችሁ በሉን። እርስ በእርስ የተጣላን ቢመስላችሁ እውነት አይደለም ለቅጥፈት የቆምን መስሏችሁ አትሳሳቱ። ለእውነት ለፍትህ፣ ለብሄር እኩልነት ነው የቆምነው በሉን። ከእናንተ የተለየ ሃሳብ ቢኖረን አትራቁን። ተስፋችንን አለምልሙት። ለነገ አዘጋጁን፣ በደርግ የቆሰለውን ቁስላችን ሌላ ዝንብ ሳይበላው በፊት ጠግኑልን። የአገራችንን ጥሪ ስንሰማ እንድንሮጥ ደግፉን። ከአሜሪካው አሳሳች ባህል አድኑን። በDrug ፋንታ መፅሀፍ፣ በዝሙት ፋንታ ትምህርት እንድንመርጥ አበረታቱን። ድሀ እድለቢሶች ብንባል ሳናፍር ሌላው ቢቀር የጀግኖች፣ የእውነተኞች ልጆች ነን እንድንል ሁኑልን–የአባቶቻችሁ የተሰዉትና እየተሰዉ ያሉት ጓደኞቻችሁ አደራ አለባችሁና። ከሁሉ በላይ ደግሞ ከየት ናችሁ ስንባል ሳናፍር በኩራት ፊታችንን ፈገግ አንገታችንን ቀና አድርገን ከኢትዮጵያ እንድንል እርዱን! የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል! ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች! አመሰግናለሁ

ሒምራዊት ተስፋዬ

# ለአርቲስት አስቴር አወቀ የቀረበ ቃለ መጠይቅ

## ከላንዳፍታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል



"ሀገር ሀገር ሀገር ይላል ይህ ሀገረ ብርቁ፤
እኔም ሀገር አለኝ የሚታይ በሩቁ፤"

ባለፈው እትማችን እንደገለጽነው ከጥቂት ወራት በፊት ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኋላ ወደ አገሯ ሄዳ ትርኢቶች በማሳየቷ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ተቃውሞዎች የደረሰባት መሆኑን በማውሳት ይህንን በተመለከተ በበኩሏ የምትለውን ለመስማት እንድንችል ታዋቂዋን አርቲስት አስቴር አወቀን ይህን ቃለመጠይቅ አቅርበንላታል።

ጎንደር ተወልዳ አዲስ አበባ ያደገችው አስቴር አወቀ አዲስ አበባ ፈለገ ዮርዳኖስ ት. ቤት ተማሪ ሆና፤ ከዚያም በአገር ፍቅር ማህበር ተቀጥራ ለ1 ዓመት 3 ወር በመሥራት፤ ኋላም በዲ አፍሪክና ዋቢ ሸበሌ ሆቴሎች ከዚያም ወደ አሜሪካ በመምጣት ዝና ለማትረፍና በዐለም አቀፍ ደረጃ ለመታወቅ በቅታለች።

አስቴር ከ16 ዓመታት የውጭ አገር ቆይታ በኋላ ወደ አገር ቤት በመሄድ ትርኢቶቿን በማቅረቧ አገር ቤትም ሆነ እዚህ ውጭ አገር የተለያዩ ተቃውሞዎች ተሰምተውባታል። የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን እነኝህን የተወራባትን ጥያቄዎች በማንሣት በበኩሏ የምትለውን መልስ ያቀርባል።

**ላንዳፍታ፣**
ከብዙ ዓመታት የውጪ ኑሮ ቆይታሽ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በቅርቡ ሄደሽ ነበረ። ስለ አካሄድሽ ትንሽ ብትገልጪልን። ለመሄድ ምን አነሳሳሽ? መቼ ሄድሽ? ምን ያህል ቆየሽ?

**አስቴር፣**
አዎ ብዙ አመታት በጠቅላላው 16 ዓመታት ያህል ከሀገር፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ እጅግም ከምንነፋፈቀው ከሙዚቃ አፍቃሪዬ ህዝብ ጋር ተለያይቶ እንኳንስ ይህን ያህል ጊዜ ቀርቶ መንፈቅና አመት ቢለዩት እንኳ ምን ያህል ይናፍቃል? የሁልጊዜ ምኞቴ አንድ ቀን ተሳክቶልኝ ሃገሬ ገብቼ ልብ ለልብ ከምንግባባው የሙዚቃ ወዳጆቼ ፊት ቆሜ መነጋገርና ማዜም ምኞቴ ነበርና፤ ተሳክቶልኝ ሄድኩኝ። ደስታዬ ይኸ ነው ብዬ ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል። የፍቅር፣ የርህራሄ፣ የጨዋነት ጌታና ሐብታም የሆነው ህዝብ ፍቅርን አስተምረውኝና አከናንበውኝ ነው የተመለስኩት። አዲስ አበባ የገባሁት እንደ እኛ አቆጣጠር ታህሳስ 17, 1989 ዓ.ም. በፈረንጆች ገና ማግስት ሲሆን ቆይታዬም ለሁለት ወራት ያህል ነበር።

**ላንዳፍታ፣**
ቀደም ሲል ሳትሄጂ ቆይተሽ ይህን ጊዜ ለምን መረጥሽ? በተጨማሪ ከዚህ በፊት ኬንያ–ናይሮቢ ለሙዚቃ ዝግጅት በሄድሽበት ጊዜ አዲስ አበባ ሳትደርሺ በመመለስሽ በወቅቱ ብዙ ኢትዮጵያውያኖችን ቅር አሰኝቶ ነበር። የዛኔ እግረ መንገድሽን አገርሽን ለማየት ያልቻልሽበት ምክንያት ነበረሽ?

**አስቴር፣**
ቀደም ሲል ያልሄድኩበት ምክንያት እንደ ብዙ ወገኖቼ በተሰማራሁበት ስራ እኔም ብዙ ጥሬና ገፍቼ ኑሮዬን አሻሽዬ በሙያዬም አጥጋቢ ደረጃ ደርሼ ማለትም ቋንቋዬን፣ ባህሌን፣ ሙዚቃዬን የማያውቁ ህዝብ ፊት ቆሜ የኢትዮጵያም ሙዚቃ እንደዚህ ቆንጆ ነው ከሚለው ህልሜ ጋር ብዙ ውጣ ውረድ ነበረብኝ። እንደምንም ብዬም እዚያች መድረክ ላይ ለመቆም በቅቻለሁ።

ወደ ኬንያ ናይሮቢ የሄድኩት በፈረንጆች አቆጣጠር ጁን 1993 ነው። ምክንያቱ ኡርቱና (URTNA) የሚባል የሬዲዮን የቴሌቪዥን ብሮድካስት ድርጅት 48 የአፍሪካ አገሮችንና አብረዋቸው የሚሰሩ የመካከለኛው ምስራቅና አውሮፓ አገሮችን የሚወክል ማህበር የተቋቋመበትን 30ኛ ዓመት በሚያከብርበት በዓል ከየአህጉሩ የተውጣጡ ብዙ አርቲስቶች ባሉበት እኔም ሀገሬ ኢትዮጵያን ወክዬ እንድቀርብ በቀረበልኝ ግብዣ መሰረት ነው።

አዎን ብዙ ኢትዮጵያውያን ኬንያ ደርሼ ኢትዮጵያ ብቅ ብዬ ትርዒት ሳላሳይ በመመለሴ ቅር እንደተሰኙ ሰምቻለሁ። ነገር ግን የኬንያው በዓል የተዘጋጀው ጁን 27, 1993 ሲሆን በጁላይ 4, 1993 በካሊፎርኒያ ኦክላንድ የ10ኛው የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ጨዋታ በዓል ይከበር ስለነበረና በዚያው ቀን ማለትም በጁላይ 4, 1993 እኔም የነፃ አገልግሎት ለመስጠት ከፌዴሬሽኑ ጋር ስምምነት ነበረኝ። እንግዲህ ከኬንያ እስከ ካሊፎርኒያ ያለው ጉዞ ጊዜዬን ሊጨርሰው ሆነ። ያም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በየከተማው እየተዘዋወርኩ እንደምሰራው ማታ ገብቼ ጠዋት የምወጣበት፣ እንደ ኬንያ ሁለት ዘፈን ብቻ ተጫውቼ የምወጣበት፣ ኢትዮጵያ እናቴን ብቻ ስሜ የምወጣበት አገር አይደለም። ኢትዮጵያ ወዲያ ወዲህ ተብሎ ዘመድ የሚጠየቅበት፣ ቤተክርስቲያን የሚሳለሙበትና ለብዙ ነገር ሰፋ ያለ ጊዜ የሚያስፈልገው በመሆኑ ጭምር ነበር። የዛኔ ገብቼ ቢሆን ኖሮ የእኔን ትርዒት ይጠብቁ የነበሩ ወገኖቼም ቅር የሚሰኙበት ሁኔታ ይፈጠር እንደነበር አልጠራጠርም።

እንዲሁም በብዙ ዝግጅት ከ5 ሰዓት ያላነሰ ጊዜ የሚፈጅ ትርዒት መቅረብ ያለበት ነው። አንድ ጊዜ ሳይሆንም በርከት ያለ ጊዜ ለሁሉም አፍቃሪዬ እንዲደርስ መሆን አለበት የሚል እምነት ነበረኝ።

የሚገርመው ነገር ከኬንያ ከተመለስኩ በኋላ «አስቴር ኬንያ ድረስ ሄዳ ኬንያ ተጫውታ አገሯ ሳትደርስ ተመለሰች። ይህ ላገሯ ህዝብ ያላትን ንቀትና ግድ እንደሌላት ያሳያል።» እያሉ በስም ማጥፋት ዘመቻ የተሰማሩ ሰዎች ናቸው አሁን ተገልብጠው ሀገሬ ገብቼ ያለኝን ፍቅርና ናፍቆት ከሀገሬ ህዝብ ጋር አይን ለዓይን ተያይተን እስከዛሬ ድረስ ላሳዩኝ ፍቅርና ክብር ምስጋናዬን በቃልና በእንጉርጉሮ ተወጥቼው በመምጣቴ ባልዋልኩበት የሚወቅሱኝ፣ እነዚያው ለምን የዛኔ አልገባችም የሚሉት ናቸው።

ላንዳፍታ፣
በአሁኑ ጉዞሽ ኢትዮጵያ ስትሄጂ የህዝቡን አቀባበል እንዴት አገኘሽው? ስንት ትርዒት አቀረብሽ? በየክፍላተ ሃገርስ ትርኢት አሳይተሻል ወይ?

አስቴር፣
የህዝቡ አቀባበል ፍፁም ከጠበቅኩትና ካለምኩት በላይ ነበር። ከዚህ የለቀቅሁት ቅድም እንዳልኩት በፈረንጆች ገና ማግስት ነበር። የሀገሬን ምድር የምረግጥበት ጊዜ እየቀረበ በሄደ ቁጥር ሰዓቱና ደቂቃው ይረዝምብኝ ጀመር። ከመብረሬ አንድ ሁለት ቀን ሲቀረው ነው የእንቅልፍ ድራሹ የጠፋው። አይ ግድ የለም አውሮፕላኑ ላይ ስወጣ ይለቀኝና እዚያ ላይ አሸልባለሁ ብልም አይኔ ፍጥጥ እንዳለ አዲስ አበባ ገባሁ። ገና ወርጄ ተርሚናል ውስጥ ስገባ ከየት መጡ ሳልል የአየር መንገድ ሰራተኞች መሆን አለባቸው ግር ብለው መጥተው ሳሙኝ። ፊርማም መጠየቅ ተጀመረ። ወደዚያ ወደዚህ ስል የፈረምኩትንም ሳላውቀው እንደምንም ወደ ውጪ ስወጣ የዚያ ሁሉ ወጣት ጩኸትና እልልታ፣ በትልቅ ጨርቅ ላይ «አስቴር እንወድሻለን»፣ ያ ሁሉ ፍቅር፣ ደስታዬን መቆጣጠር አቅቶኝ የደስታ እንባ ይወርደኝ ጀመር። ደስታም እንደ ሀዘን በእንባ የሚገለፅ መሆኑን በዚያች ቀን ተገነዘብኩኝ። በአንድ ልቤም ህልም ነው እያለምኩ ነው እልና አስቴር እንኳን ደህና መጣሽ የሚለውን ፅሁፋቸውን እያየሁ እግሬ ሰውነቴ ሁሉ ተብረከረከ። እውነትም ህልም አይደለምና መሐላቸው ገባሁ። ያ ሁሉ ሰው በጩኸት «አስተዬ እንወድሻለን»። እኔም «እወዳችኋለሁ፣ እወዳችኋለሁ» ስል ልሳኔ ተዘግቶ አፌ ብቻ ሆነ የሚንቀሳቀሰው። እንደ ልዘፍን፣ ልጫወት መጥቼ ድምፄ ጠፋ፣ ጉልበቴም ዝሎ ከዳኝ ጉብዝ ተረዳዳ እያልኩ በግፊያ መሐል እየተንሳፈፍኩ እየተጠጋሁ ስመጣ ገና አስራ ስድስት ዓመት ያልሞላቸው ወጣቶችና ህፃናት «አስቴርዬ እንወድሻለን» ብለው ያዘጋጁትን ፅሁፍ ይዘው እንደምንም ብለው ወደፊት መጥተው በዓይኔና በእጅ መጨበጥ ሠላምታ የተለዋወጥኳቸውን ህፃናት ሳይ እንባዬ የባሰ እየተናነቀኝ እንደምንም ፈገግታዬን ከፊቴ እንዳያጡ እየጣርኩ ነበር። የፈጠረኝን አምላክ ሁልጊዜ የማመሰግነው ክብርህ ይስፋ ያልኩበትና የገረመኝ እኔ ከሀገሬ ስወጣ እነዚህ እንወድሻለን ያሉኝ ህፃናት ገና አልተወለዱም ነበር ወይም ብዙዎቹ ገና እየዳሁ ነበር ማለት ነው። አከብራቸዋለሁ፣ እወዳቸዋለሁ ምክንያቱም ፍቅርና ደግነት ሃብታቸው የሆነ እኛን የሚተኩ የነገ ኢትዮጵያውያን ናቸውና።

ወደ ትርዒቱ ልሂድና «ሀገሬ የሙዚቃ ትርዒት» ሶስት ዝግጅቶችን ያቀነባበረ ነበር። ሶስቱም ትርዒቶች የተካሄዱት በአዲስ አበባ ከተማ ነበር። የካቲት 1 እና 2 1989 ዓ.ም. በጃን ሜዳ ሲሆን የየካቲት 1 መግቢያ 12 ብር ሲሆን የየካቲት 2 ደግሞ 8 የኢትዮጵያ ብር ብቻ ነበር፣ እንዲሁም የካቲት 8, 1989 ዓ.ም. በኤግዚቢሽን ሴንተር የመግቢያ ዋጋ 200 የኢትዮጵያ ብር ነበር።

ከአዲስ አበባ ውጪ ትርዒት ያላሳየሁበት ምክንያት እንደ አዘጋጆቹ አገላለፅ ክብደታቸው ወደ 10 ቶን የሚሆን በጣም ግዙፍ የሆኑ ከውጪ ሃገር የመጡትን የሙዚቃ መሣሪያዎች ለማጓጓዝ በጣም አስቸጋሪና ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ ነው።

ላንዳፍታ፣
ባለፈው ዓመት ስዊዘርላንድ ላይ በኢህአዴግ መንግሥት አማካይነት የተዘጋጀ አንድ በዓል ላይ ተጋብዘሽ እሽ ብለሽ ተገኝተሽ ነበር የሚባለው እውነት ነወይ?

አስቴር፣
ይህ ጥያቄ በመነሳቱ ደስ ብሎኛል። እኔ እንግዲህ እስከማውቀው ድረስ በተባለው ዝግጅት ላይ የጋበዘኝም የለም። እኔም አልተገኘሁም። ኋላ እንደሰማሁት ግን አስቴር ተጠይቃ እሽ ብላ ትገኛለች ተብሎ በአዘጋጆቹ እንደተወራ ሰምቻለሁ። ይህንን ካነሳህ አይቀር በቅርቡ ደግሞ አስመራ በሚታተም ጋዜጣ ላይ እኔ አስመራ ሄጄ ትርዒት እንደማሳይ መገለጹን ስሰማ በጣም ገረመኝ። ይህ አንድ ሌላ ትልቅ የፈጠራ ውሸት ወሬ ነው።

ላንዳፍታ፣
የኢትዮጵያውን የሙዚቃ ዝግጅትሽን ስፖንሰር ያደረገው ድርጅት ከአሁኑ መንግስት ማለትም ከኢህአዴግ ጋር ንክኪ ያለው ድርጅት ነው ይባላል። ይህ ምን ያህል እውነት ነው? አንቺን ስፖንሰር ስላደረገሽ ድርጅትስ የምታውቂው ምን ነበረ? ሚጋ ስለሚባለውስ ድርጅት? ከሚጋ ድርጅት ጋርስ ይህ አንቺን ስፖንሰር ያደረገው ድርጅት ግንኙነት አለው ወይ?

አስቴር፣
መጀመሪያ መግለፅ የምፈልገው አለ። ስፖንሰርና ፕሮሞተር (አዘጋጅ) የተለያዩ ትርጉም አላቸው። እኔን አዘጋጅ የሚለው ይመለከተኛል። ምክንያቱም ውሉንም ሆነ ሁሉን ነገር ያደረግኩት ከእሱ ጋር ነውና።

የሀገሬን የሙዚቃ ትርዒት ያዘጋጀው በካሊፎርኒያ ስቴት በሎስ አንጀለስ ከተማ የሚገኝ አፍሮ ላይፍ ኢንተርቴይመንት የሚባል የመዝናኛ ኩባንያ ነው። እኔም የሀገሬ ሙዚቃ ትርዒትን በተመለከተ ጉዳይ የተፈራረምኩት ከዚህ ኩባንያ ጋር ብቻ ነው። እኔ በእርግጥ ልናገርህ የምችለው የሄድኩት አገሬ ናፍቆኝ ይህን ያህል ዘመን በናፍቆት የሚጠብቀኝን ህዝብና የወገኔን ሆይታ በአካልና በዓይን የማየት ስሜት አሰገድዶኝ ለእኔ አመቺ ጊዜ ሆኖ አገኘሁትና ሄድኩ። እውነት መጥታ ይሆናል ብሎ የጓጓ መጥቶ ተቀብሎኛልና ጨዋታዬንም አይቷል። ስለ አዘጋጆቹ ምንነት እነሱው ራሳቸው በራሳቸው ቢገልፁ ተገቢ ይመስለኛል። እኔ በተፈራረምኩት ኮንትራት

መሰረት ከሆን ካምፓኒው በካሊፎርኒያ ስቴት የተመዘገበ የግል ኩባንያ መሆኑን ነው። እኔ የማምነው ግን ከአሁኑ መንግስት ጋር ንክኪ የላቸውም በሚለው ነው። ቢሆን ኖሮ የሙዚቃ ትርዒት ዝግጅትን ለሰፊው ህዝብ ለማስተዋወቅና ለማዳረስ የሚቻለው በሬዲዮና በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጣ ነው። ግን የአሁኑ መንግስት የእኔ ስም፣ የእኔ ሙዚቃ፣ በአጠቃላይ ስለ እኔ ትርኢት የሚጠቅስ ነገር በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮም ሆነ እንዲሁም በመንግስት ጋዜጣ እንዳይጠቀስ ትዕዛዝ አስተላልፏል።

የሚያሳዝነው ነገር ለ16 ዓመታትም ሆነ ከዚያም በፊት በሰጠሁት አገልግሎት በቂ ወዳጆችን አትርፌያለሁ። ነገር ግን እኔ የማውቀው ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮም ሆነ የመንግስት ጋዜጣ የሕዝብ መገልገያ ነው። የአርቲስት ማዶና ልጅ መውለድና ቁርስዋን ምን በልታ ራቷን ምን እንደምትፈጣጥር፣ የዚጊ ማርሌይ ህይወት ታሪክና ያክስት ያጐቱ ስም ሲነገርበት የነበረው የቲቪ ጣቢያ፣ እኔ ተወልጄ አድጌ አገልግዬ ብዙ አገልግሎት የሰጠሁ፣ ብዙ ወዳጆች ያተረፍኩ ኢትዮጵያዊት በቴሌቪዥን ወጥቼ ወዳጆቼ መጥቻለሁና እዩኝ እንተያይ እንዳልል፣ ዘፈኔ እንዳይዘፈን፣ ስለ እኔ የዝግጅት ቀናት የሚገልፅና በአዘጋጁ ተከፍሎ የሚነገር የንግድ ማስታወቂያ እንዳይተላለፍ በጥብቅ ተከለከለ። ታዲያ የመንግስት ንክኪ ያለበት ዝግጅት እንዴት ይኼ ሁሉ ነገር ይከለከላል ወይም በደል ይደርስበታል? እንደው ውንጀላውን ለማጣጣምም ያስቸግራል። ይህን ፍርድ ለአንባቢና ለወዳጆቼ እተወዋለሁ።

<u>ላንዳፍታ፣</u>
ኢትዮጵያ (አዲስ አበባ) የአንቺ ዝግጅት እንዲታይ ተብሎ በጃንሜዳ መጠለያ ያሉ ችግረኛ ተፈናቃዮች እንዲነሱ ተደርጓል የሚባል ወሬ በሰፊው ተወርቷል። ይህ እዚህም ሆነ ሀገር ቤት ያለውን ህዝብ ያነጋገረ ጉዳይ ነበር። ይሄ ምን ያህል እውነትነት አለው? እውነትስ ካልሆነ ይህ ነገር ለምን ሊወራ የበቃ ይመስልሻል?

<u>አስቴር፣</u>
የእኔን ስም ለማጥፋት ሆን ብለው ዘመቻ የሚያካሂዱ ግለሰቦችና ድርጅቶች ብዙ ብዙ ከእውነት የራቀ አሉባልታ ከረጩት ሁሉ በላይ አስፀያፊውና አስከፊው ውንጀላ ይህ ነው። ጥር 14 ቀን 1989 ዓ.ም. ለግል ጋዜጠኞች በሰጠሁት የፕሬስ ኮንፈረንስ ላይ የመጀመሪያው ጥያቄ ይህን የተመለከተ ነበር። የሚገርመው ነገር ሀገሬ በቆየሁበት ሳምንታት ውስጥ ያደረግሁት ሙከራና ጥረት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያ ሔጄ ቃለ ምልልስ እንደማንኛውም አርቲስት ለማድረግ ነበር። እሱ አልተሳካም። የግል ጋዜጠኞች እሺ ብለው ቢመጡም ውንጀላው ምንም ርህራሄ የሌለው ነበር። ጃንሜዳ የሚባለውን ድሮ አውቀው ነበር እንጂ የዛኔ ሄጄ አላየሁትም። እኔ ለሀገሬ ህዝብ እንኳን ሰው የሚኖርበት መጠለያ ቀርቶ ለምን ገደል ውስጥ ቆሜ አልሞሆም። ሬዲዮና ቴሌቪዥን ለምኜ ያቃተኝ ሴትዮ ጃንሜዳን አፈናቀልኩ? በየትኛው መብቴና ሥልጣን? ይህ የፈጠጠ ውንጀላ ነው። ምንም እውነትነት የለውም።

ነገሩ በጣም ስለከነከነን ስለዚህ ጉዳይ የጃንሜዳን አስተዳደር ጠይቀን የሰጡን መልስ እንደሚከተለው ነው፦ «ጥታው የፈረስ ጋጣ ሆኖ ሳለ በተፈናቃዮች መስፈር ምክንያት አገልግሎት ላይ ባለመዋሉና በዚህም ሳቢያ ውድድር ለማካሄድ ባለመቻሉ ጉዳት እየደረሰበት መሆኑን» ፌዴሬሽኑ ለክልል 14 መስተዳድር ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ጽ/ቤት አመልክቶ በተፈቀደለት መሰረት ተፈናቃዮቹ ሰፋሪዎች እንዲነሱ መደረጉን የፌዴሬሽኑ ዋና ፀሀፊ አቶ ስብሐት ታደሰ አመልክተዋል። እንዲሁም ፌዴሬሽኑ በ6/11/87 ለክልል 14 መስተዳድር ባህልና ስፖርት ቢሮ በፃፈው ደብዳቤ መሰረት «ከኤርትራ በመጡ ተፈናቃዮች የፈረስ ጋጣው በመያዙ በዓመት ያገኝ የነበረውን ገቢ ማግኘትና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ለማዘጋጀት አለመቻሉን ገልፀው የሚመለከተው ክፍል ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ መጠየቁን የክልል 14 መስተዳድር ባህልና ስፖርት ቢሮ በ24/8/88 ለፌዴሬሽኑ በፃፈው ደብዳቤ በቅድሚያ ገልጿል።» በ1995 ፌዴሬሺኑ ተፈናቃዮች ይነሱልን፤ ይህ የፈረሰሐ ፌዴሬሽን መገልገያ ነው ብለው ጥያቄ አቅርበው መንግሥት ከሁለት ዓመት በኋላ እኔ ፕሬስ ኮንፈረንስ ልሰጥ ሶስት ቀን ሲቀረው ተፈናቃዮቹን ባስቸኳይ አስነሷቸው። ብዙዎች አንባቢዎች እንደተገነዘቡት ጃንሜዳ እጅግ በጣም ትልቅ ሜዳ ስለሆነ በአንድ አካባቢ የሰፈሩ ሰዎች ለትርዒቱ ምንም ችግር እንደማይፈጥሩ ግልፅ ነበር። መንግሥት ይህን ጊዜ ጠብቆ ለምን እድስስቸው አለውቅም። ኋላ ቆይቶ እንደተረዳሁት መንግሥትም ሆነ ፌዴሬሽኑ መታከኪያ የፈለጉ ይመስለኛል። እኔ በበኩሌ፤ እስከማውቀውም ድረስ የትርዒቱ አዘጋጆች ተፈናቃዮች እንዲነሱ አልጠየቅንም፤ ልንጠይቅም አንችልም።

በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ የሬዲዮ ጋዜጠኞች ነን የሚሉ ከአገር ቤት ፋክስ መጣልን እያሉ የፈጠራ ወሬ እያወሩ ስንበታቸውን ከሚያሳልፉ ምን አለበት እኔ በሕይወት እዚሁ አጠገባቸው አለሁ እንዲሁ ከሚያወሩ ምናለ ቢያጣሩ? እኔ እውነተኛ ጋዜጠኛ የማውቀው ነገርን አረጋግጦና አጣጥም ሲያወራ ነው እንጂ ሰውን ባልዋለበት አውሎ የአድማጭን ልብ በአፍ ለመመረዝ መሞከር አይደለም ሁልጊዜ እውነት አሸናፊ ነውና። በዚህ አጋጣሚ ላንዳፍታ መጽሔት የደረሳችሁን ወሬ አስተያየቱን ከማስተላለፍ ፋንታ የሚመለከተውን ግለሰብ (እኔን) ስለእኔ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ እድል ስለሰጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ። ይህ የሚያሳየው ለአንባቢዎቻችሁ ምን ያህል ከበሬታ እንዳላችሁ ነው።

<u>ላንዳፍታ፣</u>
አዲስ አበባ በነበርሽበት ጊዜ ነፃ ጋዜጦች(የግል ጋዜጦች) ስለአንቺ ብዙ ነገሮችን ማለትም ጥሩም፣ መጥፎም የሆነ አስተያየት በብዛት ሲሰጡበት የነበረና እኛም ጋዜጣዎቹን አግኝተናል። ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት (ኢህአዴግ) ቴሌቪዥንም ሆነ ሬዲዮ ጣቢያ ወይም ጋዜጣው ስለመምጣትሽም ሆነ ስለዝግጅትሽ ምንም ዜና አላወጡም፣ በቴሌቪዥንም አላቀረቡኝም ብለሻል። አስቴርን የመሰለች ታዋቂ አርቲስት፤ አገሯን ያሳወቀች ከብዙ ጊዜ በኋላ ወደ አገሯ ስትመለስ በአገሯ አንድ ቴሌቭዥን ጣቢያ ያልቀረበችበት ምክንያት በአንቺ አመለካከት ምን ይመስልሻል?

<u>አስቴር፣</u>

አዲስ አበባ ያሉ የግል ጋዜጦች ደጉንም፣ ክፉውንም፣ አሉባልታውንም ሁሉ ልክ ማስረጃ እንዳገኙ ሆነው ነበር ለአንባቢዎች ያቀረቡት። ህዝቡ የሚፈልገውን ፎቶግራፌን ገፄ ያደርጉና ያንንም ይህንንም ፅፈው አንባቢዎቻቸው መስማት የሚፈልጉትን መረጃ ቀጥ አድርገው ይዘው ነበር። እኔ ግን በጣም ስራ ይበዛብኝ ነበርና አላነባቸውም ነበር።

የመንግስት ሚዲያዎች ግን እኔ በውጭ አገር እያለሁ ስሰማ የእኔን ዘፈን አስመስሎ እንኳን ለዘፈነ ሽልማት ይሰጡ እንደነበር ነው። በኬንያ (URTNA) የተሰራው ቪዲዮ በሳምንት አንድ ቀን በቴሌቪዥን ሳይቀርብ አይቀርም። በሬዲዮ የዘፈን ውድድር ላይ በብዛት አሸናፊ የአስቴር ዘፈን ነበር። ግን ከነንፍሴ አለሁ ብዬ ስደርስ እንዴት ተብሎ እዚያች አካባቢ የእኔ ስም ሊደርስ? የመንግስት ሚዲያ ሠራተኞች በዚያ ነገር ቅሬታቸውን ሰንዝረውብኛል። “እባክሽ በዚህ ነገር እንዳትከፊ” አለኝ አንዱ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሠራተኛ። እኔም “እንዴት አልከፋም ሚዲያ የህዝብ መገልገያ አይደለምን?” ብዬ ጠየቅሁ። የማስታወቂያ ሚኒስቴር ኃላፊው ባለስልጣን ይህንን ትዕዛዝ እንዳስተላለፈ ሰማሁ። 120 የሚባል የቴሌቪዥን ፕሮግራም ብዙ ወደ ኢትዮጵያ ሄደው የተጫወቱ ወንድሞቼና እህቶቼ አርቲስቶችን ያስተናገደና የጋበዘ፣ ማስታወቂያቸውንም የገፉፋ ጣቢያ እንደነበረ ስለማውቅና ወጣቱ የሚወደው ፕሮግራም ስለነበረ ሲሆን ይጋብዘኛል ብዬ ጠበቅሁ። ፀጥታ ሲበዛ ተነስቼ ባመለከት እንደውም ከነአካቴው ተከለከልኩና አረፍኩት። በፊት ቀልድ መስሎኝ ነበር። ፍፁም አመረሩ ነገሩ ሊገባኝ አልቻለም። ማለትም እኔ አስቴር ስለሆንኩ በቴሌቪዥን መቅረብ አለብኝ ማለቴ ሳይሆን አርቲስት ነኝ ብሎ የቀረበ ሁሉ ይስተናገዳል። የጣቢያውም መመሪያ ሆኖ ሲኖር ሳለ ለእኔ ሲባል መመሪያ (Policy) መለወጥ የሕገ ወጥና የማን አለብኝነት አሰራር ነው። ሳልል ማለፍ የማልፈልገው ይህን ትዕዛዝ በእኔ ላይ ያስተላለፉ ባለስልጣኖች ምንም ቢሆን አድማጭና አፍቃሪ አለኝ፤ ያ አፍቃሪ ህዝብ ደግሞ የሚፈልገውን መስማት አለበት፤ መብቱም ነው። ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጣ የህዝብ ንብረት፣ የህዝብ መገልገያ መሆኑን ዘንግተው ኃላፊነታቸውን ረስተው የሚወዱትና የሚመስላቸውን መፈንጫ አድርገውታል። ግን አሁን ሳስበው ምናልባት እግዚአብሔር ሲጠብቀኝ ይሆናል የተከለከልኩት ብዬ አስባለሁ። በመንግስት ቴሌቪዥን ወይም ሬዲዮ ኢንተርቪው ወይም መግለጫ ሰጥቼ ቢሆን ኖሮማ አሁን ምን ይውጠኝ ነበር? ለነዛ ለጠላቶቼ የበለጠ ጥሩ ስም ማጥፊያ ይሆናቸው ነበር።

<u>ላንዳፍታ፣</u>
በተጨማሪም መግለጫ በሰጠሽበት ወቅት ከግል ጋዜጠኞች በስተቀር አንድም የመንግስት ጋዜጠኛ አልነበረም ይባላል? እውነት ነወይ? ይህ የሆነው ከአንቺ በቀረበ ጥያቄ ነው ወይስ እነሱ ናቸው ለመምጣት ያልፈለጉት?

<u>አስቴር፣</u>
ረቡዕ ጥር 14 ቀን 1989 ዓ.ም. (ጃንዋሪ 22, 1997) አዲስ አበባ በሚገኝ በኢምፔሪያል ሆቴል የግል ጋዜጠኞችን፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና የመንግስት ጋዜጣ ጭምር በሙሉ የተጋበዙበት የፕሬስ ኮንፈረንስ ሰጥቼ ነበር። ከ40–50 የሚሆኑ የግል ጋዜጠኞች እግዚአብሔር ያከብርልኝ ጥሪውን ተቀብለው ሲገኙ አንድም የመንግስት ሚዲያ አልተገኘም። እኔ የሰጠሁት የፕሬስ ኮንፈረንስ ለማንኛውም ጋዜጠኛ ክፍት የሆነ ነበር።

<u>ላንዳፍታ፣</u>
አገርሽን እንደምትወጂና የአገርሽን አንድነት እንደምታከብሪ ከዚህ በፊት ገልጸሻል። እና ስለአጠቃላይ ኢትዮጵያ ሁኔታ ካየሽው፣ ካስተዋልሽው፣ ከሰማሽው በመነሳት ምን ትያለሽ?

<u>አስቴር፣</u>
እኔ ሀገሬንና ህዝቧን በጣም እወዳለሁ። ያለኝንም ፍቅር ሁልጊዜ መድረክ ላይ በወጣሁ ቁጥር እግዚአብሔር በሰጠኝ ሙያ አሳያለሁ። ኢትዮጵያ ሀገራችን የብዙ ጉሳ፣ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ፣ የብዙ ታሪክ፣ የጥሩ ሃይማኖቶች እናት የሆነች ሃገር ናት። ከዚህ ሁሉ ባህልና ታሪክ መሃል በዛች አገር ውስጥ ለመብቀል እድል ያገኘን ሰዎች በያለንበት ተፋቅረንና ተስማምተን ታሪክና አባቶቻችንና እናቶቻችን ያቆዩልንን ኢትዮጵያ መገንባት ነው። እኔ ሁልጊዜ እግዚያብሔር የሰጠኝን ፀጋ አክብሬ መጠቀም አለብኝ ብዬ የማምነው ለፍቅርና ለአንድነት ብቻ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት በፍጹም አምናለሁ።

<u>ላንዳፍታ፣</u>
በተረፈ አንቺ በግልሽ ለአንባብያን ስለዚህ ጉዳይ የምታስተላልፊው መልዕክት ካለ።

<u>አስቴር፣</u>
ይኼ ጥያቄ በጣም ብሶቴን የሚያወጣና ስሜቴን ለወገኔ የምገልጽበት በመሆኑ ለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ። ወገኔ እንዲያውቅልኝ የምፈልገው ነገር አለ። እኔ አንድ ኢትዮጵያዊ ነኝ። በኢትዮጵያዊነቴ የምኮራ፤ አገሬን የምወድና ስለአገሬ ፍቅር ሁሌ የማዜም አርቲስት ነኝ። “እኔም አገር አለኝ ...” ብዬ ለዘፈንኩላትና ለምኮራባት ውድ አገሬ፤ ለወገኔና ለሥጋ ዘመዶቼ ያለኝን ናፍቆት ለመወጣት፤ በዚያውም ለሚናፍቀኝ ወገኔ አንዲትም ትርዒት ብትሆን ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቴ ደስ ብሎኝ በመሄዴ ያላሰብኩትና ከግምቴ ውጪ የሆነ ትርጉምና ስም ሲሰጠኝ ምን ያህል እንዳሳዘነኝ የምናውቀው እኔና ፈጣሪዬ ነን። ለወገኔና ለአገሬ ያለኝን ፍቅር የሚያውቁ ሁሉ ያውቁታል። ዛሬ ስሜን የሚያጠፉትም ይረዱታል፤ ከረዥም ጊዜ ቆይታ በኋላ በአገርና በወገን ናፍቆት ምክንያት ወደ አገሩ እየሄደ የሚመለሰው ኢትዮጵያዊ ብዛት ቤቱ ይቁጠረው። ያም ብቻ ሳይሆን ከዚህ በመሄድ ቅልጥ ያለ ድግስ በመደገስ ሠርግ የሚያድርገው ኢትዮጵያዊስ? ብዙ አርቲስቶችስ ይመላለሱ የለም ወይ? ትርዒትስ ያሳዩ የለም ወይ? ምነው የኔ የተለየ ትርጉም ተሰጠው? አገሬ ሄጄ ብዘፍንስ ምን ብዬ ነው የዘፈንኩት? መንግሥትን አሞገስኩ? ምን አልኩ በሞቴ? የእኔን ስም ለማጥፋት ቀደም ሲል የነበሩ ሙከራዎች አሁንም እንዳሉ አንዳንዶቹን ለወገኖቼ መግለጽ እወዳለሁ። በተለያዩ ጊዜያት የወገን ጥሪ ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ እኔን ሳይጠይቁ በራሪ ወረቀት ላይ ያወጡና ቀኑ ሲደርስ አስቴር እምቢ ብላ ቀረች እያሉ ለብዙ ጊዜ ተወንጅያለሁ። እኔ ለወገን ጥሪ ዝግጅት እምቢ ለማለት አይደለም። ቀደም ሲል ብዙ

ሰርቻለሁ። አሁን ግን ድርጅቱ በዛና ለስንቱ ልሁን፤ አንዱን እሺ ብዬ ሌላውን እምቢ ብል ችግር ሊመጣ ነው። ሁሉንም እሺ ማለት ደግሞ ያስቸግራል፤ እኔም እኮ ኑሮ አለኝ።

በሆን ባልሆን ለሚወነጅሉኝ እኔ በጣም ስራዬን የምወድና ሁልጊዜ እንቅልፍ አጥቼ ካለፈው አመት ይህን ዓመት ስራዬን ማሻሻል የምጥር ወገናችሁ ነኝ። እንድታውቁም የሚገባው አርቲስት ማለት ባህል ነው። አገርን ደግሞ አገር ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ባህል ነው። ያለ አግባብ ተነስታችሁ አርቲስትን ባጠቃችሁ ቁጥር ባህላችሁን እንደምታጠቁ እወቁት። ዛሬ እኛን የሚያገለግለንና የሚያለማን እርስ በእርሳችን መጠቃቃት አይደለም።

ወገኖቼን የምለምነው አንድ ነገር አለኝ። አካሄዴን በተመለከተ የተሰጠው ትርጉም ካሰብኩት፤ ካለምኩትና ፍጹም ካልጠበቅሁት ውጪ መሆኑን እንዲረዱልኝ ነው። ምናልባት ሳላስበው፤ ሳልገምተው የሚወደኝን ወገኔን አሳዝኜ ከሆን ከልቤ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ለአገሬ ያለኝን ፍቅርና ስለአገሬም የማደርገውን ነገር ወደፊት የሚታይ ይሆናል።

ላንዳፍታ፣

በአሁኑ ጊዜ የአስቴር ዘፈኖች በናፍቆት እየተጠበቁ ናቸው። መቼ ነው አዳዲስ ዘፈኖችሽን የምታቀርቢልን? አሁን አብረሽ የምትሰሪው ኩባንያ አለ ወይስ በራስሽ ነው የምትሰሪው? ትርዒቶች በየቦታው ለማቅረብ ዕቅድ አለሽ ወይ?

አስቴር፣

እርግጠኛ ነኝ ጊዜው ተራዝሟል። በእውነት አዲስ ዜማዎችም እየፃፍኩ ነው። ግን በአንድ አልበም ውስጥ ያሉ 8 ወይም 10 ዘፈኖች ቢሆኑ ቢቻል አብዛኛው ወይም በሙሉ ጥሩ ዜማ ሆኖ መደመጥ መቻል አለባቸው ብዬ አምናለሁ። ይኼ ይኼ ነው ጊዜ የሚወስደው። በቂ ይሆናል ብዬ እንደረካሁ ለአድማጮቼ አቀርባለሁ። የግል ሥራዎቼን የማቀርብበት ባርከንስ የተባለች ትንሽ የሬከርድ ኩባንያ አለችኝ። ብዙውን ስራ ግን ከተለያዩ ኩባንያዎች ጋር ነው የምሰራው።

ላንዳፍታ፣

በጣም እናመሰግናለን አስቴር።

## የአትላንታ ኢትዮጵያውያን ከንቲባ ቢል ካምብል በድጋሚ እንዲመረጡ ድጋፋቸውን በመስጠት ጥያቄዎች አቀረቡ።

JULY 27 1997 በአትላንታ ከተማ ሮር ስታር ሆቴል በተደረገው ዝግጅት በርካታ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ለአትላንታው ከንተባ ቢል ካምብል ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም ቀደም ሲል ከንቲባው ለአትላንታ አትዮጵያውያን ያደረጓቸው ተግባራት ተጠቅሰው የኢትዮጵያዊ የክብር ዜጋነት በኢትዮጵያውያኑ ተሰጥቷቸዋል። ለከንቲባው የቀረቡ ጥያቄዎች 1ኛ. በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት ችግር ጉዳዮች በተመለከተ፤ 2ኛ. የአትላንታ ኢትዮጵያውያን የኮሚኒቲ ማዕከል ለማሠራት የሚያያደርጉትን ጥረት በተመለከተ፤ 3ኛ. የ1998 የሰሜን አሜሪካ እግር ኳስ ጨዋታ የአትላንታን ዝግጅት በተመለከተ፤ 4. SEPTEMBER 11– የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ቀን በአትላንታ የኢትዮጵያ ቀን መባል በተመለከተ፤ 5. ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያንን ሥራ የማስያዝን ጉዳይ በተመለከተ ሲሆን ከንቲባው የተጠየቁትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቀላል እንደሆነ ገልጸዋል።

ከንቲባው በዚሁ ዕለት የተሰጣቸውን የኢትዮጵያዊነት የክብር ዜግነት ያስደሰታቸው መሆኑን ገልጸዋል።




ቢል ካምብል ከኢትዮጵያውያኖች ጋር
(ከግራ ወደ ቀኝ) ቴዎድሮስ ኃ/ጊዮርጊስ፤ መክረን ጣሰው፤ ሰለሞን ደምሴ፤ ከንቲባው፤ ኢትዮጵያ አልፍሬድ፤ ተክሌ አየለ፤ መኮንን ገሠሠ

# አጭር ልቦለድ ታሪክ

## አትዘንጋ

ከተምሳሊት ጨዋታ የተዘረፈ

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፸፭/፹፱ ዓመት

SAFEU © Copyrighted 1983/97

የትም ሆንክ የትም ምልክትህን አትዘንጋ

ቦታው እመት ተመዝብራ ይታጠቁ ቤት ውስጥ ነው። የመጨረሻ ልጃቸው ደባልቄ ቢወጣ ለትምህርት ወደ ነጭ አገር ከመሄዱ በፊት በሃሳብ የተበታተኑትን ልጆቻቸውን (ታላላቆቹን) ሊያስተባብር የሚችል፣ የዕርዳታቸው ፈላጊ (ተጧሪ) መሆናቸውን ለመግለፅና ግሳጼ ለማድረግ በነፍስ አባታቸው በመምሬ መዓዛ ይርጉና በወንድማቸው በአያ ጎርብጤ ዘውአለ ፊት ምሬታቸውንና ቅሬታቸውን ለማውጣት ጥሪ አድርገው የሚተላለፈውን መልዕክት ለማሳየት በአንድ ክፍል የተዘጋጀ አጭር ትርኢት ነው።

* * *

በለዘበ አየር ውስጥ እንደ ብርጭቆ የተጋገረው ደመና በነፋስ ግፊትና በምድር ስበት እየተረዳ መውረድ ሲጀምር ድንጋይ እንደተወረወረበት መስተዋት ብትንትኑ ይወጣ ጀመር። በአየር ቅዝፊያ ውስጥ እየተምዘገዘገም መውረዱ ሲፋጠንም አዝርዕትና ዛፎች እስክስታ እንደሚያወልቀው ትከሻ ተርገፈገፉ። ‹‹አንዴ ነግቶ ቤት ሰርቼ›› እያለ ሲያማርር አድሮ ሲነጋለት ‹ሆድ ይብሳል› እያለ በተሰማራው አሞራ ሳያበቃ ማረፊያ ተገን አለን ብለው ሣሩንም፣ ጭዱንም ለቃቅመው ጎጆ የቀለሱትን ሁሉ ሳይቀር እግዚኦ ማህረነ የሚያሰኝ በረዶ አገሩን አመሰው። መሬት ላይ ያረፈው በረዶ አዲስ መጤውን ቦታ አላጋራህም ሲለው የንዴቱን እናቱን ገጭቶት በአየር ውስጥ በመገልበጥ ከሌላው ጋር ደባልነት ይገባል።

ከእመት ተመዝብራ የሳር ጎጆ ላይ ሲያርፍ የጥጥ ፍራሽ ላይ እንደደላው ገላ ድምፁን አጥፍቶ የተረጋጋው በረዶ ከጎጆዋ ውስጥ በሚነደው እሳት ጭስ ሙቀት እየቀለጠና በአዲስ መጤው እየተገፋ ተንከባልሎ ከመሬቱ ላይ ይከሰከሳል። በጣሪያው ክፈፍ ዙሪያ የሚንጠፈጠፈው ውሃ እንደ ጢስ ዓባይ ፈንቃይ ለመሆን ጉልበቱን ቢፈታተንም ተጨማሪ ኃይል ባለማግኘቱ እየተዳከመ ነው።

ይህ ሁሉ ምስቅልቅል እመት ተመዝብራን አልረበሻቸውም። የተፈጥሮን ልማትንም ሆነ ጉልበት ስለሚያውቁትና በፈጣሪ መርሀ-ግብር ለመግባት ስለማይፈልጉ የባሰ አታምጣ እያሉ ይኖሩታል። በዐይነ-ኅሊናቸው እየተመሩ መኖር ከጀመሩ ብዙ ጊዜ ሆኗቸዋል። ትዝታ እንጂ የወደፊት ተስፋቸው እንዳያብብ የሕይወት ቦዩ ከታገደባቸው ከርሟል። በስንቱ ልጆቻቸው ተመጥምጦ ያለቀው ጡታቸው ያራገፉት ስልቻ መስሎባቸው ይታያል። እንደሙክት ከደለቡት ልጆቻቸው በአጠገባቸው ያለው ደባልቄ ቢወጣ ብቻ ነበር።

ደባልቄም እንደሌሎቹ ልጆቻቸው ከጉያቸው የመውጫው ጊዜ ስለተዳረሰ የእናትነት አንጀታቸው ብሶት ይዞት ዕንባ ዕንባ ቢላቸውም በሥራቸው ተጠምደው ደፋ ቀና ሲሉ ለሚያያቸው ግን ሰርገኛ ይመስሉ ነበር።

ደባልቄ ቢወጣ ወደ ነጩ ዓለም ለመሄድ ዕድል ስላጋጠመው በጎጆው የሳር ክዳን በላይ የጣሳ አሞራ ውስጥ ተጭኖ ለመብረር ቀኑን ይጠብቃል። ኅሊናው የሚያንጎራጉርለት ግን ብሶትን ነበር። *‹ምነው አትመክሩኝ፣ መላ አትሰጡኝ፣ ግራ ገብቶ ሲቸግረኝ፣ ይገባኛል ችግራችሁ፣ የእናንተም ነው የሁላችሁ፣ ታዲያ ምን ዝም አሰኛችሁ?›*

እመት ተመዝብራ ከጓዳ የቡና ዕቃቸውን እያቀረቡ ደባልቄን በመጥራት «ልጄ ልብ ብለህ አድምጠኝ።» አሉት። አንዳንድ ምክሮችንና የልባቸውን ጨዋታ ትንፋሻቸውን ሳያጡ የመለያያ ኑዛዜ ለማድረግ ታስቧቸው ነበር ልሳናቸውን ለመክፈት የሞከሩት።

«እየሰማሁኝ ነው።» ሲል መለሰላቸው በተሰላቸ መልክ።

«አዳምጠኝ ነው የምልህ!» ልመና ይሁን ቁጣው ባልለየ ድምፅ። ልብ ብሎ እንዲያዳምጣቸው እንጂ የገበያ ጫጫታ አይደሉም የሚሰማቸው።

«እሺ አዳምጣለሁ፣ ምንድነው የምትነግሪኝ? እሱን እንደሆነ ደግሜ ደጋግሜ ሰምቼዋለሁ።»

« *‘የትዕቢተኛ ቤቱ ከመንገድ ዳር ነው’* አሉ። ስለእሱ ልቡና ይስጥህ ልጄ። አሁን የምነግርህ ጠሊቅ ምክር ነው።» ሊያቋርጣቸው ሲል በመገሰፅ ቀጠሉ። «እኮ ቆይ ረጋ በል! ልብ አድርገህ አድምጠኝ። እንዲያው ጌሾ እንደጎደለው ቡቡኝ ቶሎ ቶሎ አትፍላብኝ። ይኸው አለማስተዋልህ አይደል ሰላም እያሳጣ ወየው የሚያሰኝህ።»

«አመልሽ ነው። ጀመራት እንግዲህ።» ደባልቄ እንደልማዱ አርጎመጎመ። ድምፁን በመቀነስ በጥርሱ ስር የሚናገረውን ዘለፋውንም ሆነ ትችቱን ስለለመዱት ችላ እያሉ ያልፉታል። «ይህንን ከማለት ይልቅ ወየው የማያሰኘውን አትወልጂም ነበር።»

«ወይ የኔ ጉድ! ብለህ ብለህ ደግሞ ባምላክ ሥራ አስገባከኝ? ገና ከዚሁ ይህንን የጀመርክማ ከዚያማ ስትደርስ እኔ እበልጥ ሳትል ይቀራል?!» አንዳንዴ ሲያስቡት ከሰው የወለዱት ልጅ አይመስላቸውም። ለምን ከእግዚያብሔር ጋር ሊያጣላቸው እንደሚፈልግም አያውቁም። ከልጅነቱ ጀምረው የቻሉትን አሁን ሊለያቸው ሲል ትእግስታቸውን ሊያጡበት አልፈለጉም። ይህቺ እየተብለጨለጨች በአየር ውስጥ የምታጓራው የአየር መንኮራኩር መንገድ ቢጠፋት እንዴት እንደምትገኝ፣ ቀለቧ ቢያልቅ ስንቋን እንዴት እንደምታገኝ መቸም ለእግዜሩ የቀረበች ስለሆነች እሱው በትንፋሹ እየደገፋት ካልሆነ በስተቀር ምስጢሩ እንቆቅልሽ እየሆነባቸው ሃሳባቸው ተንጠልጥሎ ቢናገሩት ቂል የሚያሰኛቸው ሆኖባቸው ብቻ ደግ ደጉን እየተመኙና በልባቸው እየፀለዩ ናቸው።

«አይ አንቺ እማማ፣ እንዲያው እንዲህ ያለ ሃሳብ እያፈለቅሽ ብቻ ወተቷን እንደምትነፍግ ላም ባሳብ ተጎተች።»

«ወግ ወጉንስ ይዘሃል። ላሚቷ ወተቷን የነፈገችው ለልጅዋ መሆኑን አለመረዳትህ አለመብሰልህን ያሳየኛል። እንዲያው ይህን ሳትረዳና ሳታውቅ ውጪ ሂደህ ቀለምስ እንዴት ሊዋሃድህ ይችላል? እንዲያው በቀላሉ ይህንን የሳትክማ ሌላውንስ ከቶውንም የምትከጅለው አይመስለኝም። አይ የኔስ ወላድነት ከመከኑትም ምንም ለውጥ ያለው መስሎ አይታየኝም።»

«አይ እማማ፣ ለዚህ ብዬማ ነበር ጥሩ ጥሩውን አስተካክለሽ ውለጂ ያልኩሽ። ጥሩ ጥሩውን ያልኩሽ በጠባይም ሆነ በዕውቀት በጀግንነት በስራ አንቺ በፈለግሺው ስራ ሊራመድ የሚችል ከሁሉ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ እንዲሁም አባቶቼና እናቶቼ ጋር አብሮ ለመሰለፍና ሃሳብ ለመቀበል፤ ለመንቀፍና ለመማር፣ በአጠቃላይ በዘሩ ማመን የሚችል ልጅ አትወልጂም ያልኩሽ። አለበለዚያስ ያው እንዳልሺው መምከኑ ይበጅ ኖሯል።»

አንዳንዴ የሚናገረው ልክ ነው ብለው ስለሚያምኑ በቸልታ እያድበሰበሱ በጥሞና የተነፈሳትን ሁሉ ያዳምጣሉ። ሆኖም በሃሳብም ይሁን በንግግር ሊረቱለት የቆሙባት መሬት እሺ ስለማትላቸው እየተማረሩም ቢሆን ክርክሩን፣ ሞቅሞቁን ወይንም ውይይቱን ይገፉበታል። «ቀደም ሲል መርጠሽ አትወልጂም ነበር ወይ ስትል ሳታስበው የአፍ ወለምታ የደረሰብህ መስሎኝ በጣም ሳላላምጠው በቀላል ላልፈው ነበር። አሁን ደግሞ ደግመህ በመጥቀስና ለማስፋፋትም ማለትም ባገላለፅ ለማሳመን ባደረግከው ገለፃ ከምርህ መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ፤ በተለይ በፈጣሪ ሥራ በመግባትህ እንዲያውም በጣም አስቆጥቶኛል። ስለዚህ አሁን ላንተ መልዕክቱን ከመንገሬ በፊት አንተኑ በመጀመሪያ በደንብ አድርጌ ስርዓት የምትይዝበትን መስመር መፈለግ አለብኝ።» አሉት። ስለመምሬና ስለአጎቱ መምጣትም ቀድሞ እንዳላሰቡበትና አሁን ለማስጠራት ምክንያት እንደሰጣቸው በማስመሰልም «ለዚህም ቀላል መስሎ የሚታየኝ፣ ከፈጣሪ በታች የማምናቸውን የሥነ–ምግባርና የሃይማኖት ራስ የሆኑትን መንፈሳዊ አባቴን መምሬ መዓዛ ይርጉን፣ በሀዘኔ በደስታዬ ሁልጊዜ የማይለየኝ፣ የወገኖቼን ስርዓት ማጣት እንደረመጥና እንደቋያ ቃጠሎ የሚያንገበግበውን፣ የአበውንና የወጣት አስተሳሰብን ማዋሃድ ይቻላል ብሎ የሚያምነውን ወንድሜን ጎርብጤ ዘው አለን ሁለቱን ጠርቼ፣ ወንጋራ አስተሳሰብህን ገልጪ ነግሬ ማመን የምትችልበትን ፈለግ ካላየሁ በቀር መልእክቱን ላንተ መንገሩስ ሃሳቡን በለል መልቀቅ ነው።»

የእናቱን ልብ እንደሚያደርቅ የእነኚህን የበላዮቹን ልብ ማውለቅ ስለማይችል የእናቱን አስተሳሰብ ሲረዳ አፌን በዳቦ የሚልበት አጣ። እናቱም ወደ ውጪ ወጣ ብለው የሚላክላቸው ልጅ በጥሪ ፈለጉ። «እንጉዳይ፣ እንጉዳያ! አንቺ እንጉዳይ! የለችም መሰለኝ። አዱኛ፣ አዱኛ፣» ቀልጣፋው አዱኛ አቤት ሳይላቸው የበራ አምፖል ልሳም እንደምትል ትንኝ ሮጦ እግራቸው ስር ተሰካ። «ጎሽ የእኔ ልጅ ሮጥ ብለህ ሂድና መምሬ መዓዛንና አያ ጎርብጤን እማማ ተመዝብራ ይጠሯችኋል በልልኝ። መልዕክቱን አድርሰህ ስትመልስ ኪስህን ሙሉ ቆሎ እሰጥሃለሁ።» እሺም አላላቸው በቅፅፈት ካጠገባቸው ተሰወረ።

«እማማ እባክሽን ይልቁን የምትነግሪኝን ንገሪኝና ሰምቼው ልገላገለው።» አለ ደባልቄ አላዋቂ የሚያሰኘውና ተከራክሮ የማያሸንፍበት መድረክ እንዳይከፈት በመስጋት። ያሰቡትን ያለታዛቢ እንዲነግሩት በመፈለግም «አሁን አንቺ ያመጣሽው አስተሳሰብ መጥፎ ነው ብዬ ለመንቀፍ ሳይሆን የመምሬ መዓዛ ይርጉና የአጐቴ የጋሽ ጎርብጤ ሁኔታን በደንብ ስለምረዳው አንቺ ከምትይው ሃሳብ የተሻለ አያመጡም። መምሬ መዓዛ የእናንተ አድራጊ ፈጣሪ፣ ለፈጣሪ ቀራቢ እሳቸው ብቻ በመምሰል አዲስ ሃሳብ ሲቀርብ አጥብቀው ተቃዋሚ፤ በየጊዜው በሚደርሰው ብጥብጥ በድርጊቱ የማይካፈሉ፣ በብጥብጡ በሚደርሰው የደም መፋሰስ በይው ወይም የወገን እልቂት በፈለግሺው አንቺው ሰይሚው፤ የማይገኙ ራሳቸውን ወዳድ ሰው ናቸው። አዎ ብቻ፣ *'ረሃብ ካለፈ ምሳ፣ ዝናብ ካበቃ ገሳ'* ይባል የለ። እንዲሁም እሳቸው ነገር አለሙ ካበቃ በኋላ ያምላክን ስም በመጠቀም ከታሪክም ጠቀስ ከሃይማኖትም ጠበቅ እያደረጉ ሲሰብኩ ላንቺ እግዜር በምድሩ ናቸው። በዚህ ላይ ደሞ ካንዱ ቤት ወዳንዱ ቤት ሲሄዱ በቶሎ የማይገኙ የቦይ ውሃ ሰው መሆናቸውን እኔ አላጣሁትም። ይልቅስ አጐቴ ጉርብጤ ዘውአለ ምንም እንኳን ከወጣቱ ጋር ያበውን አስተሳሰብ ለተተኪው ትውልድ አወርሳለሁ ብሎ ለተሰለፈበት ዓላማ ልክ እኛ ማለትም እኔና ሌሎቹ በምንለው መስመር ባይመጣም ትንሽ እሱው ይሻላል። የእሱ መገኘት እንኳ ባልከፋም ነበር።» በማለት ሊያግባባቸው ሞከረ።

«ታዲያ ሌላ ምን አስፈለገህ?» አጭር ነበር የሃሳብ መሰርሰሪያቸው።

«ታዲያ እሱ ደግሞ ጭራው የማይያዝ ሰው ነው። አልፎ አልፎ ውሃ ይወስደዋል። በዚህ ጊዜ የሚናገረው ቃል እኔ ትርጉሙም አይከሰትልኝም። ባጠገቡ ካሉት ስሰማ ያደንቁታል። ግን የሱ ሃሳብ በሰፊው ለሰፊው በግልፅ ሲቀርብ አላየሁም። ታዲያ ከእንዲህ ዓይነት ሰዎች ምን ይገኛል ብለሽ ነው፤ እማማ? ራሳቸው ግር ብሏቸው መፍትሄ ያጡ ሰዎች ናቸው። በተለይ መምሬ መዓዛ ይርጉማ! ክፉ ጥላቻ በእሳቸውና በመሰሎቻቸው እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ አለን።»

ፀሎት፣ ቅባቅዱስና ጠበል የማያስለቅቅ በሽታ ነው የያዘው? እያሉ በልባቸው። «ኧረ እንዲያው ተው አንተ ጉረምሳ ልብህ እንዲህ አይበጥ! *'እጅ የላከውን አፍ አያስተውልም'* አሉ።» ሲሉ አስጠነቀቁት። ግትር ጠባዩን እያወቁ።

«ይህንኑ አይደል እንድናገር የፈለግሽው። ስለዚህ እማማ፣ የሁለቱንም መገኘት ካለሁበት አስተሳሰቤ ንቅንቅ ስለማያደርገኝ ይልቅስ መልዕክቱን ንገሪኝ።»

ለደባልቄ የአጐቱም ሆነ የቀሳውስቱ ትግልና ስልት እርምጃው አልዋጥልህ ያለው ነው። የህዝቡን ብሶት በአደባባይ አሰምተዋል ተብለው መምሬን አንገላተው ከጣቢያ ሲወስዷቸው የህዝቡ ሆይታ አመፅ እንዳያስነሳ በማለት መንግስት ያሰሯቸውን ባለስልጣኖች የሥራ ዝውውር ሰጥቶ በተግሳፅ ከአንዴም ሁለቴ ነፃ ለቅቋቸው ነበር። መፈክር አለማንገባቸውና ድርጅት ከለላ ስር በመስራት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ቀደምት ሆነው አለመታየታቸውን ከትግል የራቁ አድርጎ ገምቷቸዋል። ለነፍስ እያደሩ ዓለማዊውን ህይወት እንዴት በትክክል ማራመድ እንደሚቻልና በ–ኢሰብአዊነትና ኦርቶዶክስን በመሻር የእመት ተመዝብራ ልጆች የሚደርስባቸውን ብኩንነት ያለመታከት በየጊዜው አስተምረዋል። አጎቱ አቶ ጎርብጤ ግን ደመ–ፍሉነት የሚያጠቃውና ግንባር ለግንባር እንደ ደጋ በግ የሚፈናከት በመሆኑ ቁምነገረኛነቱ በጠጪነትና በአመንዝራነት እያዋደቁበት

የእህቱን ክብርና አንድነት እንዳያስጠብቅ አድርገውታል። የእነዚህ የተለያዩ ታጋዮች መስዋዕትነትን ባለማዋደቅ እናንተው ነው ያላችሁት በርቱልኝ የሚሉት እመት ተመዝብራ ብቻ ነበሩ።

«እኔ ነኝና ተመዝብራ ይታጠቁ!» አሉ ብስጭት ብለው። «እኔ ሰውና በሰው ደረጃ የሚቆም ልጅ ያለኝ እየመሰለኝ፣ ደግሞም የእናት አንጀት ሆኖብኝ አላስችል ስላለኝ ነው እንጂ እንዲህ ዓይነት ፍፁም ጨልጦ የሚሟገት ልጅ አለኝ ብዬ ከቶውንም አላመንኩም። ይኸንንማ ጉድ ለማወቅና ለመረዳት የበቃሁት መልዕክት ለሌሎች እንድታደርስልኝ ነበር እንጂ እንደዚህ ዓይነት ሸምጣጭ ልጅ በጉያዬ በቤቴ ጓዳ ውስጥ መኖርክን መች አወቅሁኝና። ሰማህ የኔ ጉድ! አሁን ወደድክም ጠላህም የሚከተለውን ቃሌን ልብህን ከፊት አድርገህ አዳምጥ፤ ጆሮህም ይስማ፣ ዓይንህም ይይ፣ እግርህም አንዲት ስንዝር መሬት ከዚች ፈቀቅ አትል።» የእናቱ ምሬት እያየለ ሲመጣበት ደባልቄ ኩስምንምን አለ። «ከዚህም በላይ አልሰማ ካልክ ጡቴን አሽቼ ከርስት ጉልቴ እንዳትደርስ በማድረግ ልጅነትህን ከጄ የረገምኩህ እንደሆን መቅኖ አጥተህ ብኩን ሁነህ ትቀራለህ። የውጪ መሄዱንማ ነገር ፈፅሞ ካንጎልህ ፋቀው። ምነዋ ብትል፣ በዚህ ባለህ አስተሳሰብ እንደባህር ማሽላ ተበትነህ ከዚያ ተሰልጥኗል ከሚባለው ከተዛነቅህ በኋላ አንተን ለማጥራት ስለማይቻል ነዋ የኔ ጉድ!»

በእርግጥ ተስፋ እያጡበት ነው ወይንስ ስለአጎቱና ስለመምሬ የተገነዘበው ስህተት ቢሆን ነው እንዲህ ሳይታሰብ እሪ እንቧ ያሉበት። ወይንስ የሌሎች ወንድሞቹ ውድቀት ይሆን ይህንን ብሶት ያመጣው? እናቴ እናትህ አይደለሁም ብላ ካለች አገርና ዘመድ አዝማድ ያጣሁ መሆኔ አይደለም? ጎልውናዬስ ማን ያሰኘኛል? አዕምሮው በክፉ በትር ስለመታበት የማስተዋል ማኅደሩ በጥያቄ ያጣድፈው ጀመር። ቀልብ መግዛት አለበት፤ ማስተዋል አለበት። ደበሎ ለብሰው ጦር መዝዞ የማን ያለህ ያለውን በመስቀል ለማቆም የአምላክን ስም የሚጠሩና ብዝበዛን፣ ደም መፋሰስን፣ መለያየትንና ብጥብጥን በአደባባይ የሚያወግዙ መሆናቸውን እየተመለከተ ዕውር ሆኖ ይኖር እንደነበር አሁን ተሰማው።

ሰው ባህሪው ነው ወይስ አድራጎቱ መታየት ያለበት? መልካም አድራጎቱንስ መጥፎ ልማዱ ሊሰርዘው ይገባል? ወይንስ ከእኔ አመለካከትና ተመክሮ የተለየ በመሆኑና በትውልድ ልዩነት ዕምነቱን፣ ባህሉንና ሥርዓቱን ማዋደቅ ተገቢ ነው? የለውጥ አስፈላጊነቱና ትግል ማካሄዱስ የትኛው ላይ ለውጥ ለማምጣት ነው? ወይንስ የጉልቻ ለውጥ፤ የእኔ ይበልጥ ነው?

ኅሊናውን በጥያቄ ዑደት ውስጥ ነክሮ አሽከረከረው፡፡ ሌሎች በተለምዶና በሥርዓት ያስቀመጡትን እስከማይጎዳ ድረስ እንደ ዕንቁ አክብሮ መያዝ እንዳለበት ውስጡን ተሰማው። አደብ ገዝቶ ያልተገነዘበው ነገር እንዳለም የንቃት ደወል ከአብያተ–እመት–ተመንዝራ እንደ መረዋ ተሰማው።

«እማማ፣ ታዲያ ምን አድርግ ነው የምትይኝ? እሺ የምትይውን ልቀበል። አዎ አምናለሁ። *'እናት ለልጅዋ ስትል ተወጋች'* ይባል የለ። ስለዚህ እሺ እናቴ እማማ እንዳልሽ ደስ ይበልሽ። የምትይውን ሁሉ ለማዳመጥና ልብ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ።» አላቸው እናቱን ልጅነቱን በሚገልፅ ጥሞና እንደተደገፈ።

ድክመቱን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም ድክመት የተገነዘቡት እመት ተመዝብራ ግን በሃሳባቸው ፀንተዋል። አበውና አርበኛ ደጋፊዎቻቸውን ከጎናቸው አቁመው የልጃቸውን መስመር ለማስያዝ ቁርጠኛ ውሳኔ የሰጡበት በመሆኑ በአሻፈረኝነት ፍላጎታቸውን አዘከሩት። «ደባልቄ፣ ምክሬን ለመቀበል ከፈለግህ ወንድሜ ጎርብጤ ዘውአለና መምሬ መዓዛ ይርጉ መገኘት አለባቸው። ቀጥሎም ይሄ ያልጠራ አስተሳሰብህን በመንፈሳዊም ሆነ በጀግንነት ሥርዓቱን በሥርዓት እንድትወርስና ልክ እኛውን መስለህ የሚነገርህን መልዕክት ጊዜ ሳይሰጡኝ ጥበብ ይቅሰሙልኝ ብዬ የላኳቸውን ወገኖችህን ባህልና ስርዓት ምልክትም ያላቸው መሆናቸውን እንድታሰማ ነው። አዎ ለጊዜው ከዚህ ለመውጫና ለማምለጫ ብለህ እሺ ብትል ቃሌን ባዎንታህ ላይ ማኅተም ስለማደርግበት ባታደርገው ይበጅሃል። ካደረግከው ግን እንዲያው በነቁ ዓለም ውስጥ ባይተዋር ሆነህ ዕድሜ ልክህን ስትባንን ትኖራለህ። ልብ አድርገህ አድምጥ። በኋላ ካደረግከው አይ እናቴ ይህን ብላኝ ነበር በማለት ከመቆጨት እንድትታቀብ።»

«እሺ እማማ፣ አንቺም ሆንሽ መምሬ መዓዛ ይርጉ ወይንም አጎቴ ጋሽ ጎርብጤ ያላችሁትን ቃል ላንቺ ለውድ እናቴ ስል ባላምንበትም ተቀብዬ በሥራ ላይ እንዲተረጎም አደርጋለሁ። እመኚኝ እማማ። እሺ ካልኩ ሁልጊዜ እንደምፈፅም ታውቂያለሽ። ስለዚህ በፍፁም አትጠራጠሪ።»

ከዶሮ ጥፍር ውስጥ ቢገባ አልወጣም የሚለውን ቡና እየተመለከቱ *'የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው'* አሉ በሃሳባቸው። ሱሳቸውን አያበርድላቸውም። እንግዶቻቸውንስ እንዴት አድርገው ሊነፍጓቸው ይችላሉ? የችግርስ ማለቂያ የለውም? ጉድ ነው እኮ! በቡና አገር በሱስ ማረር። ምነው ሁሉ ነገር እየከዳቸው ይሄዳል? ልጆቻቸው በሃሳብና በቦታ ተበታትነዋል። ባላገርነታቸው ቀርቶ ባርነታቸውን አስመርጧቸዋል። በሰው አገር እንዴት ነፃ መሆን ይቻላል? ማኅፀናቸውን እንኳን እግዜር የባረከው ነበር። መፅሀፉም እንደዚህ እንደሚል በከፋቸው ጊዜ መምሬ ብዙ ጊዜ ነግረዋቸዋል። ይሄ የባዕድ ቋንቋ ገብቶ ነው እንዲያው ያመሳቀለባቸው። ሁሉም የየራሱን ባህሪ እያመጣባቸው። ድሮውንስ ከአህያ ጋር ጊደር ውላ! እህህ ብቻ ነው።

'ጉድ፣ ጉድ፣ ጉድ ነው! እንጨቱም ጭሱ በዛው፤ ከሰሉም አልቀጣጠል አለ። እግዜሩም ተዓምሩን በቁጣ ሆነስ ዘንድሮ የሚገልፀው።' እጃቸው እሳቱን ለማቀጣጠል ከሰሉን እየቆሰቆሱ ማራገብ ከጀመሩ ቆይተዋል። የክንዳቸው መዛል ሲሰማቸው አፍ አውጥተው ማማረር ጀመሩ። «ኢዲያ! እጄን ማራገቡ ታከተኝ። እንዲያው የዘንድሮ ከሰል ደግሞ ቶሎ አይቀጣጠል። እስቲ ውጪ ላውጣውና ነፋስ ያቀጣጥለው።»

እመት ተመዝብራ በጓዳ በር ሲወጡ አያ ጎርብጤ ዘውአለ በውሾችና በአህዮች ተደፍሮ አጥርና ከለላቸው በወደቀው ግቢያቸው ውስጥ እያቅራራ ይገባል። *«እንዴት ይዘለቃል ይህ አስከፊ ጊዜ፣ ከትዝታ ይልቅ ሲበዛ ትካዜ፤ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ልቡን ያራራቀ፣ ባጉል ፍልስፍና ከወገኑ ራቀ።»*

«እማዬ፣ አጎቴ ጋሽ ጎርብጤ መጣልሽ።» በመደነቅና እናቱን ለማስደሰት በመሞከር።

«ቤቶች! እረ እዚህ ቤቶች።»

ከጓዳቸው ሳይወጡ በሥራቸው ላይ ደፋ ቀና እያሉ «ግባማ፣ ግባ የኔ ጋሻ። ብርኩማው ላይ አረፍ በል። ደግሞ እንደ እንግዳ!» አሉት እመት ተመዝብራ በአዱኛ

ቅልጡፍ የመልዕክት አድራሽነት እየተደሰቱ። ይህን ጊዜ መምሬ እቤት ግባ ብለው ያላቸውን ጥሬ ሰጥተው ሥነ-ምግባሩን ካልመረመሩት እመንገድ ላይ ይሆኑ ይሆናል ሲሉ አሰቡ። እንዲያው ባላጣቸው ብቻ በማለት ትንሿን ፀሎታቸውን በውስጣቸው ደገሙ። ልፋታቸው ፍሬ መያዝ ይኖርበታል። እንዴት የብዙ እናት እንደ መካን ተረስታ ትቀራለች።

«ምነው ደህና? በደህናም አይደል እንዴ ያስፈለግሽኝ?»

*መምሬ ሳይመጡ የሚጀምሩት ነገር ባለመሆኑ፣ ነገራቸውን በማቃለል «እንዲያው ጥፍት ስትልብኝ ጊዜ እንድትጫወት ብዬ ነው።» ሲሉ መለሱለት።*

«አንተ ጎረምሳሳ ቀለሙን እንዴት ይዘኸዋል?»

«ይዘነዋል እየቀላ ነው አጎቴ።» አለ ደባልቄ። ድንጋይዋ በፀሃይ እየተጠበሰ እንደ ገመድ ጉተታ ወደ ፊት ወደ ኋላ እያለች የምታንጓትተውን የክር ማጫወቻውን እያስተካከለ። «ይህቺን ዜማ ሰምተሃል አጎቴ ጎርብጤ? በቴፕ ቀድቼ ያስቀመጥኩት ላንተ ብዬ ነው።»

«ያን አበድኩ ከነፍኩልሽ የሚለውን የዳንኪራ ዘፈናችሁን እንደሆነ እኔ ወላዲትን ልሰማው አልፈልግም።»

በስውር የተቀዳችና ውስጥ ለውስጥ የተሰራጨች የመንፈስ ማነቃቂያ የነበረችው ዘፈን ትሰማ ጀመር።

*ምነው ብታገስ ብችል መከራ፣*
*ማለቂ አይቀርም ሲሆን መራራ፤*

ያልጠበቀውን ነገር በመስማቱ አያ ጎርብጤ ቅብጥብጥ አለ። «ምን ዓይነቱን ቁም ነገር አገኘህልኝ። ድምፁን ከፍ አርገው። ኤዲያ! ድምፁን ከፍ አርገውና በቅጡ ልስማው።»

«ሰሞኑን ደግሞ በወረት የተያዘላቸው ዘፈን ይኸው ነው።» አሉ እመት ተመዝብራ።

«እጡብ ድንቅ ነው!» አለ እየተገረመ። «እንደዚህ ለዛና ቁምነገር ጣዕም ያለው ዘበናይ ዘፈን ሰምቼም አድንቄም አላውቅም።»

«እማርገጃው ላይ ሲረገድበት ይኸው ስንት ዘበን ሆነው፤ ካንተም ይኸው ተሰውሮ?» ከወንድማቸው የሚያመልጥ ወሬ መኖሩን እየተጠራጠሩ። *'እሱ እንደሁ ነጭ ለባሽ ይመስል እንኳንስ ያደባባዩን ቀርቶ የቤተመንግስቱን ሥረ ነገር ሁሉ ሳይቀረው ነው የሚያውቀው። ሳይማሩ እንዲህ ዓይነት ችሎታ ከየት ይገኛል? እግዜሩ ሲሰጥ ነው እንጂ! ሁሉን አሟልቶ አለመስጠቱ ለምክንያት ቢሆን ነው እንጂ ማን ይችለው ነበር?'* ይላሉ በየጊዜው ስለ እሱ በአድናቆት።

«በናንተ ጊዜ የፍቅር ሆያ ሆዬ የለም ነበር ማለት ነው?» አለ ደባልቄ አጎቱን ለማስለፍለፍ ብሎ።

«ወግ ማዕረግ ነበረው። እንደ ዘበኑ ለዛውን አላጣም። አሁንማ በያደባባዩ ከንፈር መመጣመጥና ከንፈር ማሞጥሞጥ ሆኗል።»

«ተው ተው ሰደብከን እኮ!»

«እውነት መናገር ፍቅርን አያጠፋም።»

«እንዲያው ምን ይሆን ልብህን የሚያረካው ወንድም ጥላ።» እመት ተመዝብራ መደነቃቸውን አያቆሙም።

ደባልቄ ቴፑን ዘግቶ ሬዲዮኑን ከፍቶ ስለነበር የሚከተለውን የሬዲዮ ተናጋሪው የሚያስተላልፈው ይሰማል።

*'በሞቱ ላያዝን ደስታው አድርጎለት፣*
*ለገዳይ ሰጠው ደረቱን ከፍቶት፤'*

ይሄ የሰው ልጅ ደሙ የተሰኘው ዜማ እንጉርጉሮ ነው።

*'ባይደረስ ርቀት ዘመድ ወገን ርቆ*
*በትዝታ ሽታ ባዘን ተጠላልቆ*
*ባለሁበት ቦታ ልቤ መቼ ረግቶ*
*ባሳብ ይጓዛል ብቸኝነት ጠልቶ።*
*በትዝታ ጉዞ ድንበር ሳይወስነው*
*ልቤና ሃሳቤን ዕረፍት እየነሳው*
*በሀሲና ሙግት ተሟግቼ አልረታው*
*ካልተደረሰበት ሃሳብ መቃብር ነው።'*

አያ ጎርብጤ በጥሞና አዳመጠ «በሀሳብ የሞተ ሰው መርዶው በዓመት ነው የሚደረሰው።» ሲል አርጎመጎመ። ራዲዮኑ በመቀጠልም «ቀደም ሲል የሰማችሁት 'ሃሳብ መቃብር ነው» ከተሰኘው ዜማ የተገኘ ግጥም ነው። በመጨረሻ ላይ የሰማችሁት።

*ስርዓት ባህሌን ወግ ማዕረጉን ትቼ*
*ብይዘው አያምረኝ ለባዕድ ተረትቼ*
*ማመዛዘን ካልቻልኩ እራሴኑ ትቼ*
*ተንጠልጣይ አልሆንም ካልተቀበርኩ ሞቼ፤*

የሚል ነበር። አሁን ደግሞ «የሰው ልጅ ዋናው ፍላጎቱ» የተባለውን ዜማ ከዚህ ቀጥለን እናሰማችኋለን። ዜናም በስተመጨረሻ ይተላለፋል።» ሲል አበሰረ። የከሰለችው ባትሪ ጉሮሮ እየተናነቀች በጣር ሞቷን ስታሰማ ደባልቄ ዘጋት። አያ ጎርብጤ ደጅ ደጁን ሲመለከት የመምሬ መዓዛን መድረስ ያስተውላል።

«እኒያ በሩቅ የሚታዩት መምሬ መዓዛም አይደሉ እንዴ?» አያ ጎርብጤ ነበር።

እመት ተመዝብራ ሥራቸውን ቆም አድርገው ወደ ውጪ እየተመለከቱ «አሁን ነበር ልጅ የላክሁባቸው፤ እንዴት ፈጥነው ደረሱ ልጄ!» አሉ። መምሬ መዓዛ ከቤተክርስቲያን የተበተኑትን ምዕመናን እያሳለሙና እጅ እየተነሱ ሲመጡ ይታያሉ። ደባልቄ በሚያተኩርበት አካባቢ በግልፅ አይታዩም።

«የት ነው ያሉት?» በአትኩሮት ወደ ውጪ እየተመለከተ ጠየቀ፤ ደባልቄ።

«እንዴ ምን ነካህ! ኧረ እኛውልህ እዚያ ማዶው ላይ ህዝቡን እያሳለሙ እየመጡ አታያቸውም እንዴ!» አነጣጣሪው ዐይኖቹ በዚህ ዕድሜው በውሃ ውርጃ ቢጋረዱም ጨመቅ ጨመቅ ሲያደርጋቸው ጠራ ብለው የሚያየውን ሁሉ እንደ ስዕል ቀርፀው ያሳዩታል።

መምሬም «ወይ ሊቀ መላክ ቅዱስ ሚካኤል ምን ታሰማኝ ይሆን?» እያሉ እያማተቡ እንዳይደረስ የለም ከእመት ተመዝብራ ቤት ደረሱ። «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።» በማለት ካባቸውን ገለጥ ነጠላቸውን ሰብሰብ አድርገው መስቀላቸውን ከኮት ኪሳቸው ውስጥ ካወጡ በኋላ መዳረሻቸውን ሁሉ እየባረኩ ከበሩ ደረሱ።

«እንደምን አሉ መምሬ፣ ይግቡ። እስቲ ይባርኩኝ።» አሉ እመት ተመዝብራ ብረካው ዘግይቶ እንዳይቀርባቸው ወይንም አለቀ ተብለው የሚከለከሉ ይመስል በመሽቀዳደም። የመምሬም እጅ መስቀሉን ከአፍ፣ ግንባር፣ አፍ ጋር እያዛመዱ «እግዚአብሔር ይባርክ ወያብርህ ገፅከ!» አሉ። የደባልቄንም ይሁን የአንዳንድ ወጣቶችን ከአበው እምነት መራቅን ቢያውቁም መስቀሉ ወደ እምነቱ ይመልሳቸው ይመስል ሳይደባብሷቸው

አያልፉም። «አንተ ጎረምሳ አትባረክም እንዴ?» ተግሳፃቸው እመት ተመዝብራንና አያ ጎርብጤን በማያስከፋ ለዛ የተመጠነ ነበር።

መውጫ የሌለው ደባልቄ በእምነት ሳይሆን ላለማስቀየም እጆቹን ወደ ኋላው አጣምሮ ዲላማውን እንዳገኘ ቀንድ ከመስቀሉ ጋር ግንባሩን አላተመ። «ይባርኩኝ መምሬ።»

«እግዚአብሄር ይባርክ ወያብርህ ገፅከ»

ይህን ጊዜ የስንቱ ውብ ወይዛዝርት ከንፈር የላሱት መስቀል ነው ሲል አሰበ። የጉንፋናሙን ሌላውም። እንደመፀየፍም ቃጣው። እንዳይታወቅበት የራሱን አስተሳሰብ ተቆጣጠረው።

መምሬ እመት ተመዝብራ አዘጋጅተው ያቆዩቱን ውሀ ተቀብለው በመባረክ ቤቱንም እነሱም ላይ ይረጫሉ። እመት ተመዝብራም ከመረጩት የተረፈችውን የተባረከች ቅድስት ውሀ በክብር በመቀበል «ይህቺን ደግሞ ለቦሃቃዬ!» አሉ ወደ ጓዳቸው እያመሩ።

«ምነው በደህናም አይደል ያስፈለጉኝ?» አሉ መምሬ፤ ከተዘጋጀላቸው የክብር በርኩማ ላይ ጉብ ብለው። በብዙ ሃሳብ ሲብከነከኑ ነበር ከዚህ የደረሱት። ቻይና ታጋሽ እንዲሁም መላ አዋቂ ከባድ ችግር ባይደርስባቸው ከቶ አይልኩብኝም ሲሉ አሰቡ የማያውቁትን ኃጢአት እመት ተመዝብራ ሲናዘዙላቸው ለመስማት ጆሮና ልቦናቸውን በሙሉ አቁመው። የእያንዳንዱ ሰው ስብዕናው፣ ልዕልናው፣ ኃጢአቱም ስነልቡናው በእሳቸው አዕምሮ ማኅደር የተመዘገበ ነበር። አሁን ደግሞ በስውር ልብ ውስጥ ተቀብሮ የነበረው ሊነገራቸው ነው። ዓለም የማያውቀው ምስጢር ሊገለፅላቸው።

«ደህና ነን። እንዲያው ለጥቂት ፍሬ አዘል ምክክር ያባታችንን መኖር ስለፈለግን ነው።» ቅስማቸው ውድቅ አለ። ከባድ ምስጢር አይደለም ለካ ሲሉ አሰቡ መምሬ። ደባልቄ ደግሞ የእናቱን ሀሳብ ለማደናቀፍና አቅጣጫ ለመቀየር የጥያቄ በትሩን ወደ መምሬ ወረወረ። «መምሬ፣ ወያብርህ ገፅከ፤ ወያብርህ ገፅኪ የሚሉት ቃል ምን ማለት ነው?»

«አንተ ዝም አትልም እንዴ!» የደባልቄ አጠያየቅ ከከረረ ክርክር ውስጥ ከትቷቸው መምሬን በማስቀየም እመት ተመዝብራን ላለማስገመት ሲል አጎቱ አያ ጎርብጤ በቁጣ መልክ ለማቋረጥ ሞከረ።

እመት ተመዝብራንም ያስደሰታቸው ስላልሆነ ተግሳፃቸውን አሰሙ። «እስቲ እህል ውሃም ሳይባል የምን ልብ ማድረቅ ነው።»

ታጋሽና አስተዋይነታቸውን ለማስመስከርና ደባልቄንም ቅር ላለማሰኘት መምሬ ነገሩን ቀዝቀዝ ለማድረግ ሞከሩ። «አይ ግድ የለም ይጠይቅ። መጠየቅ እኮ ነውር የለውም፣ እመት ተመዝብራ።» ለስላሳው አንደበታቸው የመላዕክትነት ባህሪይ ያለው ነበር። እመት ተመዝብራ በጣሳ ጨልፈው ያመጡትን ጠላ ከብልዟ ብርጭቋቸው ውስጥ ቀድተው ከላይዋ ላይ በእፍኛቸው ጠብ ካደረጉ በኋላ ቀመስ አድርገው «እስቲ ቡና እስኪፈላ ድረስ ይህችን ያልፈላች ጠላ ይቅመሱ። ውሃ ጥም ትቆርጣለች።» ብለው ለመምሬ ሰጧቸው። «እንካ አያ ጎርብጤ» አሉ በተራው ወደ እሱ ዞረው።

መምሬም ጠላዋ ለውይይት መቆያ መሆኗን ወዲያውኑ ከቀመሱ በኋላ ስለጣመቻቸው «ማለፊያ ነው።» አሏቸው በተባረከ እጃቸው የተጠመቀው አንጀታቸውን አሸሮት። ወደ ደባልቄ ጥያቄም በመመለስ «እግዚአብሔር ይባርክ ወያብርህ ገፅከ ወይም ገፅኪ ማለት ሁሉን መለገስና መማር የሚችል ኃይል ይህም ማለት እግዚአብሄር የሰማይና የምድር አምላክ ሁሉን ይቅር ይበልህ። መንፈስህ የጠነከረ እንዲሆን የእርሱ ረድኤት በገፅህ ላይ ሰፍሮ የሚፃረርህን ሁሉ ይግታልህ ማለት ነው።» ሲሉ ተነተኑለት።

«የጠለቀ ምስጢር ነው አባቴ።» አለ ደባልቄ ውይይቱን ለማጋጋል በመፈለግ። «ሁሉም እንዲህ እያሉ ይህንንና ሌላ ሌላውን በስርዓት የሚገልፁ ካህናት በርከት ቢሉ ኖሮ ይኸ ሁሉ ምስቅልቅል ባልተፈጠረም ነበር።»

ጠላውም ከገነት በር የሚመልስ ጣዕም አለው። በጥያቄና መልሱም እየተደሰቱበት ነው። የስምንተኛውን ሺህ ፈተና ለመውሰድ ዝግጁ መሆናቸው ተሰምቷቸዋል። የእመት ተመዝብራ ጉዳይም የከበደ ቢሆንም አጣዳፊ አለመሆኑን አውቀዋል። «ሌላስ ጥያቄ አለህ ወይ?» አሉ መምሬ መዓዛ የጨበጧት ብርጭቆ እጃቸው ላይ እያሳበቀችባቸው። እመት ተመዝብራ ከጓዳ ሆነው በመጣራት ለደባልቄ ትዕዛዝ ሰጡት። «ደባልቄ የጎደለውን እያየህ ሙላ።» እንዴት ከጓዳ ሆነው እንደታያቸው እየተገረመ የታዘዘውን ያደርጋል።

«እሺ እማማ። አዎ ከፈቀዱልኝ አንድ ሁለት ጥያቄዎች ነበሩኝ።»

«በላ።» አሉት ጠላውን በአክብሮት አጎንብሶ ሲቀዳላቸው ዐይን ዐይኑን እየተመለከቱ።

«ብዙ ጊዜ በዓል ለምን በዛ? አምላክ ይህንን ዓለም ሲፈጥር በመካከሉ በዓል አለ እያለ አላረፈም። ሁሉን ሰርቶ ከጨረሰና ከፈፀመ በኋላ ቅዳሜን ብቻ ነው አከበረ የሚለው መጽሀፍ ቅዱስ። ሌላው ደግሞ ሰው ደግሶ ካላበላ ሊፀድቅ አይችልም፣ ለበላዮቻችሁ ታዘዙ የሚለው ቃል ከየት ነው የተገኘው?»

«ጥሩ ማስተዋልን አድርገሃል።» ያውቃል ግን አልተከሰተለትም። ደግሞም ነገሩ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊወስድ ነው ሲሉ አሰቡ መምሬ፤ መውጫ ስልታቸውን ሞርደው እያቀረቡለት «ግና ሁሉንም በዛሬው ዕለት ልገልፅልህ የማልችልበት ምክኛት እመት ተመዝብራ አስጠርተውኝ ለመጣሁበት ጉዳይ ልወቅና በሰፊው ጊዜ ወስነን ጥያቄዎችህን ሁሉ እመልስልሃለሁ።»

«አመሰግናለሁ መምሬ። ሃሳቤን በመቀበልዎ ብቻ በጣም ገርሞኛል። እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ ብዙውን ጊዜ የምናያችሁ ጥያቄ ሲቀርብ የማትመልሱልን እንዲያው በደፈናው ብቻ እንዳባቶች ተቀብላችሁ እመኑ የምትሉ መስሎኝ ይሰማኝ ነበር። በዛሬው ዕለት ይህንን ዓይነት ገለፃ ከርስዎ ዘንድ በማግኘቴ ከመገረምም አልፎ አስደንቆኛል። አስደስቶኛልም።»

«አይ ልጅ፤ መደማመጥ፣ መጠየቅና መረዳት በሁሉም አቅጣጫ መስመሩ ልቅ ቢሆንማ ይኸ ሁሉ ሥርዓት ማጣት መች ሥር በሰደደ ነበር? ይኸ ሁሉ የሆነው የአንድነት ማጣት ነው። ሃይማኖት አንድ አምላክን ማመን ሆኖ ሳለ የሰው ልጅ የተለያየ ጠባያትን በመፍጠር፤ በሃሳብ ላለመገናኘት ሲል ብዙ ቅርንጫፍ በማብዛት ብዙ ውስብስብ ነገሮችን መሰረተ። ከይህም መሰረት በመንደርደር የእኔ ይበልጥ የእኔ በማለት አንዱ የአንዱን የሚያንቋሽሽበትን መጥፎነት ሲፈልግ አንድነት የሚባል ቃል ተጨልጦ ጠፋ። በተረፈማ ትዕዛዙ በጣም

ቀላል ነበር። እሱም ባቄሩ በራስህ ላይ ሊደረግብህ የማትወደውን በባልንጀራህ ላይ አታድርግ ነው የሚለው ባቄሩ።» ደባልቄም የመጣባቸው አዝማሚያ ስህተት ጠቆም ለማድረግ «ግና ሰው ግብዙ ያን ትቶ ብዙ አዲስ ጎዳና በመቀየስ ህዝበ-አዳም ያለመስመሩ ገብቶ ይማቅቃል።» በማለት አቀቡት።

የሾለው የደባልቄ አፍ ሌላ ነገር ሳይተነፍስ የመምሬን ግምገማ እንደ መግቢያ አንተርሰው እመት ተመዝብራ ትኩረት ወደ እሳቸው እንዲዞር በነገር ጥልቅ አሉ። «መምሬ እርስዎና ጎርብጤ እንድትገኙልኝ የፈለግኋችሁ ለብርቱ ጉዳይ መሆኑን አምናችሁ በቁምነገረኛነት ስለመጣችሁልኝ አመሰግናለሁ። ፍሬ ቁምነገሩም ይኸው የመደምደሚያው ልጄ ደባልቄ ለትምህርት ወደ ፈረንጅ አገር ለመሄድ ስለተነሳ ከናንተ የጠለቀ አጥንት ጠልቆ የሚገባ ምክር፣ ሥነምግባር፣ የአገሩን የእትብቱን መቀበሪያውን ታሪኩንና ባህሉን ሟጥጦ እንዳይጥለውና ከዚያ ቀጥሎ ይኸው ሁላችሁ እንደምታውቁት በየውጪው ዓለም የባንኑ ወንድሞቹንና እህቶቹንም አዕምሮና ልብ የሚያስገዛ ምክራችሁን እንድትለግሱልኝ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ከዚያ ከባህር ማዶ ሁሉ ያሉትንም የሚያስተባብርና የሚያፋቅር የእናትነት ምክሬን፣ በደሌን በናንተው ፊት ለመናገር ያሳሰበኝ ቃሉ ሁልጊዜ ማኅተሙ ሆኖ እያንዳንዳቸው ህሊና ቀልብ ላይ እንዲሰፍን ብዬ ነው። ከዚህ የሃሳብ ኮርቻ ላይ የወጣሁበትም ምክንያት ይኸው ጉልበቴም ሲደክም፣ ኃብቴም ሲባልል ሰብሳቢ እያጣሁ በያቅጣጫው ወማ ውጦት እንዳይቀር ትምህርታቸውንም የጨረሱት ፊታቸውን ወደእኔ እንዲመልሱ፣ መቼም ቢሆንምና ቅሉ የትምህርትና የውሃ ማለቂያ የለውም። እንዲያው ዕልባት ተደርጎበት ባለው ዕውቀት ካልተጠቀሙበት ገና ነን የሚሉት ደግሞ ልቦናቸው በጅል ነገር ሳይለከፍ ለወጡበት ዓላማ የዕውቀት ገበያቸውን አሽማመቱን ለማወቅ የሚረዳቸውን ትብብር፤ አንድነትና ፍቅር፣ ውልን አለመዘንጋት በየግል ኅሊና ማኅደራቸው ከትበው እንዲይዙት በማለት ነው።» ችግርና ሀዘናቸውን በተናገሩ ቁጥር ናፍቆት፣ ብቸኝነትን መንገላታታቸው እየታያቸው ብሶት ስላመጣባቸው ድምፃቸው እየተቀየረና የሀዘን እንጉርጉሮ እያሰማ መጣ። «በተረፈስ እንዲያው የወላድ መካን መሆኔ ነው። ይኸው ከዚህ ያሉትም መፋቀር የሚባለውን መስመር ስለዘለሉ እርስ በርሳቸው በተሸናቆሩ ቁጥር የእናትነት ሆዴ አልችል እያለ እንዳያይ ዐይኔን አሞቅሙቆ ማያ ብርሃኔን ሊያሳጣኝ ነው። እንዲያው በጣም ምርር ብሎኛል።»

«እንዴ ይተው እንጂ የምን ልቅሶ ነው? ነውርም አይደል! የጀግና እናት እኮ ጀግና ናት!» አሉ መምሬ በመገሰፅም፣ በማሞገስም።

የእመት ተመዝብራ አንደበት እንጉርጉሮውን ከማሰማት ወዲያው አልታቀበም። «አይ የወላድ መሃን መሆኑ መሮኝ፣ እፀልይ ነበረ ልጅ እንዳላገኝ፣ የባሩድ ወላፈን እያፋጨብኝ፤ አይ መች በዚህ ብቻ፣ የወጣት ገበያ ነጪ በልቶብኝ፣ ያስቆጨኝ ጀመረ ልጅ ዓለም ጠፍቶብኝ።»

«በቅዱስ ሚካኤል ይገፎዎታለሁ፤ አልያ እገዝትዎታለሁ።» ለነፍሳቸው የሚያድሩትን ብሶተኛ ዕንባ ለማድረቅ ያቀረቡላቸው መሃረብ ነበር። «እመት ተመዝብራ የሚሉት ከቶ አንዱም መሬት ጠብ አይልም። ተቀባይ፣ ሰሚ፣ አመዛዛኝና ተቆርቋሪ ፍሬ ካለ።» ቁም ነገሩን በቁም ነገር በመግፋትም ጥሞናው መለከታዊነት ባለው ቅኝት መቃኘት ጀመሩ። «ለይኸም ታላቅ ኃላፊነት ምክርና መልዕክት እኔና ጀግናው፣ ሃቀኛው፣ ደፋሩና ሃይማኖታዊው፣ የአበው አባቶችን ወኔ የወረሰው፣ ተግባራትን በድርጊት የሚገልፀው፣ ያልተስተካከለ ፍርድ በወገኖቹ ላይ ሲያይ በዕውቀት በር ላይ የሚደቀነው የሃሳውያንና የእኩያን መድፍነ-ጦር የሆነው የወንድምዎት የአቶ ጎርብጤ ዘውአለ መገኘትም ምን ያህል ታላቅ አነፃፃሪ መሆንዎን በመገንዘብ ሁላችንንም በአርዓያነት ያስተምረናል።»

አያ ጎርብጤ በሙገሳው አካሉ ሲያብጥና በኮቱ ላይ የደረበው ነጠላ እንደተነፋ ፊኛ ሲወጠር ይታያል። ከተቀመጠበት ብርኩማ ላይ ግርማ ሞገሱን ደርቦ መቁነጥነጥ ጀምሯል።

«አይ መምሬ፣ ያለእርስዎና ያለጎርብጤማ ምኑስ ከምን ሁኖ? ሃይማኖትና ሥነ-ምግባር ጠቀስ ካልተስተካከለ ልክስክስ ስራ ሆኖ ጎርበጥ የሚል ከጠፋማ ስሜ ከመዝገቡ መፋቁ ነው። ያላችሁኝ ከፈጣሪያችን በታች እናንተ አይደላችሁ።»

«እኔም ሆንኩ ሌሎች ቅዱሳን መናንያን ኑሮአቸውን በበረሃ ካራዊት ጋር ያደረጉ፣ ይህችን ቀጣፊ ዓለም መዝባሪነት የጠሉ፤ ሰርክ ኅብስታቸው ቅጠላ ቅጠል፣ ትራሳቸው ድንጋይ የሆኑ፤ እንዲሁም አበው የገዳም መነኮሳትና የደብር ካህናት በሙሉ በየፀሎታቸው ምዕራፍ ይሄ በህብረ-ሰብእ ላይ የተጫነው ቀንበር እንዲለዝብ፣ የማይለዝብ ከሆነ ከዚያው ከጥንተ ቦታው ይመልሰው እያልን ምህላችንን ወደ ፈጣሪያችን እያሰማንልዎት ነው። እርስዎ እመት ተመዝብራ ከሌሉ የሁላችንም ዓይን መጨለሙ ነው።»

«እስቲ ቃላችሁን ቃለ ህይወት ያድርግልኝ፤ በቃሽም ይበለኝ። በዚህም ሆነ በባህር ማዶ ያሉትን ፍሬዎቼን ባንድነት አፋቅሮ ለቁምነገር ያብቃልሽ በሉኝ። አደራችሁን፤ የእኔንስ ፀሎት እግዜሩም የሰማው አልመሰለኝም።» የእመት ተመዝብራ ምሬት ከልጃቸው ከደባልቄ ድፍረት የሚተናነስ አልነበረም። መለኪያ ቢገኝለት።

ከአምላክ መራቅና ማማረር ቅስፈት ስለሚያመጣ መምሬ ቶሎ ብለው የእመት ተመዝብራ ልብ ከአምላካቸው እንዳይሸፍት ሊገሩት «ፈጣሪያችን እኮ አይቸኩልም ለቁጣውም ሆነ ለምህረቱ እመት ተመዝብራ።» አሏቸው ለእመት ተመዝብራ።

በጥሞና ሲያዳምጥ የቆየውና የመልዕክቱን ፍሬነገር የቀሰመው አያ ጎርብጤ ከተቀመጠበት ተነሳ። «መምሬ መዓዛ ይርጉ!»

«ቁጭ በልና አማክረን እንጂ፤ ለእግዜሩም ይከብድ የለም እንዴ!» ፋታም አልሰጡት መምሬ አክብሮቱን ጠልተውት ሳይሆን በቅን የነፍስ አባትነት።

«አመሰግናለሁ አባቴ።» አደግድጎ ከቆመበት እጅ ነስቷቸው ከመቀመጡ በፊት ወደ እህቱ ዘወር በማለት፤ «እቴ እመት ተመዝብራ ይታጠቁ፤ እንዲሁም ለዚህ ስብሰባ ውል የሆንከው ደባልቄ ቢወጣ፤ እኔስ በከንቱ የምለፈልፍ የገደል ማሚቶ ሆኘ የቀረሁ እየመሰለኝ አያሌውን ጊዜ ሆዴ እንደመሮጥ፣ ልቤም እንደ መሳት፣ መንፈሴም እንደ መሸበር ሊያደርገኝ ሲከጅለኝ ሁሉንም እተወውና ወደ ውሃው መንደር እኮለኩላለሁ። ከዚያም

ንዋዬ የፈቀደችልኝን ያህል ስሮቼ እስኪርሱ ከጠለቅሁ በኋላ ነገር ዓለሙን ሁላ እንደመርሳት የቅፅፈትም ዓለም አጭር ደስታ እንደ ነህሴ መብረቅ ብልጭ ድርግም ባይምሮዬ ይልና ሌላ ሌላ ጅል ስራ ማለትም እሽክም እስክስታ፣ መዳራት ወደ ደመቀበት መሄድና ሂድ ተዘነቅ ተዘነቅ የሚለኝ የኩይ መንፈስ ይገፋፋኛል። አይሂሂ፣ ይህስ አይሆንም እልና በግራ በኩል ያለችውን የጁባ ኪሴን ስዳብስ ነዋዬ ተሟጣለች። አይ እስቲ ድንገት ብዬ ደግሞ በቀኝ በኩል ያለውን ብሞክር ከነጭራሿም ተቀድዳ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ማስታወሻዎቼን ሁሉ አጥፍታለች። አይሂሂ! ድሮውንስ የሚሰማኝ ባጣ ነው ከዚህ ሁሉ ድንግዝግዝ ውስጥ የተጨመርኩ ብዬ ወደ ምርፋቄ እቀይሳለሁ።»

ውስጠ–ወይራ አባባሉ ደባልቄን ጥልቅ ካለ የሀሳብ ውዥንብር ውስጥ ጥሎታል። በሚያውቀው ቋንቋ የተነገረው ነገር እንዴት እንደማይከሰትለት ብቻ ሊገባው አልቻለም። «ለምን እንዲህ ታደርጋለህ አጎቴ?» ሲልም የጠየቀው ጥያቄ አላዋቂ አድርጎ አስገመተው። ለዚሁም ታዛቢው እናቱ ነበሩ።

«አይ የልጅ ነገር። እኔ ብዙ የሰለጠንክና ጠልቀህ የምትመራመር ይመስለኝ ነበር? ይህንን አጥተህ ነው?» አሉት በስላቅ።

«ነውር የለውም ይጠይቅ፤ እመት ተመዝብራ።» መምሬ ነበሩ በአስታራቂነት እንደበታቸው ገለፃ ውስጥ የገቡት። «መጠየቅና መረዳት ሾላ በድፍኑ ከመሆን ያድናል። ደግሞም መመራመርና መጠየቅ የብልህ መስተዋት ስውር ዓለም ነች። እንዲያውም ይሄ ደባልቄ ልጅዎት በጣም፣ በጣም፣ በጣም ብልህ ነው። ጥያቄዎቹ ሁላ እናት ይሰረሰራሉ።»

አያ ጎርብጤ ግን የእመት ተመዝብራን ሃሳብ በመደገፍ ትንተና ውስጥ በሙሉ ስሜት ገባበት። «ይሄ ሁሉ መታመስ፤ እውነት ተሸጣ፣ ሃሰት ሰፍና፤ ታሪክ ያባቶቻችን ስምና ባህል፣ ቅርስ ከስረ–መሰረቱ እየተፋቀ የተውሶ ስምና ወኔ ለማጥለቅለቅ የሚደረገው ያድርባይነት እሽቅድምድም አይከሰትልህም? ለሀቅ የቆሙት፤ በነዚህ አምሴዎች የተቀሉ፣ የታመሱና የታጨቁ እንዲሁም የዛጉትን ከምንጊዜው ረሳሃቸው? ኧረ አትዘንጋቸው! ምልክትህም አድርገህ ለዘላለም በህይወትህ እስከምትኖርበት ዘመን ድረስ አስታውሳቸው። ላንተም፣ ለኔም፣ ለሌሎቹም ምልክት አድርገን ለትውልድ ሳንዘነጋ በየግል ማንተማችን እንሰራቸው። ለትውልድም መልካም ስራቸው እንዲታወቅላቸው ምልክትህን አትዘንጋ! ስንል እንዲታወሱ እናስባቸው። አህ! ዓለም ዘወርዋራ ጊዜ ዘበናይ፤ በድርቅ ገባሁ ብላ በባሩድ ቀንጣይ። በዕዳ ባሩድ ደማቸው ለሃቋ የፈሰሰ፤ ሰብዓዊ ክብራቸውን በገዛ ወገናቸው በእናታቸው ቤት መኖሪያ ያጡ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ፈጣሪያቸው አቤቱታ በማቅረብ ላይ ናቸው። እውነትና ንጋትም እያደር ይገለጣል። አንተ ግን አስተዋይ ልጅ እንደምትሆንና ታሪክ እንደምትፅፍ ተስፋ አደርጋለሁ።»

«አይ የእኔ አለኝታ! እስቲ እንዲህ እያልክ አስረዳልኝ። ባይሆን እሱ እንኳን ወኔ ቢጫነው።»

«ፈጣሪያችን ልቦናውን ይክፈትለት እንጂ እኔስ ካባቶች የወረስኳትን ወኔና ሁነኛውን ሃቅ እንዲከተላት አስረዳለሁ።»

«እመት ተመዝብራ ያለዎትን መልዕክት ይግለፁልን።» መምሬ የነገሩን ግለት ለማብረድና ጥሞና ባለው መልክ ለመወያየት የሰነዘሩት ነገር ነበር። ለደባልቄና ለአያ ጎርብጤ ግን ሁሉ ነገር ተገልፆ ነበር የታያቸው።

«እሺ። በመጀመሪያ ስርዓቱን እንዲያውቅ ብሶቴን ከእናንተ ይረዳና ከዚያ እገልፃለሁ ብዬ ነው።»

«እማምዬ፣ ብሶትሽን እኮ ከልቤ ከምሬ ነው የምናዘዝልሽ። እማምዬ አውቃለሁ፤ የፈፀሙትን ያረመኔ ሥራ አስተውላለሁ። ግን ያንቺን ሆድ ላለማባባት ስል ነገሩ ሁሉ የማይገባኝ ቂል ጅል ሰው በመምሰል አሳልፈዋለሁ። በተረፈማ ነገሩን ከቆረቆሩት በናይምሬ እጅ እጠለፍና ማር እንደሞላበት ስልቻ እለፋለሁ። ለዚሁም ሞኝ አኗኗሬ ስንት ቅቤ አንጓች ይመለከተኛል። ኧረ እማማ ግድ የለሽም ብሶትሽን ተረድቼዋለሁ።»

«ተመስገን ፈጣሪዬ ሰማያት ወምድር አንት የማያልቅብህ ጌታ።» አሉ እመት ተመዝብራ ልጃቸው የቆፍጣናው ወንድማቸውን ወኔ ይዞ ለዘብ ባለ መልክ ሃሳቡን ሲገልፅ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰሙ ነሸጥ አድርጓቸው። «ለካ እንዲህ ኖሯል ደባልቄ የሚያስበው?!»

«ልጁ እኮ ብልህ ነው ፈጣሪያችን ይባርክልን እንጂ።» የአምላክን ስራና ታምር ለማስገንዘብ ዘወትር የሚጥሩት የነፍስ አባታቸው ፋታም አልሰጡ አድናቆታቸውን ሲገልፁ።

«ደባልቄ ልጄ ሆይ! አሁን ልብ አድርገህ አድምጠኝ፤ መልእክት የምነግርህ ስለሆነ። መልዕክቱ ከባድ አይደለም። ከዚህም የተነሳ ብዙ ሀተታ የለውም። ለዚሁም እንዲቀል ብዬ ባንድ ሀረግ ላይ አልቤዋለሁ። ‹የትም ሆንክ የትም ምልክትህን አትዘንጋ! አትዘንጋ!› ነው እምልህ።»

«እሺ እማምዬ። ይሄንስ ራስ ሀረግ እኔም እስከ ህይወቴ ድረስ ወርሼ ለሌላውም አወርሳለሁ። በዚያ ላሉትም በሙሉ ልብ አድርገው ከሰሙኝ እነግራቸዋለሁ።»

«ቆይ አልፈፀምኩም። ከዚህ ስር የሚቀጥለውን አያይዘህ አሰማቸው። ለጥበብ የወጣህ፣ ባለህበት ቦታ ሆነህ ፍቅር የነሳህ፤ የገበየኸው ጥበብ እኔን ለመቆራረስና ለመገነጣጠል ልብህን ያሳበጠህ ወጭት ሰባሪ ሁሉ እባክህ ልብ ግዛ። ከያገሩ የተሰረቀው ጥበብ ባለህበት ቢሰፍንም በቅጡ ካልመረመርከው መገነጣጠል ቀርቶ ሊያጠፋህም ያደባል።»

«እሺ እማማ።»

« ‹ዛሬስ ታድያለሁ፣ አንተን ስላገኘሁ መልዕክቱን ልኬአለሁ፣ እናትም ለመሆን እጄን ዘርግቻለሁ፣ ፍቅር የናጣቸው ልጆች ፈልጌአለሁ። ሀረጉን ሲመዝዙት ዛፍ ይወዛወዛል፤ ፍቅር የሌለው፣ አንድነት ያጣ ልጅ ሃብት ያስበዘብዛል።» እንዲያው ደህና ጊዜ እስኪመጣ እያሉ ዝም ብሎ ማየትና ማሰብ በጣም ያስወቅሳል። ለማይሆን ጅል ነገር፣ ለመልካም ነገር፣ ሁልጊዜ፤ በክፉም ጊዜ፣ በደስታውም ጊዜ አብሮ በኅብረት ሆነው ካልደከደኩት በቀር ማገጥ ዓይነት አረም ያበቅልና ሳራሚው ሁላ ያስቸግራል። ይሄ ነው መልዕክቴ የኔ ልጅ።» በግጥምም በዜማም አካላቸው እንደ ቅቤ እየተናጠ ደስታቸውንም መልእክታቸውንም አሰሙ። ቀድሞ ይተናነቃቸው የነበረው ዕንባና ብሶት ወደ ተስፋ ተለውጦላቸዋል።

ደባልቄም የተስፋቸውን ሀረግ «እሺ ጊዜ አጣን እያሉ ምክንያት ካልሰጡ እማምዬ ያልሺውን በሙሉ

አሰማለሁ።» በማለት ቋጠረላቸው። ነገር ግን ይህ ብቻ አልነበረም ከእሱ የሚጠበቀው። ሌላ መልዕክት አለ። ኅብረት ብቻ አይደለም ልጆቻቸው የተጠየቁበት። ታሪክንም ማስታወስ ይጠይቃል።

«አሁን የምትሄድበት ቦታ» አለ አጎቱ፡ አያ ጎርብጤ የጠፉትን ትውልዶች ከተበተኑበት ስፍራ በዓይነ—ህሊናው እያያቸው «ወገኖችህን ያሸፈጠ፤ ባህልና ወኔያቸውንም ያስካደ መስሎ ብዙውን ጊዜ ለህሊናዬ ስለተሰማኝ መልዕክቴን ከእህቴው ጋር ጨምረህ እንድትነግር ስል ይኸው ማኅተብህን ይገፉ አደራ እላለሁ።» ከተቀመጠበት ድረስ ሂዶ አንገቱ ላይ ያለውን ማኅተብ ሲጨብጥበት የግዴታው ኃይል ለደባልቄ ክፉኛ ተሰማው።

ብርግግ ብሎ በመነሳትም የሚጠበቅበትን ምን ያህል እንደሚያውቅ አስረዳ። «እሺ አጎቴ፤ ኧረ ማኅተብም አያሲዝም። እኔም ነገሩ እንደ ጣዝማ—ማር በስራ አካላቴ ገብቶ ስለሰረሰረኝ እንዲያው ሳልውልና ሳላድር ነው መልዕክቱን የማሰማቸው። የእማምዬን በደል መች አጣሁት ብለህ ነው? ያንተንስ መጎሳቆል የምስተው መሰለህ አጎቴ?»

የአያ ጎርብጤ ወኔ እንደገና ተቀሰቀሰ። «እንዲያ ነው እንጂ! እንዲህ እያልክ ልብ ስታደርግና ልብ ሲንጥህ የእኔም ህሊና አብሮ ይዳብራል። በል መልዕክቱን ይኼ ከዚህ በታች የምተነትነው ስለሆነ አንድም ሳይሳትህ አሰማቸው። መሰብሰብና የተሰማህን ትክክልን መናገር ይቻላል ተብሎ የሚታመንበት አገር እና ደግሞ የውጪ ዜጎች ስለሆኑ ብዙም የሚጠናወታቸው ክፍል ስለሌለ ሀቁን አበጥረህ ንገራቸው። ከዚህ በገዛ ቤታችን የተለጎምነው ይበቃል እንግዲህ ከዚህ በማያያዝ እውነት በመቀበር በሃሰት በር ላይ የገዛ ወገኖቻችን ተደቅነው በቁማቸው አነቀዙን። በዕዳ ባሩድ ጠበሱን። በባዕድ መሳሪያ መመሪያ አደረጉን። የህፃናት ደም በከንቱ ፈሰሰ። ያባቶችም መብት ወኔ ተረገጠ። ታሪክ ተደመሰሰ። የሴቶች ክብር ከመገሰሱም አልፎ ኢ—ሰብአዊ ድርጊት ተፈፀመባቸው። ይኸን በውጪ በእውን ሳታዩት ቀርታችሁ ነው? ወይስ አይሆንም ብላችሁ ነው? ወይስ ለነፍሳችሁ ፈርታችሁ ነው። *ባገኟት ያቺን ቀለህ የቴዎድሮስን፣ ባሩድ ጎርሳ ከሽንጡ ላይ የኖረችን፤ ኮሶ ሆና ሳትመረው ሊሸርባት፣ ደፋር ጀግናው ራሱ ጠጣት።»* ሲል ነሸጠው፤ ፎክር፣ ፎክር አሰኘው።

«እሺ አጎቴ ጎርብጤ። ኧረ አንገሸገሸኝ ተው አታስታውሰው የበልአ—ሰቦችን ሥራ!»

«እኔ ነኝና ጎርብጤ ዘውአለ! ሳምባዬንና ልቤን ከሚያቃጥለው፣ አዕምሮዬንም ከሚያንኮልለው፣ አምቄ ከምይዘው ይስሙት እንጂ ደግሞ ገና አልጨረሰኩም።»

«እሺ አጎቴ።»

«ይኸው የእህቴንም ቤት በልተው ጠጥተው እንዳላደጉበት ሁሉ እሷንም ሃዘን ላይ ጥለው ሃብቷን እንደ ቅርጫ ሥጋ ይቀራመቱታል። የእኛን የወገኖቻቸውን ዘር በመናቅ ዕዳው ለእኛው፣ ማጥፊያው ለእኛው የሆነ እሳት ተፊ እያስጫኑ ያስለበልቡናል። አምላካቸውም ይህንኑ የሚሰጣቸው ሆኗል። ኧረ እባካችሁ ተነሱ፤ የተፈጥሮ ውሃ እንኳ ነጥፎ ለጉሮሮአችን ማራሻ ሳናጣ። ምነው ወኔያችሁን በሙሉ ቀበራችሁት። የካሳ፣ ያሉላ እንዲሁም ያባኑበሶ ቅርሶች አልነበራችሁም? በላቸው። ኧረ ተዉ ለጊዜው ምቾት ብቻ አትኑሩ። ቀለም የበላው ሰው እንኳን ለችግር አብነት ነበር። እናንተስ ለገዛ እናታችሁ ያልሆናችሁ ለማን ልትሆኑ ነው በላቸው!»

«የማምዬን መንገላታት፣ የወገኖቼን መታመስ የገሰፅከውን በሙሉ ለመስማት ያብቃቸው እንጂ እነግራለሁኝ።»

«ምናልባት ከመቆየትና ሰሚም ከማጣት የተነሳ የእነሱን ፈለግ እንዳትከተል አደራዬ የጠበቀ ነው።»

ጠላው እየተጠጣ ቡናው እስኪያከትም ተፈላ። የዕውቀትና የምርምር ምንጭ የሆኑት መምሬም የማሳረጊያ ልሳናቸውን ማሰማት ጀመሩ። «እመት ተመዝብራ ያሉት መልዕክት አንዱም እንከን የለውም። ያው በግልፅ ሳስተዋለ ፍጥረት የሚከሰተው ነው። አቶ ጎርብጤ ዘውአለ ያከለበትና ያተኮረበትም ከቶውንም ምንጊዜም ሊዘነጋ የማይችል ትልቅ መልዕክት ነው። እግዚአብሔር ይቅር ባይና ገላጭ አምላክ ልቡናቸውን ገልጦ መልዕክቱን ለመረዳት ያብቃልን።» መልዕክቱና ምርቃቱ ግንባር ፈጥረው ተዥጎደጎዱ። አድማጮቹ በቸርነት ኃይሉ የማያልቅበት አምላክ እንዲያሰምርላቸው በመምሬ የተከፈተላቸውን ዕድል ለማለፍ ቅንጣት ያህል ጊዜ ሳያጠፉ «አሜን፣ አሜን አባታችን። እርግጥ ነው።» በማለት ፈቃዳቸውን ገለጡ። መምሬም ጭራቸውን ከግራ ወደ ቀኝ እየነሰነሱና ዐይኖቻቸውን ከጣሪያው ከምድሩ ጋር እያታኮሱ ፂማቸውንም እየጎተቱ የእጅ መነሳቱንና ይሁን፣ ይሁን መባሉን እንዳልሰሙ ሆነው የትምህርት ተዝካራቸውን ማቃመሳቸውን ቀጠሉ።

«እንዲያው ሩቅ ሳንሄድ ባጭሩ የራሳቸው ቋንቋ ሥነ—ፅሁፍ መኖሩ ብቻ ሌላ ቦታ ሳይኬድ በቂ ማስረጃ ነው። ለረዥም ዘመናት ታላቅ መሆናቸውን የሚገልፅ በቅዱስ መጽሀፍ ውስጥ ባያሌ ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሷል። ቀድሞም ቢሆን ወደ ጠፈር ከሁሉ በፊት ቀድሞ ያረገ የእሳቸው የእኛው ወገን የሆነ ‹ኤሊያስ በሰረገላ መሰጠ ደመና› ይኸም ማለት ኤሊያስ በእሳት መንኮራኩር ወደ ሰማይ ወጣ ማለት ነው። ቤተክርስቲያናችን ይህ ቋንቋ እንዳይወድም ምንጊዜም በፀሎትና በሥራ እመት ተመዝብራን ከማፅናናት ተቆጥባ አታውቅም። ምንም እንኳን ልጆቻቸው ቢያናንቁንም ይኸው ንቀታቸው ካለማስተዋል እንጂ በትክክሉ ቢያውቁ ኖሮ አንድም ጋት ከእናታቸው ፈቀቅ ባላሉም ነበር።»

«አይ መርማሪ ቢኖርማ!»

«የእኔ መልዕክት ያው ከእመት ተመዝብራና ከአቶ ጎርብጤ ምንም ልዩነት የለውም። ብቻ እኔ ባለሁበት ቦታ ምን ዓይነት ቅርስና ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ ስፍራ የያዘ ስፍራ መኖሩንና ውዳቂም <u>አርገው</u> ከመመልከት የእመት ተመዝብራን ቤት እንዳያስፈቱ ነው።»

«እሺ መምሬ እሰማዎታለሁ። መልዕክቱንም ለመንገር የፀሎትዎን ኃይል እጠይቃለሁ።» አለ ደባልቄ። እመት ተመዝብራ ይህን ሲሰሙ አንገታቸውን ደፍተው የቀሚሳቸውንጫፍ እያፍተለተሉ በተመስጦ ከተቀመጡበት ብንን ብለው ተነሱ። የፈለጉትም ይህንን የመሰለ ምክርና ዕውቀት ሳያገኙ እንዳይቀር ነበር። የደከሙትን ያህል ልባቸው ደስ አለው።

«እኔም ሆንኩ ሌሎች» ቀጠሉ መምሬ፤ «እኔን መሰልና ከእኔም የላቁ መንፈሳዊያን አባቶች የእናታቸውን ቋንቋ ጠብቀን ለማቆየት የምንታገለው መለያ ቅርስ እንዳያጡ ብለን ነው። የእናታችሁ ቋንቋ ከውቅያኖስ ባህር ጥልቀት ያለው በመሆኑ እስከ ዕድሜ ልካችን

ብንማረው የማያልቅ ነው። ማንኛውንም የጥበብ ዓይነት ሊሰራበትና ሊራመዱበት የሚችል የሚያኮራ ቋንቋ ነው። ጠባብ አድርጋችሁ አትዩት። እንዳትሳሳቱ። መለያ ምልክታችሁ ስለሆነ አትዘንጉት። መለያ የሌላቸው በተውሶ ራሳቸውን ሲገልፁ ባይሆን ኩራት አይሰማችሁም? የምትጠቀሙበትስ ቋንቋ ከስንቱ ቋንቋ የቀላወጠ አይደለም? ለምሳሌ ከላቲን፣ ግሪክ ወዘተረፈ ይል የለም እንዴ? ደግሞ በጣም የሚያሳስበን ለእናታችሁም ብርቱ ሃዘን የሆነባቸው፣ ባላችሁበት ቦታ ሁሉ የምታፈሯቸውን ፍሬዎች ሁሉ የራሳቸውን መለያ ማሳታችሁ ነው። ለምን ሃሞተ ቢስና ተቀጢያዎች ትሆናላችሁ? ከየኸ ያለው አለመግባባት አልበቃ ብሎ ከያ ደግሞ ሂዳችሁ ካብራካችሁ ከወጡ ልጆቻችሁ ጋር ባባ ትሆኑ እንዴ? እንደ ገበያ ቅቤ በዚያው እየቀለጣችሁ ለመቅረት አስባችሁ ከሆነ ፍጥረታችሁ ያሳዝናል። ካሊያም ደግሞ ምልክትን አውቆ ሌላ ያልሆነ ይዞ መምጣት ያበጣብጣል። ለምን ቢሉ በምን ቋንቋ ይግባባሉና ብለህ ንገራቸው።»

«እሺ መምሬ ይሁን።» ደባልቄ ብስለት ተሰምቶታል። የስልጣኔና የሃይማኖት የባህልና የአንድነት ምድር ውስጥ ባለ አገርና ባለ ቋንቋ መሆኑ ታወቀው። አብሮት ኗሪ ነው። ለዝንተ–አለም።

«የተሰበሰብንበትን ዓላማ ለፍሬ አብቅቶ መልዕክቱ አዕምሮን የሚያስገዛ ያድርገው።»

«አሜን! አሜን! አባታችን።» አሉ ሁሉም ከተቀመጡበት ተነስተው እጅ እየነሱ።

«ሁሉንም በሰፊው ባህሪው የሚመለከት በንፁህን መላዕክቱ ስም የሚመሰገን ልዑል እግዚአብሄር ይፈፅመው።» የማይታክተው የመምሬ እጅ መስቀሉን በአየር ውስጥ ከማቅዘፍ አላቋረጠም።

«አሜን! አሜን! መምሬ፤ አሜን! አሜን!»

«የተዛባውን ፍርድ ያቃናልን።»

«አሜን! አሜን!»

«መንገድህን ፍኖተ–ሰላም ያድርገው።»

«አሜን! አሜን!»

«ቆየት ብለው ትኩስ እንጀራ በበርበሬ አይበሉም። መቼም ቤቴ ባዶ ሆኗል።» ማጀታቸው ተሟጥጦ ሰፌዳቸውንም ቢሆን አብስለው የማያስርቡት ወላድ።

«ይህንን አይበሉ እመት ተመዝብራ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። ልጆችዎ ልብ ሲገዙ ቤትዎን የሞላ ያደርጉታል። አሁንስ ምን ጠፋና እናማርራለን። ብቻ እሱ ልቡናቸውን ሰጥቷቸው መንገዱን ይከፍትላቸው። ልጅዎትም መጎሳቆልዎትን በመልዕክቱ ያስረዳ። እኛም ጭንቀትዎ እንዲቃለል በፀሎት እንረዳዎታለን።»

መስቀላቸውን አሳልመውት የሄዱትን የመምሬን እግር በዐይኑ እየተከተለ ስሜታዊ ግጥም ይድራል።

«የችግርና የመከራን ገፈት መቅመስ
ትዕግስትና ትግል መሰረት ናቸው
የህይወት ጣዕም መዝለቂያቸው
አዕምሮ በንዴትና መሃሳብ ሲባዝን
አካል ደክሞ ደጋፊ መማፀን
መቅመስ ቢያስፈልግ የኑሮ እሬትን
በህይወት ዑደት ውስጥ አይቀርም
መቻል ነው፣ መታገል ነው የሚጠቅም
እስትንፋስ እስካለች በሰው ገላ
ህይወትና ኑሮ ትርጉሙ ቢያስጠላ
ደስታና ተድላ ችግር ሲጥሉ ነው
ለትግል፣ ለትንቅንቅ ቀበቶ ማጥበቅ ነው»

«እንዲያ ነው እንጂ የእኔ አንበሳ!» አለው አጎቱ አያ ጎርብጤ ትከሻውን መትቶ ተሰናብቷቸው የጠላ ጣሳውን እንደያዘ ሲወጣ። እያንጎራጎረ እንደመጣ እያንጎራጎረ ሲመለስም እስኪርቅ ድረስ የሚለው በጥራት ይሰማ ነበር። «ትጥቅ አጥብቆ፣ ተጠናቅቆ፣ ትልምን አውቆ፣ ውጤት አውቆ፣ መቋቋም ነው፣ መቋቋም ነው፣ ኃይል አጥልቆ። በህሊና፣ በሃሳብ ደመና፣ ሳይቀር መና፤ መጥቆ ሂዶ፣ ተረማምዶ፣ መድረስ ያሻል፣ ትግል ይረታል።» እየደበዘዘ በመጣው ምሽት ውስጥ ድምፁም እሱም ተሰወረ።

በፈታይ እጅ የተከመረ ጥጥ የመሰለው የደመና ክምር ከአድማሷ በተንጠለጠለችው የፀሀይ ብርሃን ብሩህ ፈገግታውን ፈንጥቆ ይታያል። ደብቁኝ ያለው የደመና አካል ከፊል ጎኑ ጠቆር ብሏል። ቀለል ያለው ነፋስ የደረቁ ቅጠሎችን ከአበባና የዛፍ ፍሬዎች ጋር ወደ አዲስ ስፍራ እየገፋፋ ይወስዳቸዋል። በፀሀይዋ ብርሃን የተሸነፉት ክዋክብትና ዓለማት በሰማያዊው ሰማይ ተጋርደው አልቀሩም። የድቅድቅ ጨለማውን ሲጠባበቁ የዋሉት ሰማየ–ዓለማትና ክዋክብት ምድሪቷን በጥቅሻ ሲያጫውቷት ሊያድሩ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

በናፍቆትና በእትብታቸው ስበት ከልጆቻቸው የሚነፍስላቸው እማምዬ የሚለው የትዝታ እንጉርጉሮ በቀዘቀዙት ውቅያኖሶችና ክፍለ–ዓለማት ላይ የተንሰራፋውን አየር ዘልቆ እንደ ሰመመን አሰማቸው። ልባቸውም የአምላክን ሥራና ተዓምር እያደነቀ ፅልመት በወረሰው ህይወታቸው ውስጥ ልጆቻቸው ከሩቅ እንዳሉ ብርሃን ሲፈነጥቁላቸው አድረው የንጋት ጮራ እንደሚሆኑላቸው በተስፋ ዘለቀ።

—— // ——


በኮምፒውተር የአማርኛና
የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

ከለር ማስታወቂያዎች፣
መጽሐፍት፤ መጽሔቶችና
የተለያዩ የአማርኛና
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን በጥሩ ዋጋ
በፍጥነትና ጥራት ባለው ሁኔታ
ለማሰራት ከፈለጉ ደውለው
ገነትን ያነጋግሩ።

ስልክ — (404)508–4657
ፋክስ — (404)508–2447

# የግጥም ጉባኤ

## የአንጎል መሞት!

ከልሳኑ ስምረት(ሴንትሉዊስ ሚዙሪ)

አእምሮስ ከሞተ፣ በድን ሬሳ ሆኖ
አስኳሉ ፈራርሶ፣ ንጥረ–ውሑዱ በኖ፤
ካልጣመ ቅመሙ፣ ብረት ኬሚካሉ
ተንድሎ አብቅቶ፣ ተሸንቁሮ ቅሉ።
ከተቀጠቀጠ፣ ፍሬ ዘር ቆለጡ
የእምቧይ ካብ ከሆነ፣ የጅማቶች ፈርጡ፤
ትውልድ ካሰደበ፣ ሕሊና ከላላ
ገብስ እንጀራ ቀርቶ፣ መቅመቆም ይበላ
ብቻ አንጎል አይሙት፣ የእውነት ከለላ።

ሁሉም ለጊዜው ነው፣ እንደዘይት ይፍላ
ጋይቶ ሲያነደው፣ ይመጣል በኋላ
ረሀብ ሲለብጠው፣ ይሰበራል ኬላ
አንጎሉ ካልሞተ፣ ካልሆነ ነሁላላ።
እንደገናም ኮርታ፣ ኢትዮጵያም ተሰርታ
በዘመናት ባህል፣ በጥቁርነቷ ፀንታ
የድንቅነሽ እናት፣ ትታያለች በርታ
አንጎልስ ካልሞተ፣ እውነት ካልምታታ።

የሞት ሞትስ መርዶ፣ ሞትስ የሕሊና
መታበት መቀፍደድ፣ በዶላር ምርቃና
«በግዴለሽነት» መታመም በጠና
ለካፒታል ሥርዓት፣ መቀጠር ግርድና
ለኒው ዎርልድ ኦርደር፣ መቆም በጥብቅና
ለጥቁር ሕዝብ ጥፋት፣ ላንድነት ብተና፤
የአንጎል መሞት ሞት ነው፣ የምዝብር ፈተና
የታሪክ እንቅፋት፣ ኃጥዕ ሆኖ መኖር–የትውልድ ገበና።

አንጎል ተኮማትሮ፣ ዓይን ካልፈዘዘ
ብርኃዊነት ጠፍቶ፣ ካልተበዘበዘ
በላጺስ ተፍቆ፣ ካልተደበዘዘ
እርስ በርስ ተባልቶ፣ ካልተገዛገዘ
ታሪክ ካልደለዘ፤
ሕይወትም አይጠፋም፣ ሬሳም ነፍስ ይዘራል
አንድነት በመልኩ፣ እንደሳት ይጋያል
እንደክብሪት ነዶ፣ ጭለማን ያበራርል።

በግሳንግስ ሻግቶ፣ እንደፈንገስ ገምቶ
ተሸርሽሮ አልቆ፣ ኪሪስታሉ ሞቶ
ማዕዘኑ ተላግቶ
እንደባዕ ጋንፉና ጨው፣ ኃይልነቱ ማሙቶ
ገቢራዊነቱ፣ ተሸሽጎ ጠፍቶ
ተነክሶ ታኝኮ፣ ሰውነቱ ላምቶ።

እንዳኅዛ ሌጦ፣ እንደርጥብ ጀንዲልጥ–ከተደበደበ
በባህል መላሸቅ፣ አንጎል ከደደበ
በነሚስተር ልጓም፣ አፍ ከተሸበበ
ምኑን ነፃ ወጣን፣ ውሸት ተገለበ።
ችካልም ይነሳል፣ ግንድም ይፈለጣል
ሲሚንቶም ይፈርሳል፣ ድንበርም ይገፋል
«የፈሩትም» ነገር፣ ሳይሹት ይነሳል
የጠፋውም መጥቶ፣ አጥሩም ይካባል
ታሪክ ተከውኖ፣ ታምርም ይሠራል
ውሸትም ይናጣል
የጨቀየው ነፅቶ፣ ድቅድቁም ይበራል
ኣእምሮ ካልሞተ፣ ስምረቱም ይሳካል
ብርኃዊነት ሰፍኖ፣ ሐቅም ይሰበካል።
ክፋት ከተስፋፋ፣ የሞት ሞት ከሆነ
አንጎልስ ከዛገ ከተመዘበረ፣ የሕሊና ደወል
ድብዛው ከተነነ
ክሬዲት ካርድ አንቆት፣ እንደጠኔ ሕይወት
ከተጥመነመነ
ነፃ ሊያወጣ እንኳን ሊያታግል
አስታርቆ ሊፈታ እንኳን ሊሸመግል
ዳሽቆ ይወራጫል፣ በቦካው በሊጡ
ስምጥ ብሎ ገብቶ፣ ሴሎቹ ሊናጡ
በነጭ አቡጊዳ፣ ከድጥ ወደማጡ
ዳክሮ ተለውሶ፣ በቅኔ ፈሊጡ።

በምዕራብ ብሊች፣ ፅዳት ከታቀበ
ፅሕፈቱ ከጠፋ፣ አንጎል ከታጠበ
የተቀኘው ጅማት፣ ላልቶ ከረገበ፤
ገብስ እንጀራ ቀርቶ፣ መቅመቆም ይበላ
የጎሪጥ ተያይቶ ጥላቻ ይቆላ
ብቻ አንጎል አይሙት፣ የእውነት ከለላ
የነፃነት መድኅን፣ «ወሰን የለሽ ኬላ»።

## ኢትዮጵያዊነት ባሜሪካን

ሰመፍ (10/22/89 ዓ.ም.)

ልቤ ያዝናል
ያዝናል ልቤ
በጣም!
በድሎት እያለሁ በድኅነት ስታመም።

## እኔና አንቺ

እኔ አንቺን ስጠብቅ አንቺን እኔን ጠብቂ
ንገሩኝ አትበይ ነገሩን ስታውቂ፣
ዓይን ዓይንሽን ሳየው አንቺም ዓይኔን እዪ
እንደው ችላ እያልሽኝ ዞር ዞር አትበይ፣
ወዴት ጠፋሽ ስልሽ ወዴት ጠፋህ በይኝ
እንዲያ እንደምናምን ጣል ጣል አታርጊኝ፣
እኔ ላንቺ ሳስብ አንቺም ለእኔ አስቢ
በጊዜ ስከተት አንቺም በጊዜ ግቢ፣
ስከፋ አይዞህ በይኝ ስትከፊ አይዞሽ
ጉዞዬ እንዲሰምር እንዲሰምር ጉዞሽ፣
ስንሰፈሰፍልሽ አንቺም ስፍስፍ በይ
እንደ ሌሊት ብረት ቅዝቅዝ አትበይ፣
ሁሌ ከተስማማን በዓረፍተ ነገሩ
ያብባል ይፈካል ዘላቂ ነው ፍቅሩ።
ጠብቂኝ ልጠብቅ እንጠባበቅ
እንደዛ ካልሆነ ፍቅር ሆኗል ፍቅ!
የጐደለው አለ ፍቅርሽና ፍቅሬ
ሁሉን ለመናገር አልችልም ዘርዝሬ፣
ያን የቃል ኪዳኑን ማተብ ባትበጥሽም
እኔ ያንቺ ስሆን አንቺ የእኔ አይደለሽም።

(መኩብብ–ከሲያትል)

# የአትላንታ ቡድን ለሁለተኛ ጊዜ ሻምፖዮና ሆነ!

የዘንድሮው የ14ኛው የሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ውድድር በሎሳንጀለስ ከተማ ከጁን 29 እስከ ጁላይ 5 ድረስ ሲካሄድ ቆይቶ በአትላንታ የእግር ኳስ ቡድን አሸናፊነት በከፍተኛ ድምቀት ተፈጽሟል። ዘንድሮ ከአንደኛ ዲቪዝዮን የለንደን ቡድን በቪዛ ምክንያት ባለመሳተፉ የተወዳዳሪ ቡድኖችን ቁጥር በአንድ ቀንሶታል። በዚህም መሰረት በአንደኛ ዲቪዝዮን በአራት ምድብ ተመድበው ከየምድባቸው አንደኛ የወጡት ቡድኖች ማለትም የሎሳንጀለሱ ዳሎል፣ L.A. ስታር፣ ቨርጂኒያና የአትላንታ ቡድኖች ነበሩ። ከዚያም በወጣው ፕሮግራም መሰረት ለጥሎ ማለፍ መጀመሪያ L.A. ስታር ከቨርጂኒያ ጋር ተጫውቶ L.A. ስታር ሁለት ለአንድ ሲያሸንፍ አትላንታ ከዳሎል ጋር ተጫውቶ አትላንታ በከፍተኛ የጨዋታ ብልጫ ዳሎልን አምስት ለአንድ አሸንፏል።



በዘንድሮ ውድድር ዋንጫውን ያገኛሉ ተብለው ከተገመቱት ቡድኖች መካከል ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት የነበረው የሎሳንጀለሱ የዳሎል ቡድን የብዙ ጊዜ የጨዋታ ልምድና ብቃት ባላቸው የአትላንታ ቡድን በሰፊ የግብ ልዩነት መሸነፍ ሁሉንም አስደንቋል። በዚህም ምክንያት የአትላንታ ቡድን ለዋንጫ ሽሚያ ካለፈው ከL.A. ስታር ቡድን ጋር በሰፊ የጐል ልዩነት ያሸንፋል ብለው አብዛኛው ተመልካች ግምት ሰጥቶ ነበር። በበዓሉ መዝጊያ ዕለት ከሁለቱ ቡድኖች ውድድር በፊት ከአስሩ የሁለተኛ ዲቪዝዮን ስፖርት ክለቦች መካከል አሸናፊ በመሆን ወደ አንደኛ ዲቪዝዮን ያለፉት ቡድኖች ባደረጉት ውድድር የሳንሆዜው አንበሳ ቡድን አሸናፊ በመሆን ዋንጫውን ወስዷል። ከዚህ ውድድር ቀጥሎ የተጫወቱት ከአንደኛ ዲቪዝዮን ለሶስተኛነት ደረጃ በተደረገው ውድድር የሎሳንጀለሱ የዳሎል ቡድን ቨርጂኒያን አሸንፏል።

በመጨረሻም በከፍተኛ ጉጉት ይጠበቅ የነበረው የ1997 ዓ.ም. የአንደኛ ዲቪዝዮን ክለቦች አሸናፊ ሆነው ባለፉት በሁለቱ አንጋፋ ቡድኖች ማለትም በሎሳንጀለሱ L.A. ስታርና በአትላንታ ቡድኖች መካከልየሚደረገውን ግጥሚያ ለመመልከት ቁጥሩ እጅግ የበዛ ተመልካች የተገኘ ሲሆን የዕለቱም የክብር እንግዳ ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር ወደ ሜዳው በመግባት ከተመልካቾችና ከተጨዋቾች ጋር ተዋውቀዋል። ተመልካቹም ለክብር እንግዳው ያላቸውን አድናቆት በጭብጨባ ገልጸዋል።

የአትላንታ ቡድን ከአንድ ቀን በፊት ባደረገው ውድድር ሳቢያ የድካም መንፈስ በሁሉም ተጫዋቾች ላይ ይታይ ነበር። ጨዋታው በእንዲህ እንዳለ በ15ኛው ደቂቃ የሎሳንጀለሱ የፊት አጥቂ እየሄደ ሳለ የአትላንታው አምስት ቁጥር በመውደቁ ያገኛትን ኳስ በቀላሉ በማግባት ለቡድኑ የመጀመሪያውን ግብ አስቆጠረ። አሁንም ጨዋታው ቀጥሎ ይኸው የፊት አጥቂ በሃያ አንደኛው ደቂቃ አካባቢ በተከላካይ ስህተት ያገኛትን ኳስ በቀጥታ በመምታት ለቡድኑ የሁለተኛውን ግብ አስቆጠረ። በዚህም ምክንያት አንጋፋው የአትላንታ ቡድን የመደናገጥ ስሜት ይታይበት ጀመር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የአትላንታ ቡድን ባገኘው ቅጣት ምት ክፍሉ መብራቱ በቀጥታ መትቶ ለአትላንታ የመጀመሪያውን ግብ አስቆጥሮ የመጀመሪያው 45 ደቂቃ በL.A. ስታር ሁለት ለአንድ መሪነት እረፍት ሆነ። ከእረፍት መልስ ሁለቱም ቡድኖች ባላቸው ኃይል እያጠቁ አሁንም L.A. ስታር ቡድን በዚሁ በአሜሪካዊው አጥቂ መሰረት ድንቅ ጐል በማግባት ቡድኑ ሶስት ለአንድ ይመራ ጀመር። የአትላንታ ቡድንም በበኩሉ ልምድ ባላቸው ተጫዋቾቹ እየተመራ የማጥቃት ሙከራውን ተያያዘው። ብዙ የግብ ሙከራ አድርጐ ብዙ ጐሎችን ቢስትም ሁለተኛውንና ሶስተኛውን ግብ በዳንኤል ክፍሌ አማካይነት በማግባቱ የ90 ደቂቃ ጨዋታው ሶስት ለሶስት በሆነ እኩል ውጤት በመፈፀሙ አሸናፊውን ለመለየት ሰላሳ ደቂቃዎች ተጨመሩ። በዚህም ጊዜ የአትላንታ ቡድን በንጉሴ አስፋውና በጌቱ አማካይነት ሁለት ጐል ሲያክል የL.A. ስታር ቡድን ደግሞ አራተኛውን ጐል በቢኒያም አማካኝነት አገባ። ጨዋታው ሊፈፀም ሁለት ደቂቃዎች ሲቀሩት ዳኛው አግባብ ያልሆነ የፍፁም ቅጣት ምት ለL.A. ስታር ቡድን በመስጠታቸው ምክንያት ጨዋታው ለ5 ደቂቃዎች ያህል በግርግር ምክንያት ተቋርጦ ነበር። ያለአግባብ የተሰጠውንም የቅጣት ምት ሙሴ መትቶ የግብ አግዳሚ መልሶበታል። ጨዋታው ወዲያው አልቆ የአትላንታ ቡድን አምስት ለአራት በሆነ ውጤት ሻምፒዮን ሊሆን በቅቷል። የአትላንታ ቡድን ተስፋ ሳይቆርጥና ሶስት ለአንድ ከሆነ ውጤት ተነስቶ አምስት ለአራት ማሸነፉ ቡድኑ ምን ያህል ጠንካራና የማይሸበሩ የጨዋታ ልምድ ያላቸው ተጨዋቾች እንዳሉት ያመለክታል። ዘንድሮ የአትላንታ ቡድን ከዋናው አሰልጣኝ በተጨማሪ ምክትል አሰልጣኙ ሽዋንግዛው ተረፈ ታላቅ ሚናን ተጫውቷል።

በዋንጫ መስጠት ስነስርዓት የአትላንታ ቡድን ዋናውን ዋንጫ ከመረከቡም ሌላ፤ ኮከብ ተጨዋች በመሆን ዳንኤል ክፍሌ፣ ኮከብ አግቢ በመሆን ንጉሴ አስፋው የተመረጠ ሲሆን እንዲሁም ኮከብ አሰልጣኝ በመሆን አሰልጣኝ እንዳለ ቱፋርም የልፋታቸውን ያህል ኮከብ ተብለዋል ተመርጠዋል። በዚህም ምክንያት የአትላንታ ቡድን የአራት ዋንጫዎች ባለቤት በመሆን በደስታ ወደ አገሩ ተመልሷል።

ከዚህም በተጨማሪ የአስራ አምስተኛውን የሰሜን አሜሪካ ውድድር ደግሞ አትላንታ እንዲያዘጋጅ ፌዴሬሽኑ ወስኗል። በአጠቃላይ የዘንድሮ ውድድር ይህን ይመስል ነበር። የሚቀጥለውን የውድድር ዘመን ደግሞ እንድናይ እግዚአብሔር ለሁላችንም ዕድሜና ጤና ይስጠን።

በቸር ይግጠመን

(መኮንን ጉርሙ – ከአትላንታ)

# “መንግስት ሲበድልና ፍርድ ሲያጓድል ቤተክርስቲያን የመገሰፅ ኃላፊነት አለበት!!”

ከቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ

በመጀመሪያ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ይድረሳችሁ እላለሁ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ኢትዮጵያን ነጥሎ (ለይቶ) ማየት አይቻልም። ለምን ቢባል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሀገራችን ያበረከተችው በረከት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ቀደም ሲል የትምህርት ሚ/ር በመሆን በሰፊው ለኢትዮጵያ ህዝብ ፊደል ቀርፃ የትምህርት ቤት በመክፈት ከዳር እስከጠረፍ መዋቅሩን በመዘርጋት ለህዝባችን በትምህርት፣ በንቃተ ህሊና ያጐናፀፈች፣ በባህል፣ በእምነት፣ በታሪክ፣ በማህበራዊ ኑሮ፣ ለአንድነት፣ ፍቅር፣ ለሰላም የሰበከች ያስተማረች ይህች እናት ቤተክርስቲያን ናት። ኢትዮጵያ በመፅሐፍ ቅዱስ ከአርባ ጊዜ በላይ ተጠቅሳ እናገኛለን። ይኸውም ኢትዮጵያ ከአምላኳ ከፈጣሪዋ ከእግዚአብሔር እምነተ ክርስትናን ስትቀበል ቀደም ሲል በህገ ልቡና ኦሪት ከተሰራች በኋላም ኦሪትን በመቀበል ከዚያም ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የክርስትና እምነትን ያለአንዳች ማወላወል ተቀብላለች። ለዚህም አስረጅነት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጠቃሚ ይሆናል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለሀገራችን ኢትዮጵያ ያበረከተችው በረከት ከላይ የገለፅነውን ብቻ አልነበረም። ጠላት በተለያየ ጊዜ ሀገራችንን ለመውረርና ቅኝ ለመግዛት በተሳሳተ ሀሳቡ በተነሳ ጊዜና በቃጣበት ጊዜ በቀጥታ አልነበረም ጦርነት የከፈተው የኢትዮጵያና የዓለም ታሪክ እንደሚዘክረው ጠላት አስቀድሞ የላከው ሰላዮችን ነበር። እነዚህም ሰላዮች ኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ተከታይ ሀገር በመሆኗ ለማደናገር ሲል የወንጌል ሰባኪዎች ተብለው እነአባ ማትያስ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሌሎችም መነኰሳት ተልከው ነበር። በዚህ መሰረት መነኰሳቱ የኢትዮጵያ ነገስታቱን ለመያዝ ሞክረው አፄ ሲሶንዮስን ለመያዝ በቁ። እነ.ህ ነገሥት(ንጉሥ) ኢትዮጵያን በካቶሊክ እምነት ለማኾጕርጕር ሲሞክሩ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናት የሀሳዊ መሲህን አዋጅን ህዝቡ እንዳይቀበል ህዝቡን በማስተማር በማንቃት የኢትዮጵያ ህዝብ ባርነቱ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰዎች አይደለም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት የተሰጠው ከእግዚአብሔር በመሆኑ ማንም ሊደፍረው አይችልም በማለት የአፄ ሱስንዮስ ምላስ ተጕልጕሎ በመውጣት የእግዚአብሔር ታምር እስኪገለፅ ድረስ ካህናቱ የውጭ ሴራ አክሽፈዋል። ይህ በዚህ እንዳለ ኢትዮጵያ ገና ከጥንት ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ዓለም በፊት አምልኮተ እግዚአብሔርን ከፈጣሪዋ ስትቀበል ቀደም ሲል እንደተገለጸው በህገ ልቡና ኦሪት ከተሰራች በኋላ ኦሪትን ከዚያም ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ እምነተ ክርስትናን ተቀብላለች።

ይሁን እንጂ «እንበለ መከራ ኢይትሪካብ ፀጋ» ይህም ማለት ያለ ፈተና ያለ ችግር መልካም ነገር አይገኝምና ኢትዮጵያ ለአያሌ ዘመን ተፈትናለች። አሁንም ከአብራኳ በወጡት ልጆቿ ከባድ ፈተና ላይ ወድቃ ትገኛለች። ይህች አገር ታፍራ ተከብራ ነፃነቷን ጠብቃ ከትውልድ ወደትውልድ እየተሸጋገረች ትገኛለች። ኢትዮጵያ የጥቁር ህዝብ ነፀብራቅ፣ የሃይማኖት ሰንደቅ፣ ኢትዮጵያ የዓለም ህዝብ መምህር፣ የድንቅነሽ ሃገር፣ ኢትዮጵያ የክርስትና ምንጭ፣ ለሰው ፍቅር ሰጭ፣ ኢትዮጵያ በክርስትና የተዋበች፣ በታሪክ የተደነቀች በዓለም ህዝብ የተደነቀች አገር ነች።


ብዙ ነቢያት ስለኢትዮጵያ ታላቅነት ተናግረዋል። ታላቁ ነቢይ ኤርሚያስ በም.13 ቁጥር 23 ላይ «በእውኑ የነብር መልክ ቢዥጕረጕር ኢትዮጵያውያንም እንደዚሁ መልካቸው ቢዥጕረጕር አንድ ናቸው» ብሏል። ታላቁ ነቢይ ወይም ልበ አምላክ የተባለው ዳዊት በመዝሙር 73 በቁጥር 14 «ዘንዶውን ቀጥቅጠህና አፉን ዘግተህ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምግብን አዘጋጀህ» በማለት ተናግሯል። ታላቁ ዳዊት የእስራኤል ንጉስ መሪ በነበረበት ጊዜ ህዝበ እስራኤል ጥፋት ሲመጣ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸውና ከዳዊት ቀጥሎ መንገስ ያለበት ልጁ ሰሎሞን መሆን እንዳለበት ነቢዩ ናታን ዳዊትን ይመክርና ይገስፅ እንደነበር ቅዱስ መጽሀፍ ይነግረናል። ታዲያ ይህ ከሆነ የቤተክርስቲያናችን ካህናት አጥፊውንና ሀሳበ ደካማውን ለመገሰፅና ለመቆጣት የተሳናቸው ይመስላል። ዛሬ ህዝባችን ታሪኩን ባህሉን እምነቱን አጥቶ እየጠፋና እየተጠፋፋ ያለበት ዘመን ሲሆን በተለይ ወጣቱ ትውልድ የታሪክ ተረካቢ ለመሆን ብቁ መስሎ አይታይም። ወጣቱ ትውልድ ደግሞ የሀገሩን ታሪክ እምነት ባህል የአባቶችን አደራ ካልተማረና ካልጠበቀ የሀገሪቱ ህልውና የከፋ ይሆናል።

ለዚህም ጥፋት መሰረት የሆነው የወደቀው መንግስትና አሁን በአገዛዝ ያለው መንግስት በመሆናቸው ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ህዝባችን ሃይማኖቱንና ታሪኩን እንዳይማርና እንዳይጠብቅ ከባድ ሻና ስለጣሉበት የቁም እስረኛ አድርገውት ይታያሉ። አዕምሮአችን እንዳንጠቀምበት የሰለቡን ይመስላሉ። ይህን ሁሉ የቤተክርስቲያናችን ካህናት እያወቁ ዝም ማለታቸው ከነርሱ ጋር መተባበር ይመስላል። ከጥቂት ጳጳሳትና አበው መነኰሳት በስተቀር እውነትን አበጥሮ ለመናገርና እውነቱን እውነት ውሸቱን ውሸት ብሎ የገሰፀና ያስተማረ ካህን የለም። ይህንንም የኢትዮጵያ ህዝብ በአንክሮና በጥሞና «እኸ» እያለ ይዞት ይገኛል። «እምነ መንግስት የአቢ ክህነት» ከመንግስት ክህነት ይበልጣል። መንግስት ሲበድል ፍርድ ሲያጓድል ቤተክርስቲያን የመገሰፅ ኃላፊነት አለበት። በመፅሀፍ ቅዱስ ምሎና ቅባ ሜሮን ተቀብቶ ያልተሾመ ጡንቻውን አምልኮ የመጣ መንግስት ቀርቶ በህጉ ማለትም በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ተቀብቶና ምሎ በህዝቡ ተመርጦ «ይደልዎ» ይገባሃል ተብሎ ቢሾምም እንኳ አጥፊ ከሆነ ጥፋቱን መንገር ተገቢ ነው።

(ይቀጥላል)

*ቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ በአትላንታ ሰዓሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ናቸው።*

# የአትላንታ ሳሊተ ምህረት ቅድስተ ማርያም
## አዲስ ቤተክርስቲያን ህንፃ ሊሰራ ነው።



*“ባዶ ቦታ ገዝተን ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅርጽ የያዘና አሁን ያለንበት ህንፃ ከመጥበቡ ባሻገር የሚጐድሉትን እንደህፃናት ት/ቤት፣ ሁለገብ አዳራሽ፣ የመኪና ማቆሚያና የመሳሰሉትን መሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮችን አሟልቶ የሚይዝ ቤተክርስቲያን እንስራ!”*

ይህ በአትላንታ የምትገኘው የሰአሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባል ምዕመናን የጋራ ውሳኔ ነው።

የሳዕሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የልማትና የዕድገት ኮሚቴ የቤተክርስትያኗ ምዕመናን «አዲስ ቤተክርስቲያን እንስራ» በማለት ያሳለፈውን ውሳኔ በመከተል የመጀመሪያውን የገንዘብ ድጋፍና እርዳታ ለመጠየቅ ባዘጋጀው ፕሮግራም ኦገስት 2, 1997 ዝነኛውን የአባይ ሃገር ባህል ስብስብ ጥሪ በማድረግ ታላቅ የሀገር ባህል ምሽት አዘጋጅቷል። በዚህም ዝግጅት በአትላንታ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገር ባህል ልብሳቸው አሸብርቀው አዳራሹ ወደሚገኝበት Little 5 Points Euclid Av. ሲጓዙ ማየት የሀገር ባህል ልብሳችን ምን ያህል ግርማ ሞገስ እንዳለው የሚመሰክር ትልቅ ማስረጃ ሆኖ ነበር።

የምሽቱ ፕሮግራም የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ ለህንፃው ማሰሪያ የሚሆን የገንዘብ መዋጮ ለማግኘት ቢሆንም የአባይ ሃገር ባህል ስብስብ ባሳዩት የተለያዩ ትዝታ ቀስቃሽ የሃገራችን የባህል ጨዋታና ትርኢት በአዳራሹ ውስጥ የነበረው ከ700 በላይ የሚጠጋ ህዝብ ደስታውን በጭብጨባ ገልጿል። በተለይ የቡድኑ መሪ የሆኑት ወ/ሮ ላዲና ሽናጥር (ወ/ሮ እስከዳር–የውጪ ዜጋ) ካቀረቡት የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች ሌላ ያደረጉት ንግግርና ኢትዮጵያዊ ተረትና ምሳሌ እውነተኛ የኢትዮጵያ ወዳጅ መሆናቸውን በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን በንግግራቸውም ላይ ኢትዮጵያዊን ሁሉ አንድነታችንን፣ ሃይማኖታችንን፣ ባህላችንን መጠበቅ ግዴታችን መሆኑን በተለያየ ምሳሌ በማቅረባቸው የብዙዎቻችንን ልብ ነክተውታል።

ከትርኢቱ ግማሽ ክፍል በኋላ ለምሽቱ ለጨረታ የሀገር ባህል ልብሶችና ባህላዊ ቅርፃ ቅርፆች ቀርበው በጨረታ የተሸጡ ሲሆን በተለይም እኒህ ከላይ የተጠቀሱት ሴት አንድ የቀንድ ዋንጫ እስከ $400 ድረስ እንዲጫረት በማድረግ ይህንን የተቀደሰ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ተሳታፊነታቸውን አሳይተዋል። እንዲሁም በዕለቱ የገንዘብ መዋጮ ቅስቀሳ ተካሂዶ በቡድን በመከፋፈል አምስት ቡድን እያንዳንዳቸው 1,000 ዶላር ለማውጣት ቃል ሲገቡ ሌላ አንድ ግለሰብ ደግሞ ለብቻቸው 5,000 ዶላር በማውጣት በጠቅላላው የ10 ሺህ ብር መዋጮ ለመስጠት ቃል ገብተውልናል። በዚህ ልዩ የባህል ምሽት በዝች አጭር ጊዜ ውስጥ ከትኬት ሽያጭ፤ ከቃል መዋጮ፤ ከጨረታና ከምግብ ሽያጭ በአጠቃላይ ከ$30 ሽህ ዶላር በላይ ተሰብስቧል።

በመጨረሻ በዚህ ምሽት ትኬት በመሸጥና በተለያዩ ስራዎች በመሳተፍ እርዳታ ላደረጉና እንዲሁም በፅሁፍ ስራ ለረዱን ለላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል የቤተክርስትያኗ የልማትና የዕድገት ኮሚቴ ከፍ ያለ ምስጋናውን እያቀረበ ወደፊትም በምናደርጋቸው የተለያዩ የህንፃ ግንባታ ፕሮግራሞች ከጐናችን እንድትቁሙ ጥሪውን ያቀርባል። የሳህሊተ ምህረት ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ካህናትና አስተዳደር ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ እውን መሆን በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ወገኖችን የተባበረ እርዳታና ድጋፍ ይጠይቃሉ።

የእግዚአብሔር ረድኤትና ቸርነት አይለያችሁ! ድጋፋችሁንና እርዳታችሁን ለመስጠት አድራሻችን፦


**Sealite Mihiret Kidist Mariam**
**Ethiopian Orthodox Tewahido Church**
**P.O.Box 1412**
**Decatur, GA 30031**
**Tel. (404) 377-2238**

[redacted]

# ታሪክና ምሳሌ

(ከመጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

## ከገደብ የሚያልፍ የሙዚቃ አፍቃሪነት የሚያስለከትለው ውድቀት

## (ቁጥር ሁለት)

በዓለም ላይ ከማር ወለላ የሚበልጥ ጣፋጭ ነገር የለም ሲበዛ ግን እርሱም ራሱ መራራ ይሆናል ይላል ጠቢቡ ሰሎሞን በምሳሌው። ሙዚቃ የማፍቀርንም ስሜት ከገደብ በማሳለፍ አእምሮአቸው (ናላቸው) ዞሮ መንፈሳቸው ሰክሮ፣ ልባቸው ተሰውሮ መቆጣጠር አቅቷቸው በህይወታቸው ላይ አደገኛ መቅሰፍትን የጋበዙ ብዙ ናቸው። ለዚህም ካሉን የታሪክ ማስረጃዎች አንዱን ብንጠቅስ ኔሮን ቄሣር ተቀዳሚ ሆኖ ብቅ ይላል። ኔሮን ቄሣር ራሱ ክራር ተጫዋችና በሙዚቃ ያበደም የሰከረም ሕይወት ነበረው።

ብዙዎች የዘመኑ ጠቢባን የኔሮንን አስተዳደግ ተመልክተው ስድነትን(ልቅነትን) የሚያበዛ ስለነበር ከሙዚቃ አፍቃሪነቱና ከጠንካራ መጠጥ አዘውታሪነቱም ቆጠብ ብሎ የሰከነ ሕይወት እንዲኖረው ለወላጅ እናቱ ለንግሥት አግሪፒና ምክር አቅርበውላት ነበር። እርስዋ ግን «ልጄ ይደግልኝ እንጂ ይህ ሁሉ ነገር ቀላል ነው። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይሰክናል» አለች። አዎ እናት ናትና ገበናውን ለመሸፈን ያደረገችው ሙከራ ነበር። ነገር ግን እንዳሰበችው ሆኖ አልተገኘም። ስድ አደግነቱ ከገደብ አለፈ። ታላቁ የሮም ቄሣር ቀላውዴዎስ ቄሣር ሲሞት ኔሮን የቀላውዴዎስ ቄሣርን ሴት ልጅ አግብቶ ያለ ምንም ምርጫ ራሱን በራሱ ወደ ቄሣርነት ደረጃ ከፍ በማድረግ በትረ መንግሥቱን ያዘ። የመጀመሪያ እርምጃውም ወላጅ እናቱን ንግሥት አግሪፒናን ማስገደል ነበር። ወታደር ልኮ ራስ ራስዋን በበትር ሲቀጠቅጧት ምን አጠፋሁ በደሌ ምንድነው? በማለት ጠየቀች። መልስ ሳይሰጣት ድብደባው ቀጠለ። በዚህም ጊዜ ከልጁዋ ዘንድ የተላከባት መቅሰፍት መሆኑን አውቃ፦

«ራሴ ምን አጠፋ ሆዴን ምታው እንጂ
ፀንሶ በወለደ ኔሮን ብሎ ልጅ»
አለችው ይባላል ምስኪኑዋ ንግስት
እንደእባብ በበትር ተቀጥቅጣ ስትሞት።

ተብሎ የተፃፈ የታሪክ ትዝታ አለን። ዋና መልዕክቱም በተለይ አዲስ የተወለዱ ታዳጊ ልጆች እንደ ኔሮን ቄሣር በሙዚቃ የሰከረና መላ ቅጥ የጠፋ ሕይወት እንዳይኖራቸው ተጠንቀቁላቸው። ችላ ብትሉ ግን የንግስት አግሪፒና ጽዋ ለእያንዳንዱ ወላጅ የሚደርስ ይሆናል ለማለት ነው።

ለኔሮን ቄሣር መንግስት ተንኮታኩቶ መውደቅ ምክንያቱ ከሆኑት ነገሮችም አንዱ አፍቃሪ ሙዚቃ የመሆኑ ስሜት ገደብ ማጣት መሆኑን ታሪክ ሲነግረን እንዲህ ይላል። ኔሮን ቄሣር በዘመኑ የነበራችውን የሮማ ከተማ የጥንት ፕላን አሻሽሎ ለራሱ መንደላቀቂያና መሞላቀቂያ የሚሆን አዲስ ቤተመንግስት ማሰራት ፈለገ። ይህን እቅድ ከባለስልጣኖቹ ጋር ተመካክሮ ሕዝቡንም አስተምሮና አስጠንቅቆ ንብረቱም ተጠብቆ በጥንቃቄ ሊፈጽመው ሲችል በአምባ ገነንነት ተነሳስቶ ከተማይቱ በእሳት ተቀጣጥላ እንድትጋይ አደረገ። ቤቱ የተቃጠለበት ንብረቱ የፈረሰበት ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ይህን ዕብድ ከስልጣን ጉትተን እናወርዳለን ብሎ ቁጣና መዓት የፈላበት ሰላማዊ ሰልፍ በሚተምበት ጊዜ አስገራሚው ኔሮን ቄሣር ከሰባቱ የሮም ጉብታዎች በአንዱ ተራራ ላይ ተቀምጦ ክራር እየተጫወተ ይጨፍር እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።

ለዚህ ድጋፍ የሚሆን አንድ ታሪክና ምሳሌ እነሆ!

## በአደገኛ የሙዚቃ ፍቅር ናላው የዛለ መምህር

ሲጨፍር ያድርና ቀን ቀን የሚተኛ
አንድ ሰነፍ መምህር ግድየለሽ ዳተኛ
ሌሰን ፕላን ሳይነድፍ ለትምህርት ዝግጅት
ዕቅድ ሳያወጣ በህጉ መሰረት
ሲያፌዝ ይኖር ነበር በደንታ ቢስነት።
ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ክፍል ገብቶ
ምን እንደሚያስተምር አልተረዳም ከቶ
ጊዜ ማሳለፊያ በብላክ ቦርዱ ላይ
በጠመኔ ስሎ አንድ ባቡር መሳይ
«ይህን የሚመስል አንድ ባቡር ሳሉ
ጊዜው እንዳይባክን እስቲ ቶሎ በሉ»
የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ
የሚቀምር መስሎ ሐሳብ የሚያሰላ
ወንበር ተደግፎ እንደተቀመጠ
ሰመመን ወሰደው ራሱ እየተናጠ
አንገቱን ደፋ አድርጐ ደቂቃ ሳይዘገይ
እንቅልፍ ይዞት ሄደ በጠረጴዛው ላይ።
ባቡሩም ተስሎ ለእርማት ቸኩለው
ቲቸር ቲቸር አሉት ህይወት አለው ብለው
ጩኸት ሲበዛበት መምህሩ ባነነ
እየተወራጨ መበሳጨት ሆነ
ዝምበሉ በማለት ማስመሪያ እየቃጣ
ማስታገስ ቢፈልግ የሚሰማው አጣ
«አሁን ያርሙልን ውጤቱን እንወቅ»
ብለው ገትተው ያዙት እንዳይነቃነቅ
ሌላ አማራጭ ጠፋ ፉጨት ተከተለ
ሳይወድ በግዱ ሥዕሉን ተቀበለ
እዚያው መልሱን ሊሰጥ እርማት ቀጠለ።
ታዲያ ከዚያ ሁሉ ነጎዴ ተማሪ
ለካ አንድ ወጣት ኖሯል ብልህ ተቆርቋሪ
በወረቀቱ ላይ ባቡር መሳል ትቶ
ለመምህሩ አሳየው ሀዲድ የሚመስሉ መስመሮች ዘርግቶ
መምህሩም ተቆጣ በኃይል ገሰፀው
«አንተ ሰነፍ ዋልጌ በምን ምክንያት ነው
ሐዲድ ብቻ ስለህ ባቡሩን የተውከው?
በል እስኪ ንገረኝ» ብሎ ቢጠይቀው
«ባቡሩ አልፎ ሄዷል እርስዎ ተኝተው
ሊመለስ አይችልም እኔ ምን ላድርገው
ብሎ መልስ ሰጥቶ መምህሩን አስቆጣው
ያም ሁሉ ተማሪ በዚያ አስተማሪ ላይ
በህብረት ሳቀበት መንጋጋው እስኪታይ።

በቁጥር ሶስት የዚሁ ተከታይ እስክንገናኝ ጤና ስጥልኝ።

# ሰንጠረዥ ፩

## በሰይፉ አዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺፱ ዓመት

SAEFU © Copyrighted 1997

ይህን የሰንጠረዥ ጨዋታ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይና በሰያፍ በመክበብ የቀሩት ሆሄያት የሚያነቡትን በመፈለግ በጊዜዎት ይዝናኑ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ታ | ማ | እ | ን | ዲ | ሁ | ም | ፉ | ከ | ይ | አ | ታ | ሺ | እ |
| ብ | ፍ | ማ | ሱ | ነ | እ | እ | ን | ተ | ዋ | ወ | ቅ | ር | ሺ |
| እ | ረ | ጥ | ሰ | ን | እ | ን | ራ | መ | ድ | እ | ሰ | ፍ | እ |
| ም | ን | ራ | ል | ን | ዳ | ሠ | ዴ | ን | ን | በ | ገ | ል | ን |
| ኛ | እ | ላ | ቀ | ገ | እ | ል | ላ | ዴ | እ | ጋ | እ | ጋ | በ |
| እ | ን | ወ | ቅ | ን | ታ | ጥ | ታ | ር | ደ | ን | ን | ል | ል |
| ን | ማ | ታ | ቢ | ን | እ | ን | ሳ | ን | ግ | ? | ዋ | ፈ | / |
| ፉ | ር | ማ | ኛ | እ | ቢ | ች | እ | ለ | ኖ | ግ | ዴ | ስ | ላ |
| ቀ | ቅ | ተ | ሏ | ን | ን | ን | ፅ | ሆ | ን | ደ | ድ | ያ | ባ |
| ር | ን | ሳ | እ | እ | ደ | ሥ | ት | ወ | ጫ | ን | እ | ም | ባ |
| እ | ሱ | ን | ን | ማ | ር | ዴ | ራ | ም | ን | እ | ና | ታ | ግ |
| ዳ | ፃ | ረ | መ | ~~እ~~ | ~~ን~~ | ~~ግ~~ | ~~ዲ~~ | ~~ያ~~ | ~~ማ~~ | ~~!~~ | ው | ቢ | ን |
| ፍ | ዳ | ጥ | ኘ | እ | ነ | ሱ | ጠ | ፍ | ብ | ል | ጋ | ን | እ |
| ዳ | ዳ | ረ | ን | እ | ው | ነ | ተ | ኛ | ታ | ን | ው | እ | ኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እንመኝ | እንቢታ | እንዴት ሆኖ | እውን |
| እርስ በእርሳችን እንረዳዳ | እንማር | እንቢታም ያስፈልጋል | እንዴታ |
| እርግጠኛ | እንምራ | እንተኛ | እንጋልብ |
| እሱን | እንሠልጥን | እንተዋወቅ | እንግለፅ |
| እሷ | እንሥራ | እንታገል | እንግባባ |
| እሷማ | እንረዳዳ | እንወቅ | ~~እንግዲያማ!~~ |
| እሺ እንበል | እንራመድ | እንዋደድ | እንጫወት |
| እሺታ አይከፋም | እንሳቅ | እንደማመጥ | እንፃፍ |
| እነሱ | እንስማማ | እንደጋገፍ | እንፋቀር |
| እነሱማ | እንስጥ | እንደግ | እኛ |
| እናውጋ | እንቀራረብ | እንዲሁም | እኛም |
| እንላቅ | እንቢ | እንዴ | እውነተኛ |

ያለፈው የሰንጠረዥ ፩ መልስ <u>ወየው ሀገሬ</u> ነው።


## ያለፈውን ሰንጠረዥ የመለሱ

1. ደረጀ አሰፋ – ከላስ ቬጋስ ለ4ኛ ጊዜ
2. አስናቀ አሰፋ — ሂውስተን ለ3ኛ ጊዜ
3. ሰላማዊት መኰንን– ከሳን ሆዜ ለ3ኛ ጊዜ
4. ጋሻው ታፈረ – ከሎሳንጀለስ ለ3ኛ ጊዜ
5. መስፍን ወርቁ – ከሳንዲያጎ ለ2ኛ ጊዜ
6. ተስፋሁን ልጅ ዓለም – ከኦሃዮ ለ2ኛ ጊዜ
7. ትዕግስት ጥላሁን – ከሴንት ሉዊስ
8. ኑር ሁሴን – ከፕሌኖ
9. ታዬ ጥበቡ – ከቨርጂኒያ

(ሳያቋርጡ 5 ሰንጠረዥ በትክክል ሞልተው በወቅቱ በአድራሻችን ለሚልኩ ሶስት እትም በነፃ እንሸልማለን)



# ቃላት በሰንጠረዥ



ይህን ሰንጠረዥ የላከልን ኮሚዲያን አብርሃም ወልዴ ነው።

## ወደ ጎን

1. ትክክል ያልሆነ
4. ማያያዝ
8. ጠላ መጥመቂያ
9. ዕውቀት ልገብይ
11. እህል ሲያሰኝ
12. በወረቀት ላይ ታኑርልህ
14. መረከብ
15. ከፊት ትሁን
17. ያልደረሰ ጠላ
18. የውስጥ እጅ
20. ቅብብል
22. _______ና ምሣሌ
23. ጾም ቀን
25. ነጠቀች
27. መደሰት
29. ማምታታት
32. ውድ አለመሆን

33 መራድ
35. በሽታ
36. ባለጌ
37 እርጉዝ

## ወደ ታች

1. ፍርሃት
2. ፎቅ
3. ረዣዥም
4. ጣፋጭ
5. ተስማማው
6. አፀዳዱ
7. ከገላሽ በላይ ያለውን
10. ወረቀት መያዣ
13. እንጀራ በወጥ ላቁጦ
16. ለሰው የሚለገሱ
18. መበጣበጥ
19. ልጁን ለባል ሰጠ
21. ዙሪያ ጥምጥም
24. ሐኪም ጋ ወሰደኝ
25. ቅምጥል
26 ዱቄት ማድረግ
27. መመሪያ
28. ያልተጠበቀ ነገር ሲሆን የሚሰበር
30. የጾታ ዓይነት
31. አራከሰ
34. ጥሪ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

| | 12 ISSUES | | 6 ISSUES | |
|---|---|---|---|---|
| U.S | $30.00 | ☐ | $16.00 | ☐ |
| Canada | $40.00 | ☐ | $22.00 | ☐ |
| Europe | $56.00 | ☐ | $30.00 | ☐ |
| Asia | $70.00 | ☐ | $38.00 | ☐ |
| Institutions | $80.00 | ☐ | $40.00 | ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* ______________ *Phone:* (     ) ______________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* ______________ *Phone:* (     ) ______________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*

# RE/MAX®
**today's inc.**
an independent member broker

የንግድ ሥራ መግዛት
ለምትፈልጉ

Business Broker
Convinient Store
Liquor Store
Dry Cleaning & so on

**FINANCING AVAILABLE**

እንኳን ለአዲሱ ዓመት
በሰላም አደረሶት!

- √ Residential
- √ Commercial
- √ Business
- √ Relaocation
- √ Forclosures
- √ HUD

ቤት መግዛት ለምትፈልጉ
መሬትም ገዝታችሁ መሥራትም ሆነ
Subdivision ውስጥ ለማሠራት የምትፈልጉ
ሁሉ ደውሉልኝና እረዳችኋለሁ።
የክሬዲት ችግር ቢኖርቦትም ደውሉልኝ!
ሁልጊዜ ኮሚሽን የምከፈለው በሻጭ ነው



ሰላማዊት ታደሰ
Selamawit "Sammy" Tadesse
Realtor
Remax Today's Inc
1597 Phoenix Blvd Suite 5
College Park, GA 30349

Tel. (770)907-0525
(770)907-0183
Voice Mail: (770)798-7496
Fax: (770)907-0524

# አባይ ምግብ ቤት
## Abay Ethiopian Restaurant

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረስዎ!
አዲሱን ዓመት ፲፱፻፺፫ን ለመቀበል ምሽቱን ከኛ ጋር አሳልፉ።
HAPPY ETHIOPIAN NEW YEAR!!



እንቁጣጣሽ
በያመቱ
ያምጣሽ!!

የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉና
ብቅ ብለው በደስታ እናስተናግዶት።
በዕረፍት ቀናት ምሽት የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።

*Authentic Ethiopian Restaurant*
Have a spicy authentic Ethiopian Dinner
and stay for the cultural Entertainment on weekends

3375 Buford Highway #1050
Atlanta, GA
(404)321-5808

# ሀናና ብንያም ምግብ ቤት

## H & B Restaurant

## Ethiopian Cuisine & Bar



በቅርቡ ሥራውን የጀመረው
ሀናና ብንያም ምግብ ቤት የውድ
ደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በልዩ
ዝግጅትና መስተንግዶ የባህል
ምግቦችን ያቀርባል።

በተጨማሪም ዘወትር ዓርብ፤
ቅዳሜና እሁድ የተለያዩ
የምሽት የመዝናኛ
ፕሮግራሞችን
ያቀርብላችኋል።

**H & B Restaurant**

*Ethiopian Cuisine & Bar*

4600 A. E. Ponce DeLeon Ave.
Clarkston, GA 30021
Phone: (770)723-0502






መጥተው ይጎብኙን!!
በመስተንግዶአችን ይኮራሉ።

በተጨማሪ በ431 N. Indian Creek, Suite
በሚገኘው ሀናና ብንያም በተሰኘው
የኢትዮጵያ ሸቀጦች መደብራችን የበለ
በማሻሻል እንጀራ፤ በርበሬና
የመሳሰሉትን፤ እንዲሁም የአገር ልብስና
ጌጣጌጦች በጥሩ ሁኔታ እናቀርባለን።
ጎብኙን!!
ስልክ ቁጥር (404) 296–2766